ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ

በ
ሃፍታይ ገ/እግዚኣብሔር አለማዮህ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጥር 2003 ዓ.ም

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ

በ

ሃፍታይ ገ/እግዚአብሔር አለማዮህ

አማካሪ

ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

ጥር 2003 ዓ.ም

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ

በ

ሃፍታይ ገ/እግዚኣብሔር አለማዮህ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ

ፈቃዱ ካሀዘዞ


ፈታኝ

ሀፍታይ መንግሥቱ ኪሮስ

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ. ፕ. ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

Administrative Region and Woreda Map of Tigray



LEGEND

- Region
- Woreda

Zone

- C. Tigray
- E. Tigray
- Mekele
- S. Tigray
- W. Tigray

Disaster Prevention and Preparedness Agency

Administrsative Map of Tigray Region

Map No: 001/DPPA/Administrative/13/Tigray

The delineation of national and international boundaries must not be considered authoritative
Data courtesy of DPPA
©DPPA Information Center 2006

ምስጋና

ለፍጻሜው ላደርስከው እግዚኣብሔር ክብር ምስጋና ይገባሃል። በመቀጠል "አሀ! የት ደረሰ? እንደልጅ ተቆጣጠርኩህ አይደል!? የሚሉ አባታዊ ቃሎቻቸው ሳይለየኝና የነበራቸው የስራ መደራረብ ሳያግዳቸው ይህ ስራ ለፍጻሜው እንዲበቃ የጎበጠውን በማቃናት፣ የተበላሸውን በማስተካከል እገዛቸው እስከመጨረሻዋ ሰዓት ላልተለየኝ አማካሪዬ ደ/ር ፈቃደ አዘዘ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ።

በመስክ ጥናቴ ከራሴ ደህንነት ጀምሮ አስፈላጊውን የመረጃ ትብብር ላደረጉልኝ የኩናማ ብሔረሰብ ሽማግሌዎች ያለኝ ምስጋና ከፍ ያለ ነው። እግዚአብሔር ያክብርልኝ።

በአስቸጋሪ ወቅቶች ከጎኔ ሳይለዩ በምክርም በገንዘብም አለኝታነታቸውን በተግባር ለገለፁልኝ ወላጆቼ አቶ ገብረእግዚኣብሄር አለማዮ እና ወ/ሮ ብርሃን ግደይ እጅግ በጣም አመሰግናችኋለሁ። ውለታችሁን ከፋይ ያድርገኝ።

እጮኛዬ ማሂ (ማህሌት ማሞ) ታጋሽነትሽን ምን ብዬ እንደምገልፀው ባላውቅም በተለመደው ቋንቋ ምስጋናዬ የላቀ ነው። እንዲሁም ጓደኛዬም የስራ ባልደረባዬም ሓድጉ ተካ ንጉስ ላደረግከው ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ። በመጨረሻም የዚህን ጥናት ረቂቅ በማረምና በማስተካከል ላገዛችሁኝ ጋሽ ደረጀ ገብሬ እና ወ/ሮ ሰላማዊት መካ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ፥ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙት ሦስት ብሔረሰቦች በኩናማ ብሔረሰብ የሚከናወነውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና የሚኖረውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳወቅ፣ እንዲሁም አስታራቂ ሽማግሌዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ምን ዓይነት ስልት እንደሚጠቀሙና ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደቱ ምን እንደሚመስል መተንተንና መግለጽ ላይ ነው።

ኩናማ ብሔረሰብ ወደ ግጭት ከሚያስገቧቸውና ለግድያ ግጭት ከሚያደርሷቸው ምክንያቶች ቅድመ ክርስትና ሃይማኖት መቀበል፥ ከኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር የተሳሰረ ሲሆን፤ ከክርስትና ሃይማኖት መጠመቅ በኋላ ደግሞ የኢኮኖሚው እንዳለ ሆኖ "በትዳር ላይ መወሰለት" ዋነኛው እንደሆነ የጥናቱ ግኝት ነው።

ኩናማ በነዚህና ሌሎች ምክንያቶች የተከሰተው ግጭት ስር ሰዶና ተስፋፍቶ የከፋ አደጋ እንዳያደርስ የሚከላከሉበት ብሎም ዘላቂ ሰላም የሚያሰፍኑበት ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ሂደት ሁለት ገፅታዎች አሉት። ቀላል የሚባሉ ግጭቶችን የሚፈቱ "ላጋኬ" የሚባሉ የሀገር ሽማግሌዎች ሲሆኑ፤ "ሳንጋኔና" ወይ የአጥንት አስታራቂዎች ተብለው የሚታወቁት ደግሞ የግድያ ግጭትን የሚፈቱ ናቸው። ላጋኬ ቀላል የሚባሉ የመንደር ግጭቶችን ዘላቂና ፍትሃዊ የሆነ ብይን በመስጠት የታወቁና በብሔረሰቡ አባላትም የታመነባቸው ናቸው። የግድያ ግጭትን በተመለከተም የገዳይ እና የሟች ቤተሰብ በማገናኘት ዳግመኛ ወደ ግጭት እንዳይመለሱ በመለመን (በማስፈራራት)፣ ስርዓታቸው በሚያዘው የዕርቅ ስርዓት በመፈፀምና መሃላ በማስፈፀም እንዲሁም ለሟች ቤተሰብ ከገዳይ ቤተሰብ የደም ካሳቸውን በአግባቡ በማስከፈል ረገድ ሳንጋኔና ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል።

ተጋጪዎች የፈፀሙትን ቃለ መሐላ በመፍራት፣ ለአስታራቂው ካላቸው ከፍተኛ እምነት እንዲሁም የአስታራቂው የትሰበራለህ፣ ዘርህ ይጠፋል ወዘተ. ያሉ ማስፈራርያም ማስታረቅያም ቃላትን በመፍራት በሳንጋኔና የተፈፀመው የዕርቅ ስርዓት ያፀናሉ። የብሔረሰቡ አባላትም ለሳንጋኔና ሕግ ተገዝተውና አምነው ይኖራሉ።

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና i

አጠቃለሎ ii

1. መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት 3

1.2 የጥናቱ አላማ 4

1.3 የጥናቱ ዘዴ 4

1.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ 5

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት 6

1.6 የጥናቱ መረጃ ምንጮች 7

1.7 የጥናቱ ወሰን 7

1.8 በጥናት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው 8

1.8.1 ያጋጠሙ ችግሮች 8

1.8.2 የተወሰዱ መፍትሔዎች 9

1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ ጠቃሚ ተመክሮ 11

2. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ 13

2.1 የኩናማ ብሔረሰብ ታሪክና ስያሜ 13

2.1.1 ታሪክ 13

2.1.2 ስያሜ 17

2.2 መልክዓ ምድር፣ የአየር ንብረትና ስነህዝብ 19

2.3 ጎሳ 21

2.4 ኢኮኖሚ 25

2.5 አስተዳደር 28

2.5.1 ልማዳዊ አስተዳደር 28

2.5.1.1 ላንኬ 39

2.5.1.2 ሳንጋኔና 30

2.5.2 ዘመናዊ አስተዳደር 30
2.6 ቋንቋና እምነት 31
2.6.1 ቋንቋ 31
2.6.2 እምነት 32
2.7 ልደትና ስያሜ 33

3. የግጭት ንድፈ ሓሳባዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጥናቶች 35
3.1 የግጭት ብያኔ 35
3.2 የግጭት ዓይነቶችና ደረጃዎች 37
3.3 የግጭት መንስኤዎች 39
3.4 የግጭት አፈታት ዘዴዎች 40
3.5 ተዛማጅ ጥናቶች 41

4.ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ 42
4.1 የግጭት ምንነት በኩናማ ብሔረሰብ 42
4.2 የግጭት መነሻ ምክንያቶች 43
4.3 ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት 44
4.3.1 ላጋኬ 45
4.3.1.1 ላጋኬና የባልና ሚስት ፍቺ 46
4.3.1.2 የካላ (የአውጫጪኝ) ስርዓት እና ላጋኬ 49
4.3.1.3 ላጋኬና ዕፀኞች 51
4.3.2 ሳንጋኔና 53
5. ማጠቃለያ 66
6. ይሁንታዎች 68
ዋቢ. መፃሕፍት (References) 70

አባሪዎች

- አባሪ አንድ አውራ የመረጃ አቀባዮች አጭር መግለጫ
- አባሪ ሁለት የአጋዥ መረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር
- አባሪ ሦስት ፎቶግራፎች

1. መግቢያ

ግጭት በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው። በግለሰብ፣ በቡድን እንዲሁም በሃገር ደረጃ ሊታይ ይችላል። ግጭት እንደ ደረጃውና እንደ ባህርየ ፍጥረቱ የተለያዩ መቆጣጠርያ እና ማርገብያ መንገዶች አሉት። ከነዚህም በዋናነት ዘመናዊና ባህላዊ ሕጎችና ደንቦች ሊያደርሰው ከሚችለው ጉዳት ለመታደግ አገልግሎት ላይ ውለው ይታያሉ።

ዘመናዊው የግጭት ማስወገጃ ስርዓት፣ ምንም እንኳን በተወሰነ መልኩ ከመንግስት መንግስት ከአገር አገር ከአካባቢ አካባቢ ቢለያይም በአካባቢው ሰላምና መልካም አስተዳደር እንዲኖር ህግና ደንብ ይደነግጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ማህበረሰቡ ባህላዊ ስርዓቶችና ህጎችን ከትውልድ ትውልድ ሲረካከባቸውና ሲቀባበላቸው የቆዩ ግጭቶችን የሚያረግብባቸው ብሎም የሚፈታባቸው ሂደቶች አሉት።

ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ረዘም ላሉ ዘመናት ትኩረት ሳይሰጣቸው ወይም በመደበኛው ስርዓት ተዕዕኖ ስር ወድቀው ቢቆዩም አንዳንዶቹ ግን ስርዓቱን ጠብቀው ከዘመን ዘመን ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገሩ እስከአሁን ቆይተዋል ወደፊትም ይኖራሉ። ሃገር በቀል ከሆኑ ባህላዊ ተቋማት መካከል የኩናማ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሞች "ሳንጋኔና" እና "ላጋኬ" ተጠቃሾች ናቸው።

በኩናማ የሚፈፀመው የዕርቅ ስነ ስርዓት በብሔረሰቡ ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ አስታራቂዎቹም በህዝቡ ዘንድ ልዩ አክብሮትና ተሰሚነት ያላቸው ናቸው። በሳንጋኔና እና በላጋኬ የሚፈፀመው የዕርቅ ስነ ስርዓት በጣም ረጅምና አድካሚ ቢሆንም በህብረተሰቡ የተፈጠሩ ግጭቶችን አስወግዶ ዘላቂ የሆነ ዕርቅና ስምምነት በማምጣት ረገድ ለብሔረሰቡ ከፍተኛ አስተጽኦ የሚያበረክት ነው። ስለሆነም፥ የዚህ ጥናት ትኩረት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል፣ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ የኩናማ ብሔረሰብ ከዘመን ዘመን ከትውልድ ትውልድ እያሸጋገሩ ያቆዩትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት አጠቃላይ ገፅታ ምን እንደሚመስል እና ያለውን ማህበራዊ ፋይዳ መግለፅ ነው።

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን ምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ ነው። በስሩም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ የመረጃ አሰበሰብ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የጥናቱ ወሰን፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው እንዲሁም የመስክ ተሞክሮ ያካተተ ነው። ምዕራፍ ሁለት ጥናቱ የተካሔደበትን አካባቢ አጠቃላይ ገፅታ የሚያመለክት ነው። ስለሆነም፣ የብሔረሰቡን ታሪክ እና ስያሜ፣ መልክዓ ምድር፣ የአየር ንብረትና ስነ ህዝብ፣ ጎሳ፣ ኢኮኖሚ፣ ባህላዊ አስተዳደር፣ ቋንቋና እምነት፣ ልደትና ስያሜን የሚያስረዱ መረጃዎችን አካቷል።

በምዕራፍ ሶስት የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት፣ የግጭት ብያኔና የግጭት መንስኤዎች፣ የግጭት አይነቶችና የግጭት አፈታት ዘዴዎች የሚሉ አጠቃላይ የግጭት ንድፈ ሃሳባዊ ዳራዎች ቀርበዋል።

ምዕራፍ አራት፣ የኩናማ ብሔረሰብ አባላት ስለ ግጭት ያለውን አመለካከት፣ ለግጭት መከሰት መነሻ የሚሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶችና ግጭት ሲከሰት እንዴት በባህላዊ ዘዴ እንደሚፈታ አጠቃላይ ሂደቱን ያመለክታል። ምዕራፍ አምስት ደግሞ ማጠቃለያና ይሁንታዎችን ይዟል። በመጨረሻም ዋቢ መፃሕፍትና ጥናታዊ ፅሑፎች እንዲሁም የአባሪዎች ዝርዝር ይገኙበታል።

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔረሰቦች (ethnic groups) አገር መሆንዋ ይታወቃል። ከእነዚህ ብሔረሰቦች መካከል የተወሰኑት፤ በመጀመርያ እና በሁለተኛ ዲግሪ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት የኢትዮጵያ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር አጥኚዎች ለመዳሰስ ተሞክረዋል። ሆኖም ከ Alexander (1982[1])፤ Cittadini (1967)፤ ቆርነሊዎስ (1980)፤ ገ/ኪዳን (1988)፤ በስተቀር ሌላ በኩናማ ብሔረሰብ ባህል ላይ የተደረገ ጥናት ለማግኘት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላይብረሪዎች እንዲሁም በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ላይብረሪዎች ዳሰሳ አድርጌ አላገኘሁም። ስለሆነም የዚህን ብሔረሰብ ባህል ወደ አካዳሚያ ማምጣትና ለጥናትና ለምርምር ማዋል እንደሚያስፈልግ በማሰብ ለማጥናት አነሳስቶኛል።

ሁለተኛውና የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን *"ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ"* እንዳጠና ካነሳሳኝ ምክንያት፤ በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ቅጥር ግቢ አቶ ክልካይ የተባለ ወዳጄን በኩናማ ብሔረሰብ ላይ ማጥናት እንዳሰብኩ ስነግረው፤ እጅግ አስገራሚ የሆነ የግጭት አፈታት ስርዓት እንዳላቸው የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች ሰጠኝ፤ ምንም ሳላቅማማ በውስጤ የነበረውን ብሔረሰቡን የማጥናት እና ወደ አካዳሚያ የማምጣት ፍላጎቴን በበለጠ አጠነከረልኝ።

[1] እዚህ ጥናት ላይ የተገለገልኩባቸው የመረጃ ምንጮች በውጭ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆኑ ዘመኑም በውጭ፤ በሀገር ውስጥ ቋንቋ የተጻፉ ሲሆኑ ደግሞ ዘመኑ በኢትዮጵያ አቆጣጠር እንደሆነ ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ፥ በኩናማ ብሔረሰብ የሚከናወነውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና ያለውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሣወቅ፣ እንዲሁም አስታራቂ ሽማግሌዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ምን ዓይነት ስልቶች እንደሚጠቀሙና ባህላዊ የግጭቶች አፈታት ሂደቱ ምን እንደሚመስል መግለፅ ላይ ያተኮረ ነው። ጥናቱ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በሂደት ይመልሳል።

- በብሔረሰቡ በዋናነት የሚፈጠሩ ግጭቶችና ዋነኞቹ መከሰቻ ምክንያቶች ምንድ ናቸው?
- የተፈጠረውን ግጭት ለመፍታት የሚካሄደው ስርዓትስ ምን ይመስላል?
- ባህላዊው የግጭት አፈታት ስርዓት ለመምራትና ለመወሰን የሚፈቀድለት የብሔረሰቡ ጎሳ የትኛው ነው?
- በዚህ ባህላዊ የግጭት ማርገብያ ዘዴ ከአንዱ ጎሳ የተመረጠው አስታራቂ አራቱንም ጎሳዎች በእኩል መንገድ ያስተናግዳል?
- የብሄረሰቡ አባላት በባህላዊው የእርቅ ስርዓት ያላቸው እምነትና ተገባርነት ምን ይመስላል?

1.3 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኩናማ ብሔረሰብ የሚፈፀመውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ሂደት ማሳየት ላይ እንደመሆኑ፤ የዕርቁ ስነ ስርዓት ሂደት ከተለያዩ መረጃ አቀባዮችና ምንጮች በተገኙ መረጃዎች በትክክል በማብራራት ትክክለኛ ገፅታውን የሚያሳይ ገላጭ የምርምር ዘዴ (descriptive study) ነው። እንዲሁም ባህላዊ አስተራቂዎች ተጋጪዎችን ለማስታረቅ እና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚጠቀሙበትን ስልት፣ ተምሳሌት ትርጉምና አገልግሎት ከነምክንያቱ ለማሣየት የይዘት ትንተና (content analysis) ተጠቅሜያለሁ።

1.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ወደ መስክ ስራ ከመሰማራቴ በፊት በርዕሰ ጉዳዩ ትውራዊ እውቀት ለመጨበጥ እችል ዘንድ በቤተመፃህፍት ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ምንጮች ስለ ግጭትና መንስኤ ምክንያቶች እንዲሁም አጠቃላይ ስለመስክ እና መስክኛ የመስክ ትምህርት ስማር ባገኘሁት እውቀት በመጠቀም፤ እንዲሁም ስለሚጠናው ብሔረሰብ አንዳንድ ጽሑፎች በማገላበጥ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ። ቀጥሎም ከመስክ ጥሬ መረጃን መሰብሰቢያ በሆኑት ቃለ መጠይቅ (interview) እና ምልከታን (observation) (Goldstein, 1964 እና ፈቃደ፥1991) በመጠቀም በቪድዮ፤ በፎቶግራፍ እና በቴፕ ሪከርደር በመቅረፅ መረጃ ለመሰብሰብ በማቀድ ተንቀሳቅሻለሁ።

በመስክ ተገኝቼ ምልከታና ቃለ መጠይቅ በማደርግበት ወቅት መረጃዎች ካጋጠሙኝ በተፈጥራዊ መቼት (natural setting) ካልሆነ ደግሞ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት (induced natural setting) በማዘጋጀት፤ ሁለቱም ሳያመቹ ሲቀሩ ደግሞ በአርቴፊሻል መቼት (artificial setting) ለመሰብሰብ አቅጄ ሄጀ ነበር።

ሆኖም፥ ተፈጥሯዊ መቼቱን ለማግኘት፤ ከጥር 2002 ዓ.ም እስከ መስከረም 2003 ዓ.ም ባደረግኩት ክትትል ፈፅሞ አልተቻለም። የመስክኛ መርሁ እንደሚያስረዳው ከፍ ተብሎ በተጠቀሱት ሌሎች የመቼት ዓይነቶች በቅንብር ተፈጥሮአዊና አርቴፊሻል መቼት ለመጠቀም ጥረት ባደርግም፤ ሚርትና ርክሰት በሚባሉ ሁለት ዋና ዋና የብሄረሰቡ እምነቶች ምክንያት ሳይሳካ ቀርቷል።

በኩናማ ብሔረሰብ "ሚርት" ላይ ከፍተኛ እምነት አለ። ስለሆነም፥ ባህላዊ የፅርቅ ስርዓት ሂደት ከፍ ሲል በተገለፀው የጊዜ መጠን ተፈጥሮአዊ መቼቱን ስላላገኘሁ በቅንብር ተፈጥሮ ወይ በአርቴፊሻል መቼት እንዲያዘጋጁልኝ በተማጠንኳቸው ጊዜ፤ የባህላዊ ተቋሙ አስታራቂ (ሳንገሰኔና) የሆኑት ካሽኪ ዑመር በአስተርጓሚያቸው አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ በኩል "ይህ ሚርት ነው። ሰው ሳይሞት ሞተ ብሎ መስራት የተኮነነ ነው። በህዝባችን... በብሔረሰባችን ላይ እልቂት ይመጣል መአት ልታመጡብን ነው ወይ" በማለት እምቢተኝነታቸው አፅንተዋል።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እንዲህ በቀላሉ ሰው ሳይሞት ሞተ ተብሎ ቢሰራና የዕርቅ ስርዓቱ ቢፈፀም በአስታራቂውና በዕርቅ ስነ ስርዓት ሂደቱ ያለው እምነት ይጠፋል የሚል ነው። ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣውን የብሔረሰቡን መተዳደርያ ሥርዓት ማርከስ ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ሌላ እውነተኛ ዕርቅ ቢያጋጥም ህዝቡ አሜን ብሎ ለማመን ይቸገራል፤ የታራቂው እምነት ይሸረሸራል ሲሉ አስታራቂው ጨምረው ገልፀውልኛል። በመሆኑም፥ በነዚህ ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የዕርቅ ስነ ስርዓት ሂደት መቼትን በካሜራ ሳልቀርፅም... ሳልመለከትም ቀርቻለሁ።

ስለሆነም፥ ጥናቱ የተካሄደው ለተመረጡ የመረጃ አቀባዮች ጥልቅ ቃለመጠይቅ (interview) በማድረግና የቡድን ውይይት (focus group discussion) በማካሄድ ነው። እንዲሁም ብሔረሰቡ በሚገኝበት ወረዳ ከሚታተሙ መፅሔቶች፤ ጥራዞች እና ከአንዳንድ የስነልሳን ትምህርት ክፍል ጥናታዊ ፅሁፎች፤ በግል ካገኘሁዋቸው ለህትመት ያልበቁ ሰነዶች፤ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን በ1995 ዓ.ም. "የኩናማ ባህል" በሚል ርእስ ካሰራጨው ፕሮግራም እና ሌሎች መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። በዚህ መልክ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአግባቡ ከተደራጁና ስርዓት ከያዙ በኋላ የፅሑፍ ስራው ተከናውኗል።

1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

በኩናማ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት ላይ ትኩረት ያደረገው ይህ ጥናት፤ የተለያዩ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል። የብሔረሰቡን ማንነትና ማህበራዊ ህይወት ያስተዋውቃል፤ የአካባቢውን ትውፊታዊ ልማድ ወደ አካዳሚያ ያመጣል፤ ሃገር በቀል እውቀቶች የተሻለ ትኩረት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል። እንደዚሁም መደበኛ የፍትህ አካላት ከተመክሮው ዕውቀት የሚቀስሙበትን መንገድ ይጠቁማል የሚል እምነት አለ።

1.6 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት ሲካሄድ ከዕሑፍ መረጃዎች በተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት በአብዛኛው ትኩረት ያደረግኩት በብሔረሰቡ ውስጥ በታሪክ አዋቂነታቸውና በብሔረሰቡ የዕርቅ ስነ ስርዓት ተካፋይነታቸውና አስታራቂነታቸው ከሚታመንባቸው የአገር ሽማግሌዎች የተመረጡትና የአካባቢው የመንግስት ሃላፊዎች ዋነኞቹ ናቸው። የመረጃ አቀባዮቹ ከ 35 እስከ 90 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሆነው ከአራቱም የብሄረሰቡ ጎሳዎች አባላት ናቸው። እንዲሁም ስለ ግጭት አጠቃላይ ንድፈ ሀሳብ የመስኩ ምሁራን የፃፉዋቸው ልዩ ልዩ ስራዎች፣ ብሄረሰቡን አስመልክቶ የተፃፉ የጥናት ወረቀቶች መፅሔቶች እና ሌሎች ሰነዶች በማሰባሰብ በጥናቱ ተጠቅሜባቸዋለሁ።

1.7. የጥናቱ ወሰን

ኩናማ ብሔረሰብ በኤርትራና በኢትዮጵያ ይገኛል። በተጨማሪም ከኤርትራ ተሰደው የመጡ የብሔረሰቡ አባላት በትግራይ ክልል የስደተኞች ካምፕ በሆነው "ሽመልባ" በተባለ ቦታ ይገኛሉ። ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኢትዮጵያ፣ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ በወረዳ ታሕታይ አድያቦ በሚገኙት የብሔረሰቡ አባላት ላይ ብቻ ነው። በተለይ (ገዛ መቐር፣ ገዛ አዱራ፣ ዕርዲ ወያነ፣ መዳበ፣ ሽምኒ፣ መንጠብጠብ) በሚባሉ ቀበሌዎች የሚገኙ አባላት ባላቸው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ነው። እነዚህ አካባቢዎች የተመረጡበት ምክንያት በቁጥር ብዛት ያላቸው የብሄረሰቡ አባላት የሰፈሩባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው እና ከሌላው በተሻለ መልኩ ለደህንነት የተመቹ ቦታዎች በመሆናቸው ነው።

በተጨማሪም በአንድ ማሕበረሰብ ውስጥ በርካታ የግጭት ዓይነቶችና የአፈታት ስርዓቶች እንደሚኖሩ ይታወቃል። በዚሁ ብሔረሰብም በርካታ የግጭት ዓይነቶች እና የአፈታት ስርዓቶች ቢኖሩም በዋናነት በግድያ ግጭትና የአፈታት ስርዓቱ ላይ ተወስኖ የቀረበ ጥናት ነው።

1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎች

1.9.1 ያጋጠሙ ችግሮች

አንድ የመስክ አጥኚ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ በሚያደርገው የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ውስጥ ከሚጠናበት አካባቢ ሁኔታ እንዲሁም ከመረጃ አቀባዮች በርካታ ችግሮች እንደሚገጥሙት የታወቀ ነው። እኔም መረጃዎችን በየቀበሌዎቹ በመዘዋወር በማሰባስብበት ወቅት በርካታ ችግሮች ገጥመውኛል። ያጋጠሙኝ ችግሮች በርካታ በመሆናቸው ሁሉንም እዚህ ለማካተት ባይቻልም የተወሰኑትንና ዋና ዋና ችግሮች ናቸው ያልኳቸውን ልጥቀስ።

- ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ የሙቀት መጠኑ ከ 40 እስከ 50 ዲግሪ ሴንትግሬድ በመሆኑ ካደግኩበትና ከኖርኩበት አካባቢ አየር ፀባይ ፍፁም የተለየ በመሆኑ ስራዬን በአግባቡና በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዳላከናውን በጤናየ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ፈጥሮብኛል።
- "ካላዛር" የተባለ በሽታና የወባ በሽታ የተስፋፉበት አካባቢ በመሆኑ እነዚህ በሽታዎች በተለይ "ካላዛር" የሚባለው በሽታ ምንም ሕክምና ሳይገኝለት ለረጅም ጊዜ የአካባቢውን ሰው ስለ መጉዳቱ መረጃ ስለነበረኝ በስራዬ ላይ የስነ ልቦና ጫና አሳድሮብኛል።
- አካባቢው ድንበር አካባቢ እንደመሆኑ ሁሉም ሰው አዲስ የመጣ ሰውን በአካባቢው አነጋገር "ፀጉረ ልውጥ" ሲመለከቱ በተጠንቀቅ ዓይን ይጠብቁታል። በዚህ ምክንያት መረጃ ለመጠየቅ ብቻ ሳይሆን በነፃነት ለመንቀሳቀስም አስቸጋሪ ነበር። ይህም በመሆኑ ከአካባቢው ሰው ለመላመድና የመጣሁበትን ዓላማ ለማስረዳትና ለማሳመን ረጅም ጊዜን ወስዷል።
- በአካባቢው "የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ነን" የሚሉ፤ እንዲሁም ከብሔረሰቡና በአጠቃላይ ከክልሉ ወንጀል ሰርተው የተሰወሩ "ሽፍቶች" ይገኛሉ። የተቃዋሚዎቹ ልዩ ስማቸው "ደምህት"[2] ነው። እነዚህ ወደ አካባቢው ሰርገው በመግባትና ከአካባቢው ህዝብ ጋር በመመሳሰል እንደኔ ዓይነቱን ለአካባቢው አዲስ ሰው ሲያገኙ "ከመንግስት የተላከ ሰው

[2] ደሞክራስያዊ ምንቅስቃስ ህዝቢ ትግራይ (የትግራይ ህዝብ ዴሞክራስያዊ እንቅስቃሴ)

ነው" በሚል እስከመግደል ይደርሳሉ። አለዚያም አግተው ለኤርትራ መንግስት በማስረከብ በአገሪቱ ቴሌቪዥን ጣብያ እንዲናገር የማድረግ ልማድ እንዳላቸው መረጃዎች ነበሩኝ። ይህም በስራዬ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ካሳደሩብኝ ችግሮች አንዱ ነው።

- ሌላው የብሄረሰቡ አባላት በተወካያቸው ካልተነገራቸው በስተቀር ለመረጃ ክፍት አለመሆናቸው ነው። የብሄረሰቡ ተወካይ የሆኑትን አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴን በማግኘት ችግሩን ለመፍታት ብሞክርም ግለሰቡ በወቅቱ በነበረው የምርጫ ሳቢያ በኋላም በበርካታ ስብሰባዎችና ጉባኤዎች ላይ ተካፋይ ስለነበሩ እርሳቸውን ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖብኝ ሰንብቷል።

- የባህላዊ የፅርቅ ስርዓት ሂደትን መቼት ማግኘት አለመቻል ሌላው ችግር ነበር። ይህም በመሆኑ በተለመደው የመስክ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ በአርቴፊሻል መቼት ለማድረግ ጥረት ባደርግ የብሄረሰቡ አባላትና ሽማግሌዎች "ሚርት" ነው፣ "ይረክሳል"፣ እምነት ያጣል በማለት እምቢተኝነታቸውን አፅንተዋል።

- ብሄረሰቡ ወደሚገኝባቸው ቀበሌዎች ለመድረስ ካረፍኩበት "ሽራሮ" ከተማ በግምት በጣም የቀረበው የአንድ ሰዓት ተኩል፣ የራቀው ደግሞ የሁለት ሰዓት ተኩል የእግር መንገድ ያስፈልጋል። የትራንስፖርት አቅርቦት ባለመኖሩ በየቀኑ ወደነዚህ ቀበሌዎች መጓዝን አንዱ ፈታኝ ችግር ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

1.9.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

ከላይ የተገለፁትን ችግሮች ለመወጣት የወሰድኳቸው መፍትሄዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የአካባቢውን የአየር ፀባይ ለአካባቢው አዲስ የሆነ ሰው ለመልመድ ቢቸገርም፤ እንደ አካባቢው ሰው አለባበሴን በማስተካከል *(በጃፓኒ፣ በስስ ካናቴራ እና በነጠላ ጫማ)* እንዲሁም ጥላ በመግዛት በተወሰነ መልኩ ጸሓዩንና ሙቀቱን ለማስወገድ እንደ አማራጭ ወስጃለሁ።

- በሽታውን ከህክምና ባለሙያዎችና ከአካባቢው ሰው ጋር በመወያየት ስነ ልቦናየን ከመጠገን እና የበሽታው ሰበብ የሆኑት ትንኞች የሚገኙበትን አሸዋማ ቦታ ላለመርገጥ ጥንቃቄ ከማድረግ ውጪ የወሰድኩት እርምጃ አልነበረም።

- "ፀጉረ ልውጥ" ከሆንኩባቸው ሰዎችም ለተወሰኑት ሰዎች የመጣሁበትን ዓላማ በማስረዳት በእኔ ላይ ያላቸውን ያለመተማመን ስሜት ቀስ በቀስ ለማቃለል ችያለሁ። በተለይ የብሄረሰቡ አባልና የወረዳው የመንግስትና ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ የሆኑት አቶ ብርሃነ ሃይለ ጋር ከተገናኘንና ዓላማዬን ከነገርኳቸው በኋላ፤ ያረፍኩበት ሆቴል ድረስ በመምጣት የመጣሁበትን ዓላማና ማንነቴን በመግለፅ፣ ባለሆቴሎቹ ደህንነቴን እንዲጠብቁልኝ በማድረግ ከፍተኛ እገዛ አድርገውልኛል።

- ከገዳዮቹና ከአጋቾቹ ለማምለጥ የተወሰደው እርምጃም፣ በብሄረሰቡ ተወካይ አስተባባሪነት አካባቢውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሁለት ታጣቂ ሚሊሻዎች ስለተመደቡልኝ ስራዬን ያለ ስጋት እንዳከናውን መልካም ሁኔታ ፈጥሮልኛል።

- መረጃ ለማግኘት የግድ አቶ ብርሃነን በትእግስት መጠበቅ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነበር። ከተገናኘንና ከተዋወቅን በኋላም በየሄዱባቸው የገጠር ስብሰባዎች ይዘውኝ በመሄድ እና ማንነቴን በመግለፅ ከብሄረሰቡ ጋር አስተዋውቀውኛል። በዚህም ምክንያት ከህብረተሰቡ ጋር በቀላሉ ለመግባባት ችያለሁ።

- ለጥናቱ ተፈጥሯዊ መቼት ማዘጋጀት ባለመቻሉ የተፈጠረውን ችግር በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት መረጃውን በመሰብሰብ ችግሩን ለማቃለል ሞክሬያለሁ።

- በመጓጓዣ ረገድ አንዳንድ አመቺ በሆኑ ቦታዎች ብስክሌት በመዋስና በመከራየት፣ አመቺ ባልሆኑ ቦታዎች ደግሞ በእግር በመጓዝ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

1.10. በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ ጠቃሚ ተሞክሮ

ወደ ጥናት ቦታ ከመሄዴ በፊት የሚጠናው አካባቢ ምን እንደሚመስል ከተለያዩ ፅሑፎችና ግለሰቦች በቂ መረጃ ሰበሰብኩ። በመቀጠል በአካባቢው ከብሄረሰቡ ጋር የሚያስተዋውቀኝና አላማዬን በውል ተረድቶ የብሄረሰቡን አባላት የሚያስረዳልኝ ሰው ለየሁ። የመረጥኳቸው ሰው አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ ይባላሉ። አካባቢውን ለመቃኘት (pilot survey ለማካሄድ) እና ግለሰቡን ለመተዋወቅ መጋቢት 30፣ 2002 ዓ.ም. የመጀመርያውን የመስክ ጉዞ አካሄድኩ። አካባቢውም ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ቻልኩ። ግለሰቡን ለማግኘት ግን አልቻልኩም። ግለሰቡ በስብሰባ ምክንያት ከአካባቢው ወደ መቀሌ ከተማ መሄዳቸውንም ሰማሁ። በቀጥታም ከሽራሮ ወደ መቀሌ ተጓዝኩ። እንደተባለው ግለሰቡን መቀሌ አገኘሁዋቸው። ከአባቴ ጋር ሆነንም ሻይ ቡና እያልን ስለመጣሁበት አጠቃላይ ዓላማ አወጋሁዋቸው። ከቤተሰብም ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት እንዲኖራቸው አድራሻ ሰጠናቸው። በዚያው እለት መረጃ እንዴት ማግኘት እንደምችል እና በምን መልኩ ሊተባበሩኝ እንደሚችሉ ጥያቄ ሳቀርብላቸው ምንም ሊያሳስበኝ እንደማይገባና ከብሄረሰቡ አባላት ጋር በማስተዋወቅ እንዲሁም መረጃ ሰጪዎችን በመምረጥ እና ከነርሱም ጋር በማስተዋወቅ ሊረዱኝ እንደሚችሉ ጠቁመው "ለኔ ተወው ሆኖም ከመጣህበት ዩኒቨርሲቲ ይሁን ተቋም የትብብር ደብዳቤ አስፅፈህ አምጣ" ብለው፤ ደብዳቤ የሚጻፍላቸውን አራት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጠቅሰው ነገሩኝ። በመጀመርያ የጥናቱ አካባቢ ቅኝት ላይ እንዲህ ዓይነቱን መረጃ ይዞ መምጣት ለዋናው የመስክ ስራ እጅግ በጣም ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በዚህ መልኩ ከተለያየን በኋላ ተፈጥሯዊ መቼቱ ካጋጠመ እንደሚያሳውቁኝና እንደሚጠሩኝ በሰፊው ተነጋግረንበት ስለ ነበር በተደጋጋሚ ስልክ በመደወል ብከታተል ሊገኝ አልቻለም።

በተባልኩት መሰረት ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የተዘጋጀውን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ነሓሴ 25፣ 2002 ወደ አካባቢው በድጋሚ ተጓዝኩ። አቶ ብርሃነም በደስታ ተቀበሉኝ። የትብብር ደብዳቤውንም ወድያው አስነበብኳቸው። ወደ አካባቢው የደረስኩበት ሰዓት የስራ ሰዓት ስለ ነበር ወደሚመለከታቸው ቢሮዎች በመሄድ የትብብር ደብዳቤዬን በተነ·ልኝ።

ከሁለት ቀን ቆይታ በኋላ የብሄረሰቡ ዋና ዋና ሽማግሌዎች ወደሚገኙበት የብሄረሰቡ ልዩ ስብሰባ ይዘውኝ ሄዱ። በዚያውም ማንነቴንና የመጣሁበትን ዓላማ ለህዝቡ ገለፁ። ደግሞም "ከምንኮራበት ባህላችን አንዱ በሆነው በዕርቅ ስነ ስርዓት ላይ ጥናት ሊያደርግ ነው የመጣው" በማለት አከሉበት። ከዛ ቀን በኋላ የመንግስት ስራቸውን በመተው በቃላቸው መሰረት አውራ የመረጃ አቀባዮችን በማፈላለግ እና በማስተዋወቅ እንዲሁም በየገጠሩ ስዬድ ታጣቂ ሚሊሻ በመመደብና አብረውኝ በመሄድ ተሳትፈዋል። ይህ በመሆኑም ብሄረሰቡ የሚፈፅማቸውን ተግባራት አብሬያቸው እያከናወንኩ የሚበሉትንና የሚጠጡትን እየበላሁና እየጠጣሁ የብሄረሰቡን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት መረጃ ሰብስቤ ለመመለስ ችያለሁ።

2. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስር ጥናቱ የተካሔደበትን አካባቢ አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳዩ መረጃዎች ይቀርባሉ። ስለሆነም፣ የብሔረሰቡን ታሪክና እና ስያሜ፣ መልክዓ ምድር፣ የአየር ንብረትና ስነ ህዝብ፣ ጎሳ፣ ኢኮኖሚ፣ ባህላዊ አስተዳደር፣ ቋንቋና እምነት፣ ልደትና ስያሜን አስመልክቶ ገለጻ ይቀርባል።

2.1. የኩናማ ብሔረሰብ ታሪክ እና ስያሜ

2.1.1 ታሪክ

የኩናማ ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጥ ሲነሳ ግልፅና በመረጃ የተደገፈ መነሻ ማግኘት አልተቻለም። ሆኖም አንዳንድ የብሔረሰቡ አባላት፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ፀሐፍት በከፊልም ቢሆን የብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ ታሪክ ላይ ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ ሰንዝረው ይገኛሉ።

ኩናማ ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጡ ከአክሱም እንደሆነና በንጉስ ኢዛናም ይመራ እንደነበር ቆርኔሊዎስ÷ (1980፡1)፤ Nikodimos, (1987፡17)፤ Alexander, (1982፡3)፤ Alem, (1982:1) ይጠቅሳሉ። እንዲሁም Aster (1980 ÷1) " *The Kunnama claims to be desendants of King Bazen who ruled Aksum for seventeen years and his queen (Kuname*[3]*)*" በማለት አስፍራለች። በተጨማሪም አለቃ ታየ ገብረማሪያም (1955÷62) "ባዜን ከልደት በፊት በስምንት ዓመት ከልደት በኋላ ዘጠኝ ዓመት ዘመነ መንግስቱ 17 ዓመት" በአክሱምና አከባቢው እንደነበር አስቀምጧል።

በተመሳሳይ ኩናማ ብሔረሰብ በሚኖሩበት ወረዳ "ታሕታይ አድያቦ"[4] በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተመው "አድያቦና" የሚል መፅሔት ስለብሔረሰቡ አመጣጥ አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴን በመጥቀስ የሚከተለውን አስፍሯል።

---

[3] ንግስት "*kuname*" የንጉስ ባዜን ባለቤት እንደነበረችና ለኩናማ ብሄረሰብ የስም መጠርያ መነሻ እንደሆነች አንዳንድ የብሄረሰቡ አባላትና *Nikodimos (1987:17)* ይገልፃሉ።

[4] ሁለት አድያቦዎች ስለሆኑ ብሄረሰቡ የሚኖርበት የአካባቢ ስም ሆኖ ታችኛው የሚል ትርጉም አለው።

አመጻዕአ እዚ ብሔር ቅድም ክብል በንጉስ ባዜን ዘመነ መንግስቲ አብ ማእኸላይ ዞባ ትግራይ አክሱም ዝነብር ዝነበረ ሕዝቢ ኾይኑ ብምክንያት ካብ ውቅሮ ክልተ አውላዕሎ ዝመፀ ናይ ንጉስ ዳጌና ኩናት ምክፋትን ድሕሪ መራሒ ብሔረሰብ ኩናማ ንጉስ ባዜን ሞትን ተፈናቂሉ ናብ ምዕራባዊ ዞባ ትግራይ ናይሎሚ ሰሜን ምዕራብ ትግራይ መሬት አድያቦ [መዕዶ] (አድያቦና፣ 2001÷28) ::

የ [ኩናማ] ብሔረሰብ አመጣጥ ቀደም ሲል በንጉስ ባዜን ዘመነ መንግስት በትግራይ ማዕከላዊ ዞን አክሱም ይኖር የነበረ ሕዝብ ሆኖ [፣] "ከውቅሮ ክልተ አውላዕሎ" በመጣ የንጉስ ዳጌና ጦርነት መነሳት እና በንጉስ ባዜን ሞት ምክንያት [ከነበረበት አክሱም] ተፈናቅሎ ወደ ትግራይ ምዕራባዊ ዞን የአሁን ሰሜን ምዕራብ አድያቦ ምድር [መጣ] (አድያቦ፣ 2001÷28) ::

በማለት ሲያስቀምጥ ገ/ኪዳን ወ/ሃዋርያት በተመሳሳይ መልኩ እንደሚከተለው አትተዋል::

ብሔረሰብ ኩናማ ናይ ትውልዲ ዘርኢ ሐረጎም ምስ አክሱማዊ ንጉስ ባዜን ብምርኻብ ምቁዛር ይጅምሩ እዮም:: ቅድሚ ባዜን እውን አብ አክሱም ከባቢ ዝነብሩ ምንባሮምን አብቲ ቦታ ዓብዩ ግደ ከም ዝነበሮምን ይዝክር (1988÷2)::

የኩናማ ብሔረሰብ የትውልድ ዘር ሐረጋቸውን ከአክሱማዊው ንጉስ ባዜን በማገናኘት መቁጠር ይጀምራሉ:: ከ[ንጉስ] ባዜን በፊትም አክሱም አካባቢ ይኖሩ እንደነበር እና በቦታው ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ይነገራል (1988÷2)::

የኩናማ ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጥ ከአክሱም መሆኑንና ንጉሳቸውም ንጉስ ባዜን ከባለቤቱ ከንግስት ኩናሜ ጋር እንደነበር ከፍ ሲል የተቀመጡ መረጃዎች ያመለክታሉ:: ከዚህ ሀሳብ በተጨማሪ የብሔረሰቡ አባል የሆኑት አቶ ሃይለ ወለላ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል::

መቼም አንሕናኳ ቆልዑ ኢና ነይርና እንታይ ፈሊጥናዬ ኾይኑ ግና ወለድና ከምዝነግሩና፣ [ብሔረሰብ] ኩናማ አመፃዕኡ ካብ ግብሚ ከም ዝኸነ እዩ። ደሐር ድማ አክሱምን ከባቢኡን በረኻ /ሜዳ/ ስለዝነበረ አብኡ ሰፊሩ ንጉሱ ድማ ንጉስ ባዜን ኾይኑ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ገፅ 2)።

መቸም÷ እኛ እንኳን ልጆች ስለ [ነበርን] ምኑን አውቀነው ሆኖም ወላጆቻችን እንደነገሩን ኩናማ [ብሔረሰብ] አመጣጡ ከግብፅ እንደሆነ ነው። በኋላ አክሱምና አካባቢው በረኻ (ሜዳ) ስለነበር እዛ ሰፈረ። ንጉሱም ንጉስ ባዜን ሆነ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ገፅ 25)።

ቀደም ሲል ሲጠቀስ ከነበረው ሀሳብ ለየት ባለመልኩ፣ የኩናማ ብሔረሰብ የመጣው ከሱዳን እንደሆነ Trevaskis *(1980:4)* የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሯል። *"....Eriterean earliest inhabitants are believed to have been a "Nilotic people, Negroid"* [5] *forest dwellers who have moved from their homes in the thick of the South Eastern Sudan in to the Gash and Setit low lands". (የኤርትራ ቀደምት ነዋሪዎች ኒላውያን (ጥቁሮች) እንደሆኑ የሚታመን ሲሆን እነዚህም ከሚኖሩበት ጫካ በምስራቃዊ ሱዳን ወደ ጋሽ እና ሰቲት የተባሉ ቆላማ ቦታዎች ተበትነዋል።)*

ኩናማ ከኒላውያን ጋር በመጠኑም ቢሆን ግንኙነት እንዳለው ቆርኔሊዎስ (198÷4) ጠቅሰው÷ ባህላቸው እና ቋንቋቸው ሲታይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከኒላውያን ጋር ይገናኛል ሲሉ አስፍረዋል።

---

[5] *"Nilotic people, Negroid"* እያለ የሚጠራቸው የኩናማ ፣ብሄረሰብ ህዝብን ነው። ኩናማ ቀደም ያሉ መጠርያዎቹ ባርያ፣ ሻንቅላ ወዘተ. የሚሉ እንደነበሩ ሃይለ ወለላ ነግረውኛል። እናም የውጭ ጸሓፍት በአብዛኛው ይህንን ስም ሲገለገሉ ይታያል። በአሁኑ ሰዓት ይህንን ስም ለመጠርያነት መጠቀም በብሄረሰቡ ተወላጆች ክልክል ነው።

በተጨማሪም ገብረኺዳን፡-

> *ኩናማ ብሔረሰብ ናይ ዘርኢ ፍልፍሉ ኒሎሰሃራን ተባሂሎም ምስ ዝፍለጡ ዝምደብ እንትኾን ናይ እዚ ነገድ ቋንቋ ተናገርቲ ብፍላይ አብ ደቡብ ይርከቡ። ንአብነት፣ አኝዋክ፣ በርታ፣ ጉሙዝ፣ ማሳንጐ ኒዌር እዩም። ገ/ኪዳን (1988÷1)*
>
> *የ ኩናማ ብሔረሰብ ዘር ምንጭ ኒሎ ሰሀራ ተብለው ከሚታወቁ ነገዶች የሚመደብ ሲሆን የዚህ ነገድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ፡ በተለይ በደቡብ ይገኛሉ። ለአብነት፣ አኝዋክ፣ በርታ፣ ጉሙዝ፣ ማሳንጎ፣ ኑዌር ናቸው። ገ/ኪዳን፣ (1988÷1)*

በአጠቃላይ÷ አንዳንድ የብሄረሰቡ ተወላጆች እና በብሄረሰቡ ጥንተ አመጣጥ ዙርያ የሚያትቱ ፅሑፎች፣ የኩናማ ብሔረሰብ አክሱም አካባቢ ይኖር ነበር ሆኖም ከንጉስ ባዜን[6] ሞት በኋላ በአካባቢው [አክሱም] በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት መበታተን መጀመሩንና ከብሔረሰቡ አንዱ ክፍል[7] ተገንጥሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ በማምራት ከሌላ ነገድ/ ዘር ወይ ብሔረሰብ ተቀላቅሎ ተውጠ እንደቀረና፤ የተቀረው ክፍል ደግሞ ፡ በጊዜው በነበሩት ጦርነቶች ተሸንፎ ቀስ በቀስ እየሸሸ በሰዓቱ ጠላት[8] ወደማያይበት አሁን ወዳለበት የትግራይ ምስራቃዊ ክፍል ተንቀሳቅሶ መኖር መጀመሩን ይገልፃሉ። በመሆኑም የኩናማ ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ ከፍ ሲል የተጠቀሱት አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ከአክሱም እና አካባቢው እንደሆነ ለመገመት ያስችላል። የበለጠና ጥሩ የታሪክ ጥናት ተካሂዶ የዚህን ብሄረሰብ ጥንተ አመጣጥ የሚገልፅ እስኪገኝ ድረስ የኩናማ ብሄረሰብ ከአክሱምና አካባቢው በመፍለስ አሁን ወዳለበት አካባቢ ሊመጣ የቻለ ብሔረሰብ ነው።

---

[6] እንደ ኒቆዲሞስ አባባል፤ የንጉስ ባዜን ለሕልፈተ ሕይወት መብቃት ምክንያት ነው ተብሎ በአፈታሪክ የሚነገረው "ጠላቶች በሚጠጣው ጠላ ላይ መርዝ አድርገው ሰጥተውት ነው" ተብሎ እንደሚታመን አስቀምጧል።

[7] የትኛው ክፍል እንደሆነ በግልፅ የተቀመጠ ወይም የተነገረ ነገር የለም።

[8] በዛን ጊዜ ለብሔረሰቡ ጠላት ማለት ሐበሻ ሁሉ እንደሆነ የብሄረሰቡ አባላት ይናገራሉ።

2.1.2. ስያሜ

የብሔረሰቡ ዋነኛና ህጋዊ መጠሪያ ስም ኩናማ የሚል ነው። ለመሆኑ ኩናማ የሚለው የብሔረሰቡ መጠሪያ ከየት መጣ? እንዴትስ መጠሪያቸው ሆኖ ሊያገለግል ቻለ? ትርጉሙስ ምንድነው? ብሔረሰቡ የሚጠራባቸው ሌሎች ስያሜዎችስ አሉ? ለሚሉ ጥያቄዎች ከብሔረሰቡ ተወላጆችና ከአንዳንድ የተጻፉ "ጥራዞች"[9]፣ መጽሔቶች እና ጋዜጠኞች የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል። አቶ ሃይለ ወለላ እንደሚከተለው ሲሉ ነግረውኛል።

> "ኩናማ" የማንም [ምንም ነገር] አይፈልግም ፣ የራሱ እምነት ብቻ ይዞ የሚኖር ሕዝብ ነው። መጥፎም አያስብም። ኩናማ የሚለው ስያሜም ከዚሁ ከባህሪው ጋር በተያያዘ የመጣ ነው። በአጭሩ ንጹሕ፣ ምንም ተንኮል የሌለው ሕዝብ ማለት ነው ሲሉ (ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ገፅ 23-24) ገልፀውልኛል።

ኒቆዲሞስ፥ (1980፡8) ስለ ብሔረሰቡ መጠሪያ አመጣጥ ሲገልፅ፥ ኩናሞች አክሱም ነበሩ፤ በጦርነት ምክንያት አያቶቻቸው አገሩን ለቀው አሁን ወዳሉበት[10] እንደመጡና "ኩናማ" የሚለውን ስምም ከአያታቸው ከንግስት "ኩናሜ" እንደወሰዱ ያምናሉ ብሏል። ቆርኔልዎስ፥ (1980፡8) ደግሞ "ኩናሞች" በዝምድና ሐረግ የተነሳ በእናት አያታቸው "ኩናሚ" ስም ይጠራሉ የሚል ግምት አለ ሲል ጽፏል።[11]

እንደ አድያቦና፥ (2001፡28) አገላለጽ ደግሞ፥ ኩናማ የሚለው ቃል በቀጥታ በብሔረሰቡ ቋንቋ (ኩናምኛ) ሲተረጎም፤ ከትርጉሙ አልፎ ስለ ስያሜው አመጣጥም ሊያሳይ እንደሚችል አስቀምጧል።

---

[9] ጥራዞች የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ስራዎች ህትመት ላይ ያልዋሉ የአቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ፣ የአቶ ገብረኪዳንና የአቶ ቀርኔሊዎስ ዑስማን ስራዎች ናቸው።

[10] ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ

[11] ሆኖም እንደ አሌክሳንደር ናቲ አባባል ኩናማ ብሄረሰብ ለሴት ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ ስለሆነ ስያሜያቸው እንዴት በንግስቲቱ ሊጠሩ ይችላሉ ሲል ይሞግታል። አንዳንድ ያነጋገርኳቸው የብሄረሰቡ አባላትም ቢሆኑ ይህንን የአሌክሳንደር ናቲ ሃሳብ የሚያስረግጡ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

ኩናማ ዝብል ትርጉም ቅድም ክብል ምስ ናይ ደገን ውሸጥን ከም ጥልያን እንግሊዝ ከምአ ኤውን ምስ ኤርትራ ተታሒዙ ምስ ሊባን ሐማሴን፣ አብዝገብሮም ዝነበረ ኩናት አብ ሐደ ረጊእኻ ናይ ምቅማጥ ዕድል ካብ ምስአን ዝተልዓለ ብዙሓት ሕልክላኻት እናሓለፈን እናሰገረን ዝመፀ ምስ ምኳኑ ተታሒዙ ናይ ባዕሉ ታሪካዊ ስያመ ከም ዘለዎ ይፍለጥ። ነዚ እውን እዩ ኩናማ ማለት "ዘወር ምበልኩካ ምሓሽ" ዝብል ትርጉም ዘለዎ ...(2001÷28)

ኩናማ የሚል [ቃል] ትርጉሙ÷ ቀደም ሲል ከውጭና ከውስጥ እንደ ጣልያን እንግሊዝ እንዲሁም ከኤርትራ ጋር ተያይዞ ከሊበን፣ ሐማሴን ጋር ሲያደርገው የነበረው ጦርነት [ምክንያት] በአንድ ቦታ ተረጋግቶ የመቀመጥ ዕድል ከማጣቱ የተነሳ በርካታ መሰናክሎች እያለፈ የመጣ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ የራሱ ታሪካዊ ስያሜ እንዳለው ይታወቃል። ይኸው ስያሜውም " ኩናማ" የሚል ሲሆን ትርጉሙ ደግሞ "ዘወር ምበልኩ ምሓሽ" (ዞር ብል ይሻላል) የሚል [ነው።] (2001÷28)

በተጨማሪም÷ ብርሃነ ሃይለስላሴ (መስከረም 15፣2003÷ ገፅ 96) እና ቆርኔሊዎስ÷ (1980፡ 8-9) ፣ ኩናማ የሚለው ቃል በቀጥታ ሲታይ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች የያዘ የጥምር ሆሄዎች ውህደት ሲሆን "ኩ" የሚለው "ኩዳ" (ዞር ማለት ከመንገድ) ከሚል የመነጨ ሲሆን "ናማ" የሚባለው ደግሞ "አልኩ እኮ" ማለት ነው። ሁለቱ በጥምረት "ኩናማ" ተብሎ ሲጠራ "ዞር አልኩ እኮ" የሚል ትርጉም እንደሚሰጥ ይገልፃሉ።

ኩናማ ብሔረሰብ የሚጠራባቸው ሆኖም ብሔረሰቡ የሚያወግዛቸውና የማይቀበላቸው ሌሎች መጠሪያዎችም እንዳሉት አንዳንድ ፀሐፍት ይጠቁማሉ። ከነዚህ "የኩናማ ብሔረሰብ በሱዳኖች "ባዛ"፣ በኒዓሚሮች ባዚን ወይም /ባዳን/፣ በናራ ብሔረሰቦች ደግሞ "ዲላ" ተብለው እንደሚጠሩ ቆርኔሊዎስ÷ (1980:9) ሲገልጽ ፣ እነ ጀምስ ብሩስና ሄንሪ ሶልት የተባሉ ሁለት እንግሊዛውያን ደግሞ የኩናማ ብሔረሰብን በጐበኙ ጊዜ "ሻንቅላ" (የተከዜ ሻንቅሎች) ብለው እንደሰየሙዋቸው ኒቆዲሞስ÷ (1973: XXI) ይገልጻል።

ሆኖም÷ የኩናማ ብሔረሰብ አባሎች ከፍ ሲሉ የተጠቀሱትን መጠሪያዎች ፍጹም የማይቀበሉና የማይፈቅዷቸው ሲሆኑ ዋነኛ የማጭት አነሳሽ ምክንያቶች ተደርገው እንደሚወሰዱ ሃይለ ወለላና ካሽኪ ዑመር ነግረውኛል። ስለሆነም ብሔረሰቡ "ኩናማ" ተብሎ መጠራት እንደሚፈቅድና እንደሚፈልግ ገልፀውልኛል። በተጨማሪምኒቆዲሞስ÷ (1973: XXI) "ያም ሆነ ይህ ብሔረሰቡ እንዲጠራበት የመረጠው ሕጋዊ ስሙ ‹ኩናማ› ነው።" ብሎ ሲያስቀምጥ፤ ቆርኔልዎስ÷ (1980:9) " ብሔረሰቡ ሕጋዊና ትክክለኛ አጠራር ነው ብሎ የተቀበለው ኩናማን ነው ሲል አስፍሯል።

2.2 መልክዓ ምድር፣ የአየር ንብረትና ስነሕዝብ

የኩናማ ብሔረሰብ በአገራችን ኢትዮጵያ ከሚገኙ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች አንዱ ነው። ይህ ብሔረሰብ ከአዲስ አበባ በስተሰሜንና ሰሜን ምዕራብ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ "በታሕታይ አድያቦ" ወረዳ ይገኛል። (ቆርኔሊዎስ÷ 1980:7) ኩናማ ብሔረሰብ አሁን ወዳለበት ቦታ ሊመጣ የቻለው በጊዜው (*ገዜው መቼ እንደሆነ በውል አይታወቅም*) ከነበረው ጦርነት ለመሸሽ ሲል የተከዜን ወንዝ ተከትሎ እንደሆነና እዚሁ ቦታም ተረጋግቶ መኖር እንደጀመረ ይገልጻሉ።[12]

ብሔረሰቡ የሚገኝበት ወረዳ ታሕታይ አድያቦ 353.655 ሄክታር የቆዳ ስፋት ያለው ሆኖ 18 ቀበሌዎችንና 65 ጐጦችን ያቀፈ ነው። ከዚሁ የቆዳ ስፋት 25% በደን የተሸፈነ ሲሆን ቀሪው 75% በረሀማ ነው። በተጨማሪም÷ የኩናማ ብሔረሰብ የሚገኝበት ትክክለኛ ቦታ በ 36^0 40` እና $30^0$ 55` ምስራቅ ሎንግቲዩድ (longitude)፤ በ14^0 15^0 እና 15^0 20` ሰሜን ላቲቲዩድ (Latitude)" እንደሆነ (Nikodimos, 1987:13) አስቀምጧል።

---

[12] የዚሁ ብሔረሰብ ሌላው ክፍልና በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ በኤርትራ /ባሬንቱ፣ ተሰነይ፣ ተኸምብያ፣ ቃሓውታ ... ተበታትኖ እንደሚኖር ገብረሀዋርያት (1978÷10) አስቀምጧል።

ካርታ፡- 1፣ የታሕታይ አድያቦ ወረዳ ካርታ



- በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የኩናማ ብሄረሰብ የሚገኙበት የወረዳ ታሕታይ አድያቦ ካርታና የአካባቢ መግለጫ፡- ምንጭ አድያቦና መፅሔት

በዚህ ወረዳ የኩናማ ብሔረሰብ በአብዛኛው ተራርቀው በሚገኙ በለምለም (ገዛመቀር፣ ገዛ አዱራ ፣ መዳበ፣ ዕርዲ ወያነ ፣ ሽምኒ) ፣ መንጠብጠብ፣ ፣አደመይቲ ተብለው በሚጠሩ ቀበሌዎች ይኖራል። በተጨማሪም በሽምብሊና (ዓዲጐሹ፣ ዓዲባይ እና ሕሌት ካሳ) በተባሉ

ቦታዎች እንደሚገኙ Nikodimos (1987:13) አስፍረዋል። እንዲሁም አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ[13] ነግረውኛል።

እንደ የወረዳው የመንግስትና ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ እና የኩናማ ብሔረሰብ ተወካይ አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ ገለጻ፥ የኩናማ ብሔረሰብ የሕዝብ ብዛት 6,700 ይገመታል። "በታሕታይ አድያቦ" ጣብያ ለምለም 3010፣ ዓደባይ 3000 እና በተለያዩ የትግራይ፣ የኢትዮጵያ ከተሞች በተለይ ደግሞ ከትግርኛ ተናጋሪው ጋር ተቀላቅለው የሚገኙት 600 የሚሆኑ ናቸው።

2.3 ጎሳ

ኩናማ ÷ በአራት ጐሳዎች የተከፋፈለ ነው። እነሱም፥ ሽዋ፣ ካለዋ፣ ሴማ፣ ጉማ ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ጐሳዎች ሽዋ÷ የጎተራ ጐሳ፤ ካለዋ "የምልያ" (የዉበት) ጐሳ፣ ጉማ የወንዝ ጐሳ፣ ሴማ ደግሞ የንብ ጐሳ እንደሚባሉ Alexander (1982፡ 7) እና Cittadini (1966/7፡1) አስቀምጠዋል። የኩናማ ብሔረሰብ አራት ልዩ ልዩ ጐሳዎች ያሉት ቢሆንም የጐሳ ክፍፍሉ መቼ? ከየት፣ እና እንዴት? ሊመጣ እንደቻለ የብሔረሰቡ ተወላጆችም ሆኑ ሌሎች የተጻፉ መረጃዎች የተናገሩት ነገር የለም። የብሔረሰቡ ተወላጆችም ቢሆኑ "በቃ ይህ ከወላጆቻችን የወረስነው ነው" የሚል መልስ ከመስጠት ወጪ ያስቀመጡት የለም።

እነዚህ ጐሳዎች በመልክ መጠነኛ የሆነ ልዩነት ቢኖራቸውም ከብሔረሰቡ ተወላጆች ውጪ የሆነ ማንም ሰው ሊለያቸው አይችልም። እንዲሁም በሚጠቀሙበት ቋንቋ ይሁን በሚገለገሉበት ቁሳዊ ባህል፣ ልማዳዊ እምነት ወዘተ. ተመሳሳይ ሲሆኑ መጠነኛ የሆነ ልዩነት ይታይባቸዋል። ከሚለያዩባቸው ነገሮች ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ÷ የቤት አሰራር፣ የፀጉር አሰራር እንደሁም የማጋጌጫ ንጥረ ነገሮች በዋናነት የሚነሱ ናቸው። ከነዚህ ልዩነቶች መካከል የቤት አሰራር ልዩነታቸውን ዘርዘር አድርገን በማየት የብሔረሰቡን የአስተሳሰብ አድማስ እንቃኝ፡

አራቱ ጐሳዎች አንድ አይነት የቤት አሰራር አላቸው። ገ/ኪዳን (1988፡4) እንደሚለውና እኔም በምልከታዬ እንዳረጋገጥኩት፤ አራቱ የቤት አሰራሮች ከታች ከመሰረቱ እስከ ፍጻሜው ድረስ

[13] አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ የብሄረሰቡ ተወካይና የተወካዮች ምክርቤት አባል ናቸው።

በተመሳሳይ እንጨትና ሳር የተሰሩ ናቸው። ልዩነቱ የሚታየው በቤቱ አናት ላይ በሚቀመጡ ጉልላት መሰል ምልክቶች ነው።

የካለዋ ጎሳ የቤት መለያ ምልክት



የሸዋ ጎሳ የቤት መለያ ምልክት



የጉማ ጎሳ የቤት መለያ ምልክት



የሴማ ጎሳ የቤት መለያ ምልክት



- የኩናማ ብሄረሰብ የጎሳ መለያ የቤት ምልክት[14]

[14] አራቱንም ቤቶች በቦታው ተገኝቼ ፎቶግራፍ ያነሳሁት እኔ ነኝ።

በቤት አናት ላይ የሚቀመጠውን ምልክት ለተለያዩ ጉዳዮች ይጠቀሙበታል። የብሔረሰቡ አባል ሆኖ ከሩቅ አካባቢ ተነስቶ የኩናማ ብሔረሰብ አባላት ወደሚገኙበት አካባቢ ሲሄድ ሰው መጠየቅና ዘመድ አዝማዱን ማፈላለግ አይጠበቅበትም። በደረሰበት መንደር ባሉት ቤቶች አናት ላይ የተቀመጠውን ምልክት በማየትና ከራሱ የቤት አሰራር ጋር በሕሊናው በማስተያየት ከእርሱ ጋር እሚመሳሰለው ቤት ዘው ብሎ መግባት ብቻ ነው። የገባበት ቤት አባሎችም ያለምንም ማመንታት የራሳቸው ጐሳ አባል እንደሆነ አምነው እንግዳቸው መሆኑን ተቀብለው አስፈላጊውን ነገር ያሟሉለታል።[15]

በተጨማሪ፣ አራቱም ጐሳዎች በከብት ጠባቂ ልጆቻቸው ፀጉር ላይ በቤታቸው አናት ላይ የሚቀመጠውን ምልክት በሚያሳይ መልኩ ላጭተው ወደ በረሀ እንደሚልኩ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፡ 2002 ፥ 36) ገልፀውልኛል። ሽዋ የሆነ ከብት ጠባቂ /እረኛ/ የሽዋ የቤት ምልክት ተላጭቶ ይሄዳል። የሴማ፣ ከለዋ፣ ጉማ እንደዚሁ የየራሳቸውን ጐሳ የቤት አሰራር በሚያሳይ መልኩ ተላጭተው ወደ በረሀ ይሄዳሉ።[16] በሄዱበት አካባቢ ራብ፣ ጥማት፣ ሌላም ሌላም ችግር ቢደርስ በአካባቢው የሚኖሩም ይሁኑ እግር ጥሏቸው የመጡ የብሔረሰቡ አባላት ችግር በደረሰባቸው እረኞች ፀጉር ላይ ያለውን ምልክት በማየት የራሳቸውን ጐሳ (ዘመድ) ይለዩና እረኞቹን ከገጠማቸው ችግር ሊታደጉ ፣ ከለላም ሊሆኑላቸው ይችላሉ ተብሎ ይታመናል።

ምልክቶች አንዱን ጎሳ ከአንዱ ጎሳ ለመለየት ከማገልገላቸው ውጪ ሌላ ትርጉም እንዳላቸውና በምልክቶቹ መጠቀም እንዴት እንደተጀመረ ለማወቅ፤ የብሔረሰቡን አባላት ጠይቂያቸው ነበር። ሆኖም ከዚህ የዘለለ ሌላ ፍቺ እንደሌላቸው፣ መቼና በምን መልኩ በምልክቶቹ መጠቀም እንደተጀመረም በውል እንደማያውቁ ነግረውኛል።

የእነዚህ አራት ጐሳዎች የጋብቻ ሁኔታ ሲታይ÷ ለጋብቻ የሚተጫጨት /የሚፈቃቀዱት/ የሽዋ ጐሳ ከካለዋ ጋር ብቻ ሲሆን÷ ሴማ ደግሞ ከጉማ ጋር ብቻ እንደሆነ Alexander (1982፡7) Cittadini (1966/7:1) አስቀምጠዋል። ከዚህ ውጪ በብሔረሰቡ እምነት መሰረት ሶስት ጉልቻ መመስረት ክልክል ነው። እንደምክንያት የሚያቀርቡትም÷ ሽዋና ሰማ፣ ካለዋ እና ጉማ የስጋ ዘመድ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው ይላሉ።

---

[15] ቀደም ባሉት ዘመናት ሚስታቸውን እስከ መጋበዝ ድረስ አስፈላጊውን ነገር ያሟሉ እንደነበር ፅጌ (1995) ይገልፃል።

[16] እረኞቹ ወደ በረሀ የሚሄዱት ቢያንስ ለ6 ወርና ከዚያ በላይ ሊሆን እንደሚችል ይነገራል።

2.4. ኢኮኖሚ

ኩናማ ብሔረሰብ ቀደም ባሉ ዘመናት ዋነኛ መተዳደሪያው አደን እንዲሁም የበረሀ ፍራፍሬ መልቀም ነበር::[17] ለዚህም ያመቸው ዘንድ ነው የተከዜን /መረብ/ ወንዝ ተከትሎ የተቀመጠ ው:: በተጨማሪም አቶ ሃይለ ወለላ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል::

> ኩናማ ሕርሻ እንታይ ይፈልጦ[::] ንሱ በረኻ በረኻ ስለ ዝኾነ እታ አክሊሲ ብሓቂ እኽሊ ኾይና አይፈልጠን ነይሩ:: በረኻ በረኻ ስለዝኾነ ፍራምረ ዓየዶ፣ አጉልምዶ መቂዕ፣ ሳዳ፣ ምልዖ [ከምኡ ውን] ወድንቢ፣ ዓጋዘን፣ ሚዳቅ ቀቲልካ ምብላዕ ጥራሕ እዩ ዝፈልጥ ነይሩ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም ስክርብ ÷ ገፅ 7)::

> ኩናማ እርሻ ምን ያውቀዋል:: እሱ በረኻ በረኻ ስለሆነ እህሏን በእውነት እህል ሆና አያውቃትም ነበር:: በረኻ በረኻ ስለነበር ፍራፍሬ ዓየ፣ አጉልም መቂዕ፣ ሳዳ፣ ምልዖ[18] [እንዲሁም] ወድንቢ፣ ዓጋዘን፣ ሚዳቅ [አድነህ] ገድለህ መብላት ብቻ ነበር የሚያውቀው (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም ስክርብ ÷ ገፅ 25 እና 30)::

ብሔረሰቡ በዚህ መልክ ኑሮውን ሲገፋ÷ ወደ ዘር መዝራትና እርሻ መጀመር ሊያሸጋግሩት ከቻሉት ዋነኛው ምክንያት "የዝሆን ኩስ" እንደሆነና የሂደቱን ታሪክ ጨምረው አቶ ሃይለ ወለላ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል::

> ...ሓርማዝ ርሑቅ ቦታ እክሊ ረኽቡ ምስ በልዐ አብአ አብታ ሳዳ ዝኹዕቱላ ከባቢ ሐረኡ:: ድሕረኡ ከብቶም ሳዳ ዝኹዕቱ ሰባት እንታይ እዩ እዚ ፍሪኡ ኢሉ:: እዚአሳ ክንሪአ እስኪ ኢሎም ንዓአ አብ ማይ ዘቅዚቆም አኽሊ አውጺኦም:: ... ነዓ ዘውዕእዋ ፍረ ሕዲተይ ሕዲተይ ተማቂሎም ከይጠፍኦም አብ ነፀለኦም አሲሮም ናብ ዓዲ ተመሊሶም::

---

[17] የኩናማ ብሔረሰብ ያገኙትን ነባር ሁሉ ይበሉ እንደነበር ይሄውም መለያቸው እንደነበር መስፍን (1990፡18) ይገልፃል ::

[18] እነዚህ በኩናማ ብሔረሰብ አካባቢ የሚበቅሉ የፍራፍሬ ዓይነቶች ናቸው::

ስነ ምስኮነ ድማ ነቲ አክሊ አብ ጥቃ ገዝኦም ቢተንዎ። ዋእ እታ አክሊማ ሰብ ኾይና። ድሕረኡማ ስለስተ እናገበሩ ይዘብጥዋ። ምስ ዘጠ ቡ ድማ ነታ አክሊ ሸም አውፁኡላ "አቢንከፊ"[19] ኢሎም ሰይሞሙዋ። ... ድሕረኡ ብዕጨይቲ እናወግኡ ብሰብ ገይሮም እናሓረሱ ምዝራእ ጀሚሮም። ከምአ ከምአ እንዳበሉ ሰለስተ አርባዕተ ዓመት ምስ ፀንሑ "ዋእ እዚ ገዲፍና ደአ ንበረኻ ኾንኾይድ ኢሎም ማዕቢሎም ሓበሻ ካብ ቀይሕ ባህሪ ናብ ኤርትራ ምስመፀ ክልተ ገረውኛ ሰለስተ ገረውኛ ምሸላ እናሸጡ ብዕራይ ዓዲጎም ነዊት ነዲሎም ናብቲ ሐዚ እትርእዮ ዘለካ ማሕረስ አትዮም ይብለካ።[20]" (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 7-8)።

ዝሆን ሩቅ ቦታ እህል አግኝቶ ከበላ በኋላ እዛው ሳዳ የሚቆፉሩበት አካባቢ ኩሱን (ሰገራውን) ይጥላል። እዛ ቦታ ኩሱን ከጣለ ቦኋላ ሲቆፍሩ የነበሩት ሰዎች ምንድነው ይሄ ምን ዓይነት ፍሬ ነው ብለው ይህ እንኳን ማየት አለብን ብለው የዝሆኑን ኩስ ይዘው በውሃ በጠበጡት እህልም አወጡ። ያገኙዋትን ፍሬ ትንሽ ትንሽ ተካፍለው እንዳትጠፋባቸው በነጠላቸው ጫፍ አስረው በመያዝ ወደ ቤት ተመለሱ። ሰኔ ሲሆን ያገኙትን እህል በቤታቸው አጠገብ በተነ። ከዚያ [የተበተነችው እህል እህል ሆነች]። በኋላ እማ ሶስት ሶስት እያደረጉ ይወቁት ጀመር። ከወቁት በኋላ "አቢንከፊ" ብለው ስም አወጡለት ። ከዚያ በእንጨት በሰው እየጎተቱ መዝራት ጀመሩ። እንዲ በንዲህ መልኩ ሶስት አራት አመት ሲቆዩ "እንዴ እንዴት ይህን ትተን በራሃ ለበረሃ እንከራተታለን ብለው ሰልጥነው ከቀይ ባህር ወደ ኤርትራ ሀበሻ ሲመጣ ሁለት ሶስት ጣሳ ማሽላ እየሸጡ በሬ በመግዛት እና

[19] "አቢንከፊ" ማለት ከዝሆን ኩስ የተገኘ ማለት እንደሆነ የብሄረሰቡ አባላት ይናገራሉ።

[20] ይህ ወደ እርሻ የመሸጋገር ታሪካቸውና የዘር ማወቅ ታሪካቸው ኩናማ በአካባቢው /አሁን ባሉበት/ እስከ አሁን ለምን ቆዩ ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ይመስለኛል። ምክንያቱ <ይህን ትተን ለምን በረኻ በረኻ እንሂዳለን> አሉ የሚለው ሀሳብ ስለሚያስረግጥልን።

ሞፈር ቀንበር በማዘጋጀት አሁን ወደምታየው እርሻ ገቡ እልሃለሁ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም ስክርብ ÷ ገፅ 30-31)።

ብዚህ መልኩ መጣ የሚሉት የብሔረሰቡ የእርሻ ታሪክ÷ በአሁኑ ሰዓት በቀዳሚነት የሚጠቀሰው መተዳደሪያቸው ግብርና ሆኖ ይገኛል። ከብሔረሰቡ 90% የሚሆነው አባል በእርሻ ይተዳደራል አድያቦ (2002፡17) ገ/ሃወርያ (1978፡5)።

ኩናማ÷ ከዝሆን ኩስ ካገኘው የበቆሎ ዘር በተጨማሪ የተለያዩ የአስተራረስ ስልትና የአመራረት ስልቶችን በመጠቀም በርካታ የሰብል ዓይነቶች ያመርታል። ከነዚህም ውስጥ በቆሎ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ሰሊጥ፣ ዳጉሳ፣ አዳጉራ፣ ቡልቱግ[21] እና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው። ከነዚህ መካከል የብሔረሰቡ ዋና የገቢ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው "ሰሊጥ" ነው።

የኩናማ ብሔረሰብ የሚተዳደርባቸው ሌሎች የገቢ ምንጮች ከብት ማርባትና እደጥበብ ናቸው። ከብሔረሰቡ 10% የሚሆኑት አባላት በዚሁ ይተዳደራሉ። በአሁኑ ወቅትም ከብት፣ ፍየል፣ አህያ እንዲሁም በተወሰነ መልኩ በግ ብሔረሰቡ የሚያረቧቸው እንስሳት ናቸው። በእደ ጥበብ የሚተዳደሩትም ወንበር ÷ ማርገብገቢያ በአጠቃላይ የሰንበሌጥ ውጤቶችን በመስራትና በአቅራቢያቸው ወደሚገኘው ሽራሮ ከተማ ወስደው በመሸጥ ነው። የተወሰኑት የብሔረሰቡ አባላት ደግሞ በአቅራቢያቸው ባለው ከተማና በሚኖሩበት መንደር "ዳጋ" የተባለ የብሔረሰቡን ባህላዊ መጠጥ በመሸጥ ይተዳደራሉ።

[21] "ቡልቱግ" ፣ በብሄረሰቡ ብቻ የሚበቅል ባህላዊ ዘር ሆኖ በዋናነት ለምግብነት (እንጀራ፣) የሚያገለግል ነው።

2.5. አስተዳደር

2.4.1 ልማዳዊ አስተዳደር

ከፍ ሲል በገፅ 21 የተጠቀሱት አራቱ የብሔረሰቡ የጐማ አባላት ከጥንት ጀምሮ በልማዳዊ አስተዳደር ይተዳደሩ እንደነበር ይነገራል። ከጥንት ጀምሮ እያንዳንዱ ቤተዘመድ ራሱን የቻለ መሪ /ማንዳ/ እንደነበረው የብሔረሰቡ አባሎች እና ሌሎች የታሪክ ፀሐፍት ጠቅሰዋል። የብሔረሰቡ አባላት ከሆኑት ውስጥ ሃይለ ወለላ፥ *"ኩናማ ካብ ቀደም አትሒዙ ንንዳ ፖሊስ ንንዳ ዳኛ ብፍፁም አይክይድጅ። አብ ዓዱ ብዘለው መመሓደርቱ ገይሩ እዩ ፀገሙ ዝፈትሕ።"* [ኩናማ ከጥንት ጀምሮ ችግር ሲገጥመው ወደ ፖሊስ፣ ዳኛ በፍጹም አይሄድም። አገሩ ውስጥ ባሉ አስተዳዳሪዎች ይዳኛል እንጂ።"] ብለው ሸራሮ፣ ከመቅረፀ ድምፅ ውጪ ነግረውኛል። በተጨማሪም ወይዘሮ አስቴር "እዚ ብሔረሰብ እዚ ብፍፁም ናብ እንዳ ሕጊ መፅዩ አይፈልጥን'' ["የዚህ ብሄረሰብ ተወላጆች በፍፁም ወደ ሕግ ቦታ መጥተው አያውቁም"] (ወ/ሮ አስቴር የወረዳ ታሕታይ አድያቦ አቃቤ ሕግ)[22] ሲሉ ስለ ብሔረሰቡ ልማዳዊ አስተዳደር ወዳድነትና ፅናት እንዲሁም ጥንታዊነት ይገልጻሉ።

ማህበራዊ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግለሰቦች ሕዝቡን መምራትና ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል። ከላይ ከተጠቀሱት የብሄረሰቡ ጉሳዎች በአስተዋይነቱ፣ በብልህነቱና በችሎታው እንዲሁም በብሔረሰቡ ባህላዊ መድኃኒት አዋቂነት[23] ብቃት ተረጋግጦ ለመሪነት ይመረጣል።

ከጥንት ጀምሮ የሕብረተሰቡ አመራር አካሎች ያካባቢው ሽማግሌዎች ሲሆኑ ግብጻውያን ሲገቡም ሆነ ኢጣልያኖች ሲገቡ አዲስ ዘመናዊ የአስተዳደር መዋቅር በማምጣት ሕዝቡ እንዲቀበለው ተደርጓል። የጣልያን መንግስት የግብጻውያንን ፈለግ በመከተል ገገርና ተገዢ ያለበት አካባቢ እንዲሆን ሞክረዋል። ስለዚህ ጉዳይ Alexander (1982፡8) እንዲህ ሲል ጽፏል። *"After the appointment of Totic as a chieftainship. Italians appointed a*

---

[22] ከወይዘሮ አስቴር ጋር የተነጋገርኩት በአጋጣሚ ወደ ወረዳው ስንገሠ አውቶቡስ ውስጥ ተገናኝተን ስለሆነ ከመቅረፀ ድምፅ ውጪ ነው። በኋላ ግን በስርዓት ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ስነግራቸው ሳይመቻቸው ቀርቷል።

[23] የባህላዊ መድሀኒት ማወቀ ብቃት የሚፈለገው ለተጣሉ በማስታረቅ ሂደት ላይ ለሚፈጸሙ ሂደቶች የሚፈጸሙ ልማዶችን በብቃት ለመወጣት ያስችለው ዘንድ ነው። የሂደቶቹ ዝርዝር በምዕራፍ አራት ቀርበዋል።

2.4.2.2. "ሳንጋኔና"

"ሳንጋኔና" የነፍስ ወይ የደም ወንጀል አስታራቂዎች በመባል ይታወቃሉ። የነፍስ ግድያን በሚመለከት ከ "ሳንጋኔና" በስተቀር በብሔረሰቡ እምነት መሰረት ማንም ሰው ሕጋዊና ዘላቂ ዕርቅ ሊሰጥ አይችልም ተብሎ ይታመናል። ኩናማ፥ በአስታራቂዎቹ ላይ ካለው ከፍተኛ እምነት የተነሳ "ሳንጋኔና" ያስታራቀውን ማንም ሊሽረውና ሊለውጠው አይችልም። እርቁን የሻረ ወይም የጣሰ፤ ማለትም ከዕርቅ በኋላ ደም ለመመለስ ዱላ ያነሳ፣ ድንጋይ የወረወረ፣ ብረት ያቀና፣ ቢላ የሳለ ሁሉ፤ ዱላ ያነሳበት፥ ድንጋይ የወረወረበት ብረት ያቀናበት፥ እና ቢላ የሳለበት እጁ ይሰበራል ከሚል ከፍተኛ እምነት የመነጨ ነው። ሁለተኛውና ከፍተኛው ቅጣት ደግሞ ዘሩ ሁሉ ይጠፋል ተብሎ ስለሚታመን የሚያሳድረው ፍርሃት ነው። ስለሆነም በነዚህ የግድያ አስታራቂዎች የታረቁ የደም ወንጀለኞችና ደም ተበቃዮች በእርቁ ተስማምተውና አምነው በሰላም ይኖራሉ።

ከብሔረሰቡ ልማዳዊ አስተዳደሮች ውስጥ የልማዳዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ሂደት በጣም ረዥምና አድካሚ ነው። ሆኖም ግን በማያዳግም ሁኔታ ዘላቂ የሆነ ዕርቅና ስምምነት ላይ ያደርሳል። የዕርቁ ሂደት እንዴት እንደሆነ ትኩረት ያደረግኩበት ርዕሰ ጉዳይ ስለሆነ በምዕራፍ አራት ሰፋ ባለ መልኩ ይቀርባል።

2.4.2 ዘመናዊ አስተዳደር

የኩናማ ብሔረሰብ ልማዳዊ አስተዳደር እንዳለ ሆኖ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ በሕገ መንግስቱ መሠረት ከታች ከቀበሌ እስከ ፌደራል ተዋቅሮ በመረጣቸው አስተዳዳሪዎች ይተዳደራል። በ"ጣቢያ" ደረጃ 13 ካቢኔ ፣ 200 የምክርቤት አባላት ሲኖሩት በወረዳ ደረጃ 3 የምክር ቤት አባላት፤ በክልል ደረጃ 4 የምክርቤት አባላት፣ 2 ወንዶች እና 2 ሴቶች አሉት። በፌዴራል ደረጃም 1 የምክር ቤት እና 1 የፌዴሬሽን ምክር ቤት ተወካዮች አሉት። በተጨማሪም ብሔረሰቡ ማህበራዊ ፍርድቤትና በመልካም አስተዳደር ማዕከል ያደረገ ችግሮቹን የሚፈታበት ደረጃ ላይ ይገኛል። (የመንግስትና ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊና የብሔረሰቡ ተወካይ አይተ ብርሃነ ሃይለስላሴ መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም፣ ሽራሮ)

2.5 ቋንቋና እምነት

2.5.1 ቋንቋ

የኩናማ ብሔረሰብ መግባቢያ ቋንቋ ኩናምኛ በመባል ይታወቃል። ኩናምኛ ቋንቋ ኒሎ ሰሃራዊ ተብለው ከሚታወቁ ዓበይት የቋንቋ ዘርፎች አንዱ እንደሆነ ብዙ ተመራማሪዎች Bender, (1976:40) ; Alexander (1982:1); Alem (1982:32); Nikodimos (1987:17) እና አድያቦና (2001:28) ገልጸዋል። ከ ኩናምኛ በተጨማሪ በአዋሳኙ በሚገኙት በዋናነት በትግርኛ ቋንቋ እንደሁም በተወሰነ መልኩ በአማርኛ ቋንቋ ለመግባብያነት ይገለገላል።

የኩናማ ሕዝብ ቀደም ባሉ ዘመናት ራሱን በራሱ ያስተዳድር ነበር። ስለሆነም የዛሬይቱ የጐረቤት አገር ኤርትራ በዘመኑ በነበሩ የሃይማኖት ሰባኪዎች (ሰባክያነ ወንጌል) አማካኝነት ቋንቋው ተስፋፍቶ እና አድጎ ነበር። ሆኖም÷ በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ እንደ ከብሔረሰቡ ተወላጆች የተማረ ሰው መጥፋትና በቋንቋው ፊደል ቀርጾ ወደ ጽሑፍ የመቀየር ግንዛቤ እጥረት፣ እንዲሁም ባለፉት ዘመናት የነበረው ስርዓት ለብሔረሰቡ ትኩረት ባለመሰጠቱና ሌሎች ችግሮች ተደማምረው ቋንቋው በኢትዮጵያ የሚስፋፋበት፣ የሚያድግበት ዕድል ሳይፈጠር ቆይቷል አድያቦና (2002:29)። በተወሰነ መልኩ ግን ጥቂት የብሔረሰቡ አባለት የመማር ዕድል ገጥሟቸው ነበር። ስለሆነም በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የተማሩ የብሔረሰቡ አባላት ብርታትና ጥንካሬ የብሔረሰቡ ተወላጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚማሩበትን መንገድ በመክፈት ላይ ይገኛሉ። ወጣቶች ከ1-8 ክፍል እንዲማሩ ትምህርት ቤት ተገንብቶ፣ በቋንቋው መጽሐፍ ተዘጋጅቶ መስከረም 19፣ 2003 ዓ.ም በይፋ ሲመረቅ በዓሉ ላይ ተገኝቼ ነበር።

በተጨማሪም ብሔረሰቡ በተወላጆቹ ጥረትና ብርታት እንዲሁም በራሱ ዓመታዊ በጀት ተጠቅሞ ባህሉንና ታሪኩን ከትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር የሚያስችል ሙዝየም ጥቅምት 2፣ 2001 ዓ.ም አስመርቋል። በሙዝየሙ የብሔረሰቡ ጥንታዊና ባህላዊ ማጋጌጫዎች፣ የእርሻ፣ የአደን መሳሪያዎች እንዲሁም የቀደምት የብሔረሰቡ አባላት የጦር መሳሪያዎች፣ የቤት እቃዎችና ሌሎች ልዩ ልዩ ጥንታዊ ቁሳቁሶች ይገኛሉ።

2.5.2 እምነት

ቀደም ባሉት ዘመናት ኩናማና እምነት ሲነሳ አብዛኛው የብሔረሰቡ አባሎች የባህል እምነት ተከታዮች እንደነበሩ የብሔረሰቡ ተወላጆችና በብሔረሰቡ ጥናት ያደረጉ ፀሐፍት ይገልጻሉ። ከነዚህም ኒቆዲሞስ (1973:11) "በመሰረቱ ኩናሞች ባህላዊ ኃይማኖት ተከታዮች ናቸው።" ሲል ቆርኔሊዎስ (1980:29) ሕዝቡ በባህላዊ እምነቱ ሰማይና ምድርን የፈጠረ ረቂቅ ኃይል መኖሩን አውቆ "አና" ብሎ ከማመኑና ከማምለኩ በስተቀር በዚህ ረቂቅ ኃይል ላይ ያለው አመለካከትና አስተሳሰብ ግልጽ የሆነ አይደለም። በተጨማሪም በጀግንነቱና በታማኝነቱ የታወቀና የተደነቀ "ደንጉል" በሚባል ሰው ስም ማታ ሲተኙም ሆነ ጠዋት ሲነሱ ከእግዚአብሔር "አና" በታች "ደንጉል" ይጠብቀን ይላሉ ሲል አስፍሯል።[25]

ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ልዩ ልዩ ሰባክያነ ወንጌል (Missionaries) ብሔረሰቡ ወደሚገኝበት አካባቢ በመግባት የክርስትና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውን አስፍረዋል ኒቆዲሞስ (1973:XIII)፤ Nkodimos (1987:20); Alexander (1982:15)። ሆኖም÷ የገቡት ሰባክያነ ወንጌል የተሳካ ስራ አልሰሩም። አድያቦና (2001:28) ቄስ ገብረ ሕይወት ወ/ገብርኤልን በመጥቀስ ባቀረበው ፅሑፍና በአቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ (መስከረም 15፣ 2003÷ ስክርብ ገፅ 89) አገላለፅ መሠረት፣ የኩናማ ብሔረሰብ የክርስትና (ኦርቶዶክስ) ሃይማኖት የተቀበለው በ 1942 ዓ.ም የትግራይ ክፍለሃገር ሊቃነ ጳጳስ በነበሩት በአቡነ ዮሐንስ አስተዳዳሪነት ይንቀሳቀሱ በነበሩት በአባ ማህተመ ስላሴ አጥማቂነት ነው።

ስለሆነም÷ በአሁኑ ሰዓት በትግራይ አካባቢ የሚኖሩ ኩናማዎች ባህላዊ እምነቶቻቸውና መድኃኒቶቻቸው[26] ውስጥ ለውስጥ እየተገለገሉ ከ1942 ዓ.ም ወዲህ ሙሉ በሙሉ የኦርቶዶክስ

---

[25] ስለዚህ ጉዳይ አውራ የመረጃ አቀባዮቼ በጠየኩዋቸው ጊዜ በአሁኑ ሰዓት በተለይም ከ1942 ዓ.ም ወዲህ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች እንደሆኑ እንጂ ቀደም ሲል ስለነበረው እምነታቸው ሊነግሩኝ አልፈለጉም።

[26] ኩናማ ብሔረሰብ በባህላዊ መድኃኒቶች የታወቁ እንደሆኑ አጐራባች የሆኑ የትግርኛ ተናጋሪ ሰዎች ይናገራሉ። ከነዚህ ውስጥ በዋናነት የሚታወቁበት ባህላዊ መድኃኒት "የእባብ" መድኃኒት ነው። ቀጥሎም ለባህላዊ የዕርቅ ስርዓታቸው ማስረገጫ የሚሰጡት ባህላዊ መድኃኒት ዕውቀት ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጠዋል።

ተዋህዶ እምነት[27] ተከታይ መሆናቸው የብሔረሰቡ ተወላጅና የሰበካ ጉባዔ አስተባባሪ የሆኑት አቶ ሃይለ ወለላ ነግረውኛል::

2.6 ልደትና ስያሜ

በሀገራችን ኢትዮጵያ ባሉት በርካታ ብሔረሰቦች (ethnic groups) የወንድ ወይም የሴት ልጅ መወለድ የተለየ ትርጉምና ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል:: ይኸውም ከበርካታ ብሔረሰቦቹ ውስጥ እኔ በማውቀው በትግርኛ፤ እና በአማርኛ ከሚባሉት አባባሎች ውስጥ ወንዱም ሴቱም "ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ወለድሽ? ወይ ወለድክ" የሚል የኩራት ድምፀት የተሞላበት ሐረግ ሲናገሩ መስማት የተለመደ ነው:: በተጨማሪም÷ ወንድ ልጅ ሲወለድ ሰባት ጊዜ ዕልል መባሉ፣ ሴት ልጅ ስትወለድ ሦስት ጊዜ ብቻ መባሉ ራሱ ልዩነቱን ሳያንፀባርቅ አይቀርም:: በኩናማ ብሔረሰብ ግን የሚወለደው ህጻን ወንድ ይሁን ሴት የተለየ ትርጉም ወይ የተለየ አስተያየት የላቸውም:: ወንድ ሲሆን አባትየውን ይረዳል÷ ሴት ስትሆን ደግሞ እናትየዋን ትረዳለች የሚል እምነት ከመኖር ውጪ ከፍ እና ዝቅ አድርጐ የመመልከት ሀሳብ በኩናሞች ባህልና ልማድ አይታወቅም ኒቆዲሞስ (1973 ፡28)::

ኩናማዎች ልዩና እጅግ በጣም አስገራሚ የስም አወጣጥ (አሰያየም) ስርዓት እንዳላቸውም ይነገራል:: ለልጆቻቸው ከልደት እስከ አቅመ አዳምና ሄዋን ድረስ በርካታ ስም ያወጡላቸዋል:: አንድ የብሔረሰቡ አባል ስመ ብዙ ነው:: እስከ 25 (ሃያ አምስት) የሚደርሱ ስሞች ሊኖሩት ይችላሉ:: ከ 25ቱ ስሞች ውስጥ ታዋቂነት ያለውና የተለመደ ስም (ኡዳኪዳ) ይኖረዋል:: የተቀሩት ስሞች ደግሞ ለፍቅር፣ ለወዳጅነትና ለክብር ተብሎ የሚሰጠው ስም (አሉዳ ወይም ፋኪዳ ይባላል) ይኖራቸዋል:: "አሉዳ ፋኪዳ" በብዛት የሚጠቀሙት ብዙ ጊዜ ሳይገናኙ ከቆዩ የናፍቆታቸውና የፍቅራቸው መግለጫ፣ እንዲሁም በሁለት ፍቅረኞች መካከል ፍቅራቸውን የሚገልጹበትና ለአንድ ትልቅ ሰው ክብር ሲባል የሚጠራ ስም ነው ኒቆዲሞስ (1973፡28)::

---

[27] እንደ አንዳንድ የብሔረሰቡ አባላት አባባል የክርስትና እምነት መቀበላቸውን በሁለት መልኩ ይመለከቱታል:: አንድም ከጠቃሚነቱ አንድም ከጎጂነቱ:: ጠቃሚነቱ ከሰው ጋር እኩል እንዲሆኑና በአንድ አካባቢ ረግተው እንዲኖሩ እንዲሁም ሚስት ከባሏ ውጪ፤ ባል ከሚስቱ ውጪ እንዲሄድ የማይፈቅድ መሆኑ ነው:: በተቃራኒው ለመራብና ለመጠማት ምክንያት አድርገው ይወስዱታል:: ምክንያቱ ከሃይማኖቱ በፊት ይህን ብላ ይህን አትብላ፣ ይህን ቀን ስራ ይህን ቀን አትስራ የሚል ገደብ አልነበራቸውምና:: በተጨማሪም በሴት ተጋጭቶ የማያውቀውን ህዝብ ከሃይማኖቱ በኋላ ዋነኛ የግጭት መንስኤው መሆኑ እና ሌሎች ጉዳዮችን ጨምረው ከጠቃሚነቱ ይልቅ ጎጂነቱ እንደሚያመዝን የብሄረሰቡ አባላት ይገልፃሉ::

ኩናማ ብሔረሰብ ለህጻናት ይሁን ለታዳጊ ልጆቹ ስም የሚሰጠው በአብዛኛው ከአጋጣሚዎች ጋር በማያያዝ ነው። ከአጋጣሚዎቹ ውስጥ አንዲት ነፍሰጡር ከመኖሪያ መንደሯ ወደ ሌላ መንደር እየተጓዘች/ እየሄደች ድንገት መንገድ ላይ ከወለደች እና ሴት ልጅ ከሆነች "እጅጃ"[28] ፣ "ታቢላ"[29] የሚሉ መጠሪያዎች ሲሰጧት ÷ በወረራ ወቅት ከተወለደች "ኣጃጂ"[30] ትባላለች። በአንዳንድ የብሔረሰቡ ዓበይት በዓላት ከተወለደች ደግሞ "ፍርዲ"[31] የሚል መጠሪያ ይሰጣሉ (ቆርኔሊዎስ÷ 1980፡17)።

በሁለተኛ ደረጃም የብሔረሰቡ ታዳጊዎች ከልጅነት ወደ አዋቂነት መሸጋገሪያ[32] ጊዜ ተብሎ በሚዘጋጀው በዓል ላይ ስም ይሰጣቸዋል። በዚህ ወቅት የሚሰጧቸው ስሞች ለወንድም ሆነ ለሴት አንድ ዓይነት ነው። በዚህ ምክንያት ስሞቹን ይዞ ጾታ ለመለየት አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚ ይፈጠራል።

---

[28] በረሃ ማለት ነው

[29] መንገድ

[30] ወረራ

[31] ፌስታ ደስታ

[32] በኩናማ ብረሄረሰብ ወንዶች ከ ልጅነት ወደ ጉርምስና የሚሸጋገሩት የሽግግር ወቅት ወይ "እናኢላ" በሌላ መጠርያው "የመላጨት ስርዓት" ያከብራሉ። በዚህ የሽግግር ወቅት ያላለፈ ማንም ለዓቅመ አዳም የደረሰ ወንድ እንደወንድ አይቆጠርም። ወንድነቱን ያጣል፣ ጋብቻ ብሎ ነገር አይታሰብም። በተጨማሪም በብሄረሰቡ የሚካሄዱ ልዩ ልዩ ስርዓቶች እና ጨዋታዎች በሃላፊነት ሊካፈል ሊፎክር አይችልም። ይህ በደቡብ ብሄር ብረሰቦችና ህዝቦች የሐመር ብሄረሰብ የሚፈጽሙት የጋብቻ ሽግግር ማለትም የክብት ዝላይና ግርፋት ጋር ተመሳሳይነት ይታይበታል። ከብቶቹን ያልዘለለና ያልተገረፈ ጋብቻ መፈጸም አይችልምና። ይህ ተመሳስሎ የመነጨው የሁለቱም ብሄረሰቦች ምንጭ አንድ መሆን ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

3. የግጭት ንድፈ ሓሳባዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጥናቶች

በዚህ ምዕራፍ ስር የግጭት ብያኔ እና ባህርያት፣ የግጭት ዓይነቶችና ደረጃዎች፣ የግጭት መንስኤዎች፣ የግጭት አፈታት ዘዴዎችና የተዛማጅ ጥናቶችን አስመልክቶ ትንታኔ ይቀርባል።

3.1. የግጭት ብያኔ

በግጭትና በመሰል የመ·ያ መስኮች የተሰማሩ የተለያዩ ምሁራን ስለ ግጭት ምንነት፣ ዓይነትና መንስዔ ብዙ ፅፈዋል። ከነዚህ መካከል Fisher እና Ibrahim (2000) Fisher (1962) Krisperg (1998:2) ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ፀሓፍት፥ ግጭት አንዱ ወገን የሌላውን ወገን ጥቅም፣ ግብ፣ ፍላጎት፣አተያይ፣ ባህሪ መሰረት አድርጎ የሚከሰት እንደሆነ ይገልፃሉ።

ግጭት የማይጣጣሙ ወይም ተቃራኒ የሆኑ ድርጊቶች ባሉበት ቦታና ጊዜ ሁሉ የሚፈጠር ክስተት እንደሆነ ብዙዎቹ ምሁራን ያምናሉ። አንድ ድርጊት ከሌላው ጋር ሳይጣጣም ሲቀር ተቃራኒውን መገደቡ ወይም ማገዱ ወይም በተቃራኒው ድርጊት ወይም ፍላጎት ጣልቃ በመግባት በእንቅስቃሴው ውስጥ ችግር ፈጣሪ መሆኑ አይቀርም። እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ታድያ ከባድ ወይም ቀላል ግጭቶችን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ባጭሩ ግጭቶች ተራ ያለመግባባትን ያክል ቀላል ወይም የጦርነትን ያክል ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ። አፈጣጠራቸውም በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል ይሆናል David (2004:24)።

ስለሆነም፥ የማይጣጣም ዓላማ ባላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች፣ ቡድኖች መካከል የሚፈጠረው ግጭት በሰዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ወይም ግንኙነት ውስጥ ያለና የሚኖር ክስተት ነው። ስለዚህ ጉዳይ አንዳንድ ምሁራን Stifting (2006:33); Tsegaye (2009:6); Loomis (1985:49) ግጭት ታሪካዊ ሂደት እንጂ ድንገተኛ ክስተት አይደለም፣ ግጭት በሂደት ያለ እንጂ ድንገተኛ ክስተት አይደለም እና ግጭት በሂደት ላይ ያለ እንጂ ከባዶ ተነስቶ በድንገት የሚፈጠር ክስተት አይደለም ሲሉ ይገልፃሉ።

የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፥ ግጭትን መጥፎ ክስተት የሚያደርገው ወይንም የሚያሰኘው የሰዎች አያያዝ እንጂ ግጭቱ በተፈጥሮው ክፉ ሂደት ወይም ክስተት ሆኖ አይደለም። ይልቁንም በአግባቡ ከተያዘ አንድም ለልማት፣ አንድም ለዕድገት፣ አልያም ለለውጥ ጠቃሚ መሳርያ መሆኑ ይታመናል። *"Conflict is not necessarily bad. a bad handling, that is mismanagement, might make it bad. ... In and of itself, however conflict can be an important catalyst of change, innovation and development ... Conflict can be productive if it is properly managed and transformed"* Tsegaye (2001:8) (*ግጭት ሁልጊዜ መጥፎ አይደለም። ግጭትን መጥፎ የሚያደርገው ግጭቱን ለመፍታት የሚወሰደው ጥሩ ያልሆነ ዘዴ ነው። ግጭት በተገቢው ሁኔታ ከተያዘ ግን ለለውጥና ለእድገት ትልቅ መሳርያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።*) ሲል ፀጋዬ ይገልፃል።

ከፍ ሲል፥ ግጭት ሁሌም ከሰዎች ጋር አብሮ ያለና የሚኖር ክስተት መሆኑ ተጠቅሷል። ያለና የሚኖር ሂደት በመሆኑም የራሱ የሆኑ የእድገት ደረጃዎች አሉት። ይህ ከሰዎች ጋር አብሮ ያለ ሂደት፥ መጀመርያ ቀስ በቀስ ምናልባትም፥ ሰዎች ሊገነዘቡት በማይችሉት እውነታና መንገድ አድጎ ይከሰታል።

ግጭት የሚገለፀው ወይም መኖሩ የሚታወቀው ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ፍላጎቱን ያሳወቀ ወይም የሌላውን ፍላጎት በግልፅ የተቃወመ እንደሆነ ነው። በዚህ ሁኔታ ራሱን የገለፀው ግጭት በአግባቡ ካልተያዘ ወይም ቀደም ሲል (ከመከሰቱ በፊት) መከላከል ካልተቻለ ወደ ሚቀጥለው ከፍተኛ ደረጃ (ፀብ ወይም ጦርነት) ሊያድግ ይችላል። ከዚያ በኋላ ይረግባል። ሰላም ይወርዳል። ግን ጨርሶ አይጠፋም ወይም አይሞትም። እንደገና በሌላ ጊዜና ቦታ በሌላ መልክ ይገለጣል። ዑደቱ ይቀጥላል *"... conflicts are bound to be with us always. We won't "resolve" them. Nor can we eradicate them we can prevent them. We can handle or manage them when they do occur. We can transform them. When we are lucky..."* Tsegaye (2001) ። ከዚህ በመነሳት፥ ግጭት ያለና የሚኖር ሂደት ከሆነ የግጭት አያያዝ ስርዓቱም እንዲሁ ያለና የሚኖር ሂደት ይሆናል። ግጭትን ለመቆጣጠርና ለመፍታት ደግሞ የአያያዝ ዘዴ ወይም ስልት ወይም ይህን የሚያከናውን ተቋም ሊኖር የግድ ይላል።

3.2. የግጭት ዓይነቶችና ደረጃዎች

የግጭት ዓይነቶች ከተለያዩ መመዘኛዎች አንፃር በተለያዩ መንገዶች እንደሚቦደኑ አንዳንድ ምሁራን ይገልፃሉ። ለምሳሌ፥ Heinz (2006:2) ሁሉም አካዳሚያዊ መስክ ማለት ይቻላል፣ የግጭት ዓይነቶችን በየራሱ አተያይና አመለካከት ሲቦድን እንደሚገኝ ገልጧል። ኢኮኖሚስቶች ውሳኔ ሰጪነትን (decision making) ፣ የስነ ልቦና ተመራማሪዎች ግላዊ ግጭት (Inter Personal Conflict) ፣ የስነ ሰብዕ ምሁራን የገገርና የተገገር መደቦችና የኑሮ ደረጃ፣ እንዲሁም ከፖለቲካ ሳይንስ አንፃር አለማቀፋዊና (international) በሐውርታዊ (intra-national) ተብሎ ይመደባል ሲል አስፍሯል።

በሌላ መልኩ Toure (1999:25) የግጭት ዓይነቶችን ከመከሰቻ ምክንያታቸው አንፃር በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከፈሉ "*conflict arises from human relation in two principal ways: first, individuals or groups have different values, needs and interest and second most resources are not available in unlimited quantities and so access to them must be controlled and fought for*" *(በሰዎች ግንኙነት ውስጥ ግጭት በሁለት መንገድ ይከሰታል፤ አንደኛው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የተለያዩ ፍላጎቶች፤ አመለካከቶችና ግምቶች ስላሏቸው ነው። ሁለተኛው ደግሞ በጣም ተፈላጊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎች እንደልብ ስለማይገኙ እነሱን የራስ ለማድረግ የሚደረግ ሽኩቻ ናቸው)* ሲል ቶሬ ገልፀዋል።

ስለሆነም፥ ግጭት በሰዎች መካከል ባለ ማህበራዊ ግኑኝነት ውስጥ ግለሰቦች (Individuals) ወይም ቡድኖች (Groups) የማይጣጣም ፍላጎትና እሴት ሲኖራቸው የሚፈጠሩና፤ የተፈጥሮ ሀብት እንደልብና ያለገደብ ተሟልቶ ስለማይገኝ፤ ያለውን ለማግኘት በሚደረግ መፍጨርጨር ውስጥ ግጭት እንደሚከሰት ይዘረገፈራል።

እንዲሁም የስነ ሰብዕ ተመራማሪ የሆነው Fisher (1982) የግጭት ዓይነቶችን በስድስት ክፍሎ እንደሚከተለው አስቀምጧቸዋል።

- **ግላዊ ግጭት (Inter personal conflict)** ይህ በሁለት ሰዎች መካከል በፍላጎት፣ በአላማ፣ እንዲሁም በምርጫ አለመጣጣም ሲኖር የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።
- **ሚናዊ ግጭት (Role conflict)** አንድ ግለሰብ በአንዱ ግለሰብ ጥገኛ (Interdependent) በሆነበት ማህበረሰብ ውስጥ በሃላፊነት፣ በድርሻ፣ እንዲሁም ግምት (Expectations) ልዩነት ሲኖር የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።
- **የቡድን ግጭት (Inter group conflict)** በቡድን፣ በጎሳ፣ ብሔረሰብ፣ በሃይማኖት ወዘተ. መካከል የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።
- **ህብረ ቡድናዊ ግጭት (Multi-party conflict)** በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የተለያዩ ፍላጎቶች ባላቸው ቡድኖች መካከል በፖሊሲ፣ በስልጣን ክፍፍል፣ በልማት ስርጭት፣ በሀብት አጠቃቀም ወዘተ. አለመግባባትና አለመጣጣም ሲኖር የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።
- **አለማቀፋዊ ግጭት (International conflict)** በሁለት የተለያዩ አገሮች መካከል የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።

እንዲሁም Allwood (1993:2-3) ደግሞ የግጭት ዓይነቶችን፥ የተዳፈነ ግጭት (Latent Conflict) ፣ ግልጥ ግጭት (Overt Conflict) እና ድብቅ ግጭት (Covert Conflict) ሲል ይገልፃቸዋል። የተዳፈነ ግጭት በሁለት ወገኖች መካከል የሚያጋጥም ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ግን ይሄ ሁኔታ ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል ብለው አያስቡም፤ ግልጥ ግጭት ደግሞ ሁለት ወገኖች የሚጋጩበትን ጉዳይ አውቀው ወደ ግጭት ሲገቡ የሚፈጠር ሲሆን ድብቅ ግጭት ደግሞ አንድ ወገን ስለጉዳዩ ምንም ፍንጭ ሳይኖረው በሌላ ወገን የሚፈፀምበት ጥቃት መሳሳት በማድረግ የሚፈጠር ግጭት ነው ሲል በሶስት ይመድባቸዋል።

በ Mpangala (2004:1) አስተያየት ግጭትን በዓይነት ለመፈረጅ የተለያዩ መንገዶችን መከተል ይቻላል። ከውስብስብነት (Complexity) አንፃር፥ የተወሳሰቡ እና ያልተወሳሰቡ

ግጭቶች፤ ከጊዜ አኳያ የሚደረግ ምደባ ደግሞ ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ ግጭቶችና ለረጅም ጊዜ የሚዘልቁ ግጭቶች፤ ሁከት የሚያስከትሉ (Violence Conflict) እና ብጥብጥ የማያስከትሉ (Non – Violence Conflict) ሶስተኛ መመደቢያ ሆኖ ሊታይ ይችላል። አራተኛው የመቦደኛ መንገድ ደግሞ የግጭቱ መጠን (Scale Of The Conflict) መሰረት አድርጎ ውስጣዊ፣ ክልላዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሊባል ይችላል። አምስተኛው መመዘኛ ደግሞ የግጭቱን አስፈላጊነት ወይም አላስፈላጊነት መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አፍሪካዊያን ለነፃነታቸው ሲሉ ከቅኝ ገዥዎች ጋር ያደርጉት የነበረው ፍልሚያ "አስፈላጊ" የሚባል ዓይነት መሆኑን ይገልፃል።

ከፍ ሲል በተጠቀሱት ይሁን በሌሎች የግጭት ዓይነቶች፣ ግጭት አንድ ጊዜ ከተነሳ በኋላ፣ እያደገና፣ እየተስፋፋ መልኩንና ደረጃውን እየለዋወጠ ይሄዳል። ስለሆነም የግጭትን ሂደትና ደረጃ (Stage) መረዳት ትልቅ ጥቅም እንዳለው Heinz (2006:4) ይገልፃል። Heinz የእርሱን አስተያየት ከማቅረቡ በፊት Braham (2003) ያስፈራቸውን ሰባት የግጭት ደረጃዎች ያሰፍራል። የመጀመርያው የተዳፈነ ግጭት (Latent Conflict) ያለበት ነው። ሌሎቹ የግጭት መጀመር (Conflict Emergency)፣ የግጭት መባባስ (Conflict Escalation)፣ ግጭት ከፍተኛ ደረጃ መድረስ (Hurting Or Stalemate)፣ የግጭት መቀዝቀዝ ወይ ድርድር (De-Escalation/Negotiation)፣ የግጭት መፈታት (Dispute Settlement) እና ድህረ ግጭት ወይ ሰላም ማስፈን (Post-Conflict/Peace Building) ናቸው። ከነዚህ ቀጥሎ በእርሱ አስተያየት ግጭት የሚያልፍባቸው ደረጃዎች ሶስት እንደሆኑ ገልጾ እነሱም፣ ጅማሬ (Beginning)፣ እድገት (Development) እና ፍፃሜ (End) ናቸው ብሎ ይደመድማል።

3.3. የግጭት መንስኤዎች

በአንድ ግለሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ሃገር ውስጥ ግጭት ሊፈጠሩባቸው የሚችሉ ምክንያቶች የተለያዩ እንደሆኑ የዘርፉ አጥኚዎች ይገልፃሉ። ከነዚህም Fisher (1982:1) ለግጭት መንስኤ ናቸው ያላቸውን ሶስት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ግጭቱ የኢኮኖሚ ሲሆን ሰዎች ብርቅና ውድ እቃዎችን የራስ ለማድረግ በሚደረግ ትንቅንቅ የሚያጋጥማቸው ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ሁሉም ሰው እነዚህን ጥሬ

እቃዎች የራሱ ለማድረግ ይፈልጋልና። ይህን ነጥብ በኢትዮጵያ ምሳሌ ለማቅረብ በመሬት፣ በውሃና በግጦሽ መሬት የሚነሱትን ግጭቶች መግለጽ ይቻላል።

- **የእሴት (value conflict)** ሲል ደግሞ ሰዎች በአኗኗር ስልት፣ በአይዲዮሎጂ፣ እንዲሁም እንደ እምነት በሚወስዷቸው ምርጫዎች፣ መርሆችና ተግባሮች አለመጣጣም የተነሳ ወደ ግጭት የሚያመሩበትን ሁኔታ ይገልጻል። ለምሳሌ፡ "ቀዝቃዛ ጦርነት (Cold War)" በመባል የሚታወቀውን እንደ ምሳሌ ይጠቅሳል።
- **ስልጣን (power conflict)** አንድ ቡድን በሌላ ቡድን ላይ የስልጣን የበላይነት ሊያሳይ በሚፈልግበት ጊዜ የሚፈጠር ግጭት ነው ሲል አስፈሯል።

በተጨማሪም Coser (1968:22) ለግጭት መከሰት ምክንያት ናቸው ብሎ የሚያቀርባቸው እሴት፣ ማህበራዊ ደረጃ እና የምጣኔ ሀብት እጥረት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ አስቀምጠዋል።

3.4. የግጭት አፈታት ዘዴዎች

በተለያዩ አጋጣሚዎችና ምክንያቶች የተከሰተው ግጭት ተስፋፍቶና ስር ሰዶ በህይወትና በንብረት ጥቃት ከማድረሱ በፊት የሚወገድበትና ዘላቂ ሰላም የሚወርድበት ዘዴ እንዳለ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ።

Tsegaye (2009፡12) ግጭቶች በዓይነታቸውና በመነሻ ምክንያቶቻቸው ይለያዩ እንጂ ሊፈቱ የሚችሉባቸው ወይም የሚታረቁባቸው ስልቶች ወይም መንገዶች ሁለት ብቻ ናቸው። እነዚህም መደበኛ (Formal Methods) እና ኢ-መደበኛ (Informal Methods) ስልቶች ናቸው ሲሉ ገልፀው፤ መደበኛ ስልት ÷ ፖለቲካዊና ህጋዊ የግጭት አያያዝ ስርዓቶችን የሚያጠቃልል ወይም ግጭቶችን በተፃፉ ሕጎች፣ በፍርድቤቶችና በዲፕሎማሲያዊ አገባብ ለመፍታት የሚያስችል ነው ይላሉ። ሁለተኛውና ኢ-መደበኛው የግጭት አያያዝ ስልት÷ ያልተፃፈ ግን በልማድ በሚከናወን ህገረሰባዊ የግጭት አያያዝ ስርዓትን (Local Methods) የሚመለከት ነው። ይህ ዓይነቱ ስልት ላለፉት በርካታ ዘመናት በበርካታ የዓለም ህዝቦች ዘንድ በስፋት

ሲሰራበት የነበረ፤ ዛሬም በአንዳንድ አከባቢዎች እየተሰራበት ያለ ሀገረሰባዊ እውቀት ነው። ይህ ስልት በተለይም በአገራችን ህዝቦች ዘንድ የተለመደ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ሌሎች ምሁራን Schellenberg (1996:9); Bohannan (1967:54); Gulliver (1979:37) ግጭቶች የሚፈቱባቸው መንገዶች ሁለት ናቸው ይላሉ። እነሱም የሁከት (The Violence) ማለትም የተፈጠሩት ግጭቶች በብጥብጥና በሁከት ዕልባት ሲያገኙ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሰላም (Peaceful) ማለትም የተፈጠሩ ግጭቶች በሽምግልና፤ በድርድር፤ ዕርቀ ሰላም ሲወርድ ነው።

ከፍ ሲል ከልዩ ልዩ ፀሓፍት የቀረቡት የግጭት ብያኔ፤ የግጭት ዓይነቶችና ደረጃዎች ፤ የግጭት መንስኤዎች እና የግጭት አፈታት ዘዴዎች፤ እዚህ የቀረበበት ዋና ምክንያት ለማስተዋወቅ ነው። ከነዚህ ትወራዎች፥ ግጭቶች እንደ ዓይነታቸውና አፈጣጠራቸው መለያየት የሚረግቡባቸው ብሎም የሚፈቱባቸው ዘዴዎችም እንደዚሁ በርካታ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። በትውሮቹ የቀረቡት አንዳንድ ሃሳቦች ከኩናማ ብሔረሰብ የግጭት ምንነት፤ የግጭት መነሻ ምክንያቶችና የግጭቶች መፍቻ ተቋም (ሳንጋኔና) ጋር ያላቸውን ገፅታ በክፍል አራት አቀርባለሁ።

3.5. የተዛማጅ ጥናቶች

የዚህ ጥናት ትኩረት "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሄረሰብ" የሚል ነው። ከጥናቱ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ማለትም በሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ላይ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፤ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል የተደረጉ ጥናቶች አስራ ሰባት (17) መሆናቸው ከአማካሪዬ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ብረዳም፤ የዳሰስኳቸው የጥናት ወረቀቶች ግን ሰባት (7) ብቻ ናቸው። እነዚህ የዳሰስኳቸው የጥናት ስራዎች ትኩረት ያደረጉበትን ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ምን እንደሚመስል ተምሬባቸዋለሁ። ከዚህ ውጭ ግን ከዚህ ጥናት ጋር የቀጥታ ግንኙነት ስለሌላቸው እዚህ አላቀርብም። መዳሰሴን ለማመልከት በዋቢ መጻህፍት አስፍሬያቸዋለሁ።

4. ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ

የኢትዮጵያ ኩናማ ብሔረሰብ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ ሦስት ብሔረሰቦች አንዱ ሆኖ፥ በክልሉ በስተሰሜንና ሰሜን ምዕራብ እንደሚገኝ ተገልጧል። በዚህ ምዕራፍ ስር፥ ኩናማ ብሔረሰብ ስለ ግጭትና ምንነቱ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? እንዴትስ ይበይኑታል?፣ ዋና ዋና የግጭት መንስኤዎችስ ምንድን ናቸው?፣ በአጋጣሚ ይሁን በሌላ ምክንያት የተፈጠረው ግጭትስ ባህላዊ ዘዴን ተጠቅመው እንዴት ያረግቡታል? እንዴትስ ይፈቱታል ወይም ዘላቂ ዕርቅ እንዴት ያመጣሉ? የአፈታቱ ስርዓትስ ምን ይመስላል ለሚሉ ዋና ዋና ጥያቄዎች በምርምር የተገኙት መልሶች ይቀርባሉ።

4.1. የግጭት ምንነት በኩናማ ብሔረሰብ

ግጭት አንዱ ወገን የሌላውን ወገን ጥቅም፣ ግብ፣ ፍላጎት፣ ባህሪ በተቃረነ ወይም በተጋፋ ጊዜ ወይም የሌላውን ባህሪ/ዓላማ የሱን ባህሪ ወይም ዓላማ የሚቃረን መሆኑን በገመተ ጊዜ የሚፈጠር ክስተት እንደሆነ፤ የሁለት ወገኖችን ባህሪ፣ ፍላጎትና አተያይ መሰረት አድርጎ የሚከሰት ተቃርኖ እንደሆነ በክፍል ሦስት ተገልጧል። የብሔረሰቡ አባላትም ግጭትን "‹አዳማ› ማለት ረብሻ፣ ጥል ማለት ነው። ምን ሆነህ ነው ግጭት የምትፈጥረው ሲባል በሁለት ሰዎች መካከል የሚፈጠር አለመጣጣም ማለት ነው" (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 39) ሲሉ ይበይኑታል።

እንዲሁም ሌላው መረጃ አቀባዬ የግጭትን ተፈጥሮአዊነትና አይቀሬነትን ሲገልፁ፤ "ግጭት በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠር ተፈጥሮአዊ ክስተት አይደል? [አብረህ] ስትኖር ሁልጊዜም... [የተመቻቸ] ሆኖ የሚገኝ ነገር የለም፣ [የሚጎረብጥ ሁኔታ] ሲያጋጥም ግጭት ይፈጠራል፣ የጎላ ግጭት ሊሆን ይችላል ወይም የግል ግጭት ሊሆን ይችላል" (ብርሃነ ሃይለስላሴ ሽወለ. መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 99) ብለዋል።

በአጠቃላይ እንደመረጃ አቀባዮቹ አገላለፅ፥ ግጭት በኩናማ ብሔረሰብ ጥል፣ ረብሻ እና በሁለት ሰዎች እና ቁጥራቸው ከዚያ በላይ በሆነ ሰዎች መካከል የሚፈጠር አለመጣጣም እንደሆነና በሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ ሂደት አይቀሬ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል።

4.2. የግጭት መነሻ ምክንያቶች

በክፍል ሦስት ከቀረቡት የግጭት መነሻ ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት ከሀብት (Resource) ጋር ተያይዞ የሚነሳ እንዲሁም ከክብርና ከስልጣን ጋር ተያይዞ የሚነሳ እንደሆነ ተገልጧል፤ በዚሁ ብሔረሰብም ዋነኛው የግጭት መነሻ ምክንያቶች ከሀብት ጋር የተያያዙ ናቸው።

በኩናማ ብሔረሰብ ግጭትን የሚቀሰቅሱ ምክንያቶች ክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊትና በኋላ የተለያዩ እንደሆኑ የብሔረሰቡ አባላት ያስረዳሉ። ስለዚህ ጉዳይ መረጃ አቀባዮቼ እንደሚከተለው ብለዋል። ኩናማ ቀደም ባሉ ጊዜያቶች በዋናነት ማለትም በቅድመ ክርስትና ወደ ግጭት የሚያስገቡት ምክንያቶች ድንበር መግፋት (መሬት አልፎ ማረስ) ፤ሌብነት፤ ጎሳዊ አስተሳሰብ[33]፤መጠጥ፤ አሉባልታ ወሬዎችና ፀያፍ ስድቦች[34] እንደነበሩ ይገልፃሉ (ዑስማን ሻዳ መስከረም 14፤ 2003 ዓ.ም÷ ገፅ 72 ፤ብርሃነ ሃይለስላሴ ሽወሊ መስከረም 15፤ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 100፤ ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፤ 2002 ዓ.ም÷ ገፅ 39) ።

ከፍ ሲል የተጠቀሱት የብሔረሰቡ የግጭት መከሰቻ ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው÷ ክክርስትና ሃይማኖት መቀበል በኋላ በርካታ የብሔረሰቡ አባላትን ለሞት የሚያበቃ የግጭት መንስኤ ከሴቶች ጋር በተያያዙ ችግሮች የሚመጡ እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ይገልፃሉ።

ክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት÷ "የኔ! ያንተ!" የሚባል የትዳር ሕይወት አልነበራቸውም። ማንም ተነስቶ ከፈለገው ቤት ጎራ በማለት ያሻውን ማድረግ የተፈቀደና የተለመደ ነበር። ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ አቶ ሃይለ ወለላ "በቃ ሚስቴን አንተ ሚስትህ እኔ [ነበርን።] እኛ እንዲህ አድርገን ነበር የምናልፈው። እኔ እስክጎረምስ ይህን አውቀዋለሁ። በሴት ተጣልተን አናውቅም ነበር" (ነሓሴ 20፤ 2002 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 40) ሲሉ ይገልፃሉ። ይህንን ልማድ ብሔረሰቡ ከትውልድ ትውልድ ሲያሸጋግረውና ሲቀባበለው ቆይቶ ክክርስትና ሃይማኖት መጠመቅ በኋላ ዋነኛው ግጭት ቀስቃሽ እና የብሔረሰቡ መገዳደያ ምክንያት እንደሆነ "ክርስትና [ከተቀበልን] በኋላ አሳቱ እንኳን በሴት የመጣ ነፍስ አጥፍተዋል... እዚች አሁን

---

[33] ኩናማ ብሔረሰብ አራት የተለያዩ ጎሳዎች እንዳሉት በክፍል ሁለት መመልከት ይቻላል።
[34] በኩናማ ብሔረሰብ ፀያፍ ስድቦች የሚባሉት ቀደም ባሉ ዘመናት ብሔረሰቡ ሲጠራባቸው የነበሩ ስሞች (እንደ ባርያ፤ ሻንቅላ ወዘተ. ያሉ) በአሁኑ ጊዜ የተከለከሉትን ያጠቃልላል።

ያለሀባት ቤት ነፍስ አጠፋ። ሚስቴ ጋር አድርሃል ተባብለው ተጋደሉ። ለሴት ብለው እዚህ በስንት የደም ካሳ አልፈነዋል" (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 40) ሲሉ ገልፀውልኛል።

በአጠቃላይ ዋና ዋናዎቹ የግጭት መንስኤዎች ኢኮኖሚ ነክ የሆኑ ማለትም ድንበር መግፋት፣ ሌብነት (በሬ፣ የጎተራ እህል ወዘተ.)፣ አሉባልታ ወሬዎች፣ ፀያፍ ስድቦችና ጎሳዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም መጠጥ ከክርስትና ሃይማኖት መጠመቅ በፊት የነበሩ ሲሆኑ፤ ከክርስትና ሃይማኖት መቀበል በኋላ ግን የበፊቶቹን ጨምሮ በ "ትዳር ላይ መወሰለት" ዋነኛው የግጭት መንስኤ እንደሆነ ከመረጃ ሰጪዎቼ ለመረዳት ተችሏል። ከክርስትና ሃይማኖት መቀበል በኋላ በ "ትዳር ላይ መወሰለት" ዋነኛው የግጭት መንስኤ የሆነበት ምክንያት፤ በፊት የነበራቸው እንዳሻቸው በፈለጉት ቤት ገብቶ የማደር ልማድ ከክርስትና ሃይማኖት መቀበል በኋላ ስለተከለከለ ነው።

4.3. ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

ግጭት በግለሰብ በቡድንና በዓለማቀፍ ደረጃ ሲከሰት እና በአግባቡ ካልተያዘ ከቀላል እስከ ከባድ ጥፋት ሊያስከትል እንደሚችል የታወቀ ነው። ስለሆነም ግጭቶች ተጠናክረውና ስር ሰደው ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት መርገብ ብሎም መፈታት አለባቸው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና የግጭት መንስኤ ምክንያቶችና በሌሎች ጥቃቅን ምክንያቶች የተቀሰቀሱት ግጭቶች፤ እንደየግጭቶቹ ቅለትና ክብደት ከተራ አለመግባባት እስከ ከባድ እልቂት የሚያደርሱ አደጋዎች ሊያስከትሉ ይችላሉ። ስለሆነም ብሔረሰቡ ተራ ግጭቶችን "ላጋኬ" በተባሉ ሽማግሌዎች፤ የግድያ ግጭትን በተመለከተ ደግሞ "ሳንጋኔና" ወይም "የአጥንት አስታራቂዎች" በመባል በሚታወቁ ሽማግሌዎች ያረግባሉ፤ ዕርቀ ሰላም ያወርዳሉ።

4.3.1. ላጋኬ[35]

በኩናማ ብሔረሰብ ከተራ አለመግባባት ጀምሮ እስከ ከግድያ በታች ያሉትን ግጭቶች፤ የሚመረምሩት፣ የሚያረግቡት እንዲሁም ዘላቂ ዕርቅ የሚያመጡት "ላጋኬ" ወይም በሌላ አጠራር አገር አስተዳዳሪዎች፣ መንደር ቆርቋሪዎች ተብለው የሚጠሩ የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው። "ላጋኬ የሚባሉ ሽማግሌዎች ናቸው። በአጠቃላይ የሀገር ሽማግሌ ማለት እኮ ነው። ላጋኬ ማለት ከሞት በታች የሆኑ ግጭቶች የሚፈቱ ናቸው። በተጨማሪም ሳንጋኔና የዕርቅ ስርዓቱን ለመጀመር በመጀመርያ እነሱ እንዲያሳምኑ በሳንጋኔና የሚላኩ ናቸው" (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 45)።

ላጋኬ ወይ ላጋማናይ በብሔረሰቡ የሚፈጠሩ ጥቃቅን ግጭቶችን እንደ የባልና ሚስት ግጭትና የመሳሰሉት ዕልባት እንዲሰጡ በብሔረሰቡ የተመረጡ ሽማግሌዎች ናቸው (ዑስማን ሻዳ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 74)። ሆኖም የእነዚህ ሽማግሌዎች ሓላፊነት እንደነዚህ ዓይነት ግጭቶችን የማርገብና ዘላቂ ሰላም በማምጣት ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም።

ላጋኬ ከአስታራቂነታቸው በተጨማሪ በብሔረሰቡ የሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ስርዓቶች የመክፈቻና የመዝጊያ ፀሎት እንዲሁም ምርቃት ያቀርባሉ። ከነዚህ ስርዓቶች[36]÷ የፉሽካ ስርዓት፣ ኮሎኺሻ ስርዓት፣ አናሳሳ ስርዓት፣ ጋብቻ፣ ግዘረት፣ ተዝካር፣ ማስካላ በዓል፣ ሻታ በዓል፣ ቱካ በዓል፣ ታፊላ በዓል፣ ሾምሩ በዓል፣ የካላ ስርዓት፣ የአናኢላ ወይም የመላጨት ስርዓት እንዲሁም ኮንዱራ በዓል ወዘተ. በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው *ሂቆዲምስ (1973)* ። ላጋኬዎች የሚፈትዋቸው ግጭቶችና ቅራኔዎች በርካታ ናቸው። ሁሉንም እዚህ ለመጥቀስ አይቻልም።

---

[35] በጥናቱ ወሰን እንደገለፅኩት የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በግድያ ግጭት የአፈታት ስርዓት ላይ ነው። ሆኖም አሁን በመቅረት ላይ ያለውን የ "ላጋኬ" የአነስተኛ ግጭት አፈታት ስርዓት፤ ከአንዳንድ ሰነዶችና ሌሎች የፅሑፍ መረጃዎች በመጭመቅ ስርዓቱ ሲፈፅማቸው የነበረውን ክንውኖች፤ እንዲሁም አበርክቶት ያለፈውን ፋይዳ ለማሳየት በመጠኑም ቢሆን ለማሳየት የቀረበ ነው። የጭምቅ ሀሳቡ የተገኘባቸው መረጃዎች በዋናነት የብሔረሰቡ ተወካይና የወረዳ ታሕታይ አድያቦ የመንግስትና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ እንዲሁም የምክርቤት ፊደራሽን አባል የሆኑት አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ፣ ቀደም ሲል በሃላፊነት ሲሰሩበት ከነበረ ቢሮ (የትግራይ ባህልና ቱሪዝም የታሕታይ አድያቦ ቅርንጫፍ)፤ ወደ ዋናው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ስለብሄረሰቡ አጠቃላይ ታሪክና አንዳንድ ስርዓቶች ፅፈው ከላኩቸው ሰነዶች እንዲሁም በቅርብ ቀን ለህትመት ከሚበቃው የግለሰቡ መፅሐፍ ነው። አቶ ብርሃነ የላኩቸውን 12 ሰነዶች ከነ የቱሪዝም ቢሮው ማህተምና የሃላፊዎቹ ፊርማ በእጄ ይገኛሉ። ስለሆነም ስለ "ላጋኬ" ባህላዊ ስርዓት በዋናነት የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉኝ እነዚህ መሆናቸውን ለመግለፅ እፈልጋለሁ።

[36] እነዚህ ብሄረሰቡ በዓመት አንድ ጊዜ የሚያከብራቸው ልዩ ልዩ ስርዓቶች ናቸው።

ስለዚህ፣ ከሚፈፅሟቸው ሽምግልናዎችና ውሳኔዎች ሦስቱን እጠቅሳለሁ። እነሱም የባልና የሚስት የፍቺ ስነ ስርዓት ሂደትና የሽማግሌዎች ውሳኔ፣ ከጋብቻ ውጪ የፀነሰችን ሴት ያስፀነሳት ወንድ ሲክድ የሚፈጠረውን ግጭት ለማብረድ የሚደረግ የአውጫጪኝ ("የካላ ስርዓት") ሂደት እና በባህላዊ መድሃኒት (ዕፅ) ሰው የሚያሳምሙትንና የሚገድሉትን ለማወቅ የሚደረግ የአውጫጪኝ እና የውሳኔ ሂደት ናቸው።

4.3.1.1 ላጋኬና የባልና ሚስት ፍቺ

በዚሁ ብሔረሰብ ውስጥ የባልና ሚስት ግጭቶች የተለመዱ ናቸው። ግጭቶቹ ቀላልና ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ። ቀላሎቹ ግጭቶች በእለታዊ ኑሮ የሚያጋጥሙ ጭቅጭቆችን ጨምሮ እስከተወሰነ ጊዜ የሚዘልቅ መኮራረፍ ሲሆን ከባድ የሚባሉ ግጭቶች ደግሞ እስከ መፋታት የሚያደርሱ ናቸው። ከባድ ከሚባሉ ግጭቶችም "በራሴ ነው"[37] በሚል ምክንያት እና በአሁኑ ወቅትም በትዳር ላይ መወሰለት ዋነኞቹ ናቸው።

ከፍ ሲሉ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተከሰተው ግጭት እየተፋፋመ ሲሔድ፣ "ላጋኬ" (የሃገር ሽማግሌዎች) ይመረምሩትና ጉዳዩ ለፍቺ የሚያደርስ ከሆነ የዳኝነት ስርዓቱ ከመጀመሩ በፊት በሁለቱ ባለትዳሮች መካከል የተወለዱ ልጆች ካሉ፣ ከፍቺው በኋላ ከማን ጋር ይሁኑ? የሚል ሀሳብ ይሰነዘራል። ይህም በሁለት መንገድ ይታያል።

ፍቺው የተወለዱት ልጆች የግዝረት[38] ስርዓት ከመፈፀማቸው በፊት ከሆነና የግዝረት ስርዓቱ በአጎታቸው (በእናታቸው ወንድም ወይም በቋንቋው በ "አኮ") ከተፈፀመ ከእናታቸው ጋር ወይ ከአጎታቸው ጋር ሆነው እንዲያድጉ ተብሎ ይወሰናል። ልጆቹ የግዝረት ስርዓት ከፈፀሙ በኋላ ከተፋቱ ግን፣ ልጆቹ ከአባታቸው ጋር እንዲሆኑ ይደረጋል። እነዚህ ልጆች ከማንም ጋር ይሁኑ

---

[37] ይህ አባባል በትግርኛው ተናጋሪ ህብረተሰብ በተመሳሳይ መንገድ ሲፈፀም ይስተዋላል። እንዲት ባለትዳር ሴት ባልዋ እንዲፈታት እንደምትፈልግ ለሽማግሌዎች ትናገራለች። የሽምግልና ሂደቱ ተጀምሮ ለፍቺ ያደረሳቸውን ችግር እንዲናገሩ ሲጠየቁ ሚስት "በራሴ ነው" ካሉች ሽማግሌዎች የልመናም ሆነ የሽምግልናውን ሂደት በማቋረጥ በቀጥታ እንዲፋቱ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ። "በራሴ ነው" ማለት በሽማግሌ ፊት የማይነገር የግብረስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ችግር እንደሆነ የአካባቢው አባቶች ይናገራሉ።

[38] በኩናማ ብሔረሰብ የግዝረት ስርዓት ከህፃንነት ወደ አዋቂነት መሸጋገርያ ወቅት ተደርጎ ይታሰባል።

ከማንም ወላጆቻቸውን እየሄዱ እንዲጠይቁ ይፈቀዳል። በልጆቹ ደስታና ሀዘን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ወላጆች የመሳተፍና የመገኘት ግዴታ ይጣልባቸዋል።

ላጋኬዎች በንዲህ መልኩ ካስተካከሉ ቀጣዩ ስራቸው ሁለቱ የተጋጩና ለፍቺ የደረሱ ባለትዳሮችን ሲዳኙ በብሔረሰቡ ሕግና ደንብ መሰረት ሁለት ገፅታዎች አሉ።

> አንደኛው÷ ለፍቺ ወይ ለአቤቱታ የቀረቡት ባለትዳሮች ጥፋቱ የባልየው ሆኖ በራሱ ጊዜ ሂጂ አልፈልግሽም ብሎ አባርሯት ከሆነ፣ ወላጆቿም ይሁኑ ዘመዶቿ ምንም ዓይነት ንብረትም ሆነ ካሳ እንዲሰጡ ወይ እንዲከፍሉ አይገደዱም ሲሉ ላጋኬዎች ፍርድ ይሰጣሉ። በዚህ ውሳኔም ምንም ዓይነት ክርክርም ሆነ እሰጣገባ አይፈጠርም *ብርሃነ (2001)* ።

ሁለተኛው የሽማግሌዎች ፍርድ፣ ሚስት በራሷ ጊዜ በቃኝ አልፈልግም "በራሴ ነው" ካለች ሽማግሌዎቹ ይወያዩበታል። በመቀጠልም፡-

ሽማግሌዎች፡- *አብ ማእከልኩም ዘአተወ ሰይጣን እንታይ እዩ ኃለዎ?*
ልጂ በመሃላችሁ የገባው ሰይጣን ምንድ ነው?

ባለጉዳይ፡- *እንታይ ክም ዝኮነ ባዕሉ ይፈልጦ እዩ እንተኣነ ግን ይእክለኒ*
በቃኝ ምን እንደሆነ እሱ ያውቀዋልና
ሕደገ ደአ አይክውንን ልወለድኪን ልአዝማድኪን እውን
አይጥዕምን
ተይ አይበጅም ላንቺም ለወላጆችሽም እንዲሁም ለዘመዶችሽ
ጥሩ አይደለምና
አነ ይእክለኒ "ብነብሰይ እየ" ኢለ አለኩ ሞ ሽማግለ ዓደይ
ብሰላም ፈሪድኩም ደአ አፋንዉኒ
እኔ በቃኝ "በራሴ ነው" ብያለሁ እንግዲህ የሀገሬ ሽማግሌ
ይፍረዱኝና በሰላም ይሸኙኝ
ዝወደይ እትፀውዮ ዘላ ኩሉ ሓቂ ድዩ?
ልጂ (ባልየውን) የምትናገረው እውነት ነው?
ብዝግባእ አይፈለጥኩን ክቡራት ዓበይቲ ዓዲ

በውል አላወቅኩም የተከበራችሁ ሽማግሌዎች

እንታይ ደአ ይገበር?

እንግዲያማ?

ብዝበለቶ ይኩነላ

ባለችው ይሁንላት

ስለዚ ይኩን ብዝበልክዮ ኮይኑ አሎ

እንግዲህ ይሁን ባልሺው ሆነዋል

እሺ የቀንየለይ ክቡራት ዓበይቲ ዓዲ

እሺ የተከበራችሁ የሀገር ሽማግሌዎች አመሰግናለሁ

ሲሉ የልመናውና የግጭታቸው ሂደት ላጋኬዎች ከተወያዩ በኋላ እና ተይ ተብሎ የማይተው የግጭት መንስኤ ሆኖ ከተገኘ በሰላም እንዲፋቱ ይወሰናል። ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው የላጋኬዎች የውሳኔ ሀሳብ ሚስት በራሷ ጊዜ አልፈልግም ብላለችና በብሔረሰቡ ደንብ መሰረት ባል ለጥሎሽ የከፈላቸው ከብቶች እና ሌሎች ንብረቶች በሙሉ እንዲመለሱለት ሲሉ ይወስናሉ። ከውሳኔው በኋላም ለጥሎሽ የተሰጡ ከብቶች የታረዱ እና የተሸጡ እንዲሁም በተፈጥሮ አደጋ ወይ በእድሜ የሞቱ ካሉ ተተክተው ለከፋይ ይመለሱለታል *ቶርኔሊያስ (1980፣27)* ።

ይህ ውሳኔ የሚፈፀመው ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው በሁለቱም መካከል የተወለዱት ልጆች ሁኔታ ተጠንቶ ነው። ልጆቹ በግዝረት ስርዓት ሳያልፉ የተለያዩ ከሆነና ከእናታቸው ጋር እንዲሆኑ ከተወሰነ፤ የጥሎሹ ውሳኔ የተለየ ይሆናል፤ ልጆቹ የግዝረት ስርዓቱን እስኪያልፉ ድረስ ከብቶቹ ከሚስት ጋር እንዲቆዩ ይደረጋል። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም በሌላው አካባቢ "የልጅ ማሳደግያ ተቆራጭ አድርግ" እንደሚባለው ሁሉ ከብቶቹም የልጆቹ ማሳደግያ ተደርገው ስለሚወሰዱ ነው። የግዝረት ስርዓት ካለፉ በኋላ ግን ልጆቹ እንደፍቃዳቸው ወደ አባታቸው የመሄድም ያለመሄድም መብታቸው እንደጠበቀ ሆኖ፣ ለጥሎሽ የመጡት ከብቶች ግን ወደ ባልየው እንዲሄዱ ይደረጋል።

4.3.1.2 የካላ (የአውጫጪኝ)[39] ስርዓት እና ላጋኬ

በኩናማ ብሔረሰብ ላጋኬ ከሚፈፅሟቸው በርካታ ስርዓቶች እና ውሳኔዎች ውስጥ የካላ ስርዓት አንዱ ነው *ብርሃነ (2001)* ። በብሄረሰቡ ውስጥ አንዲት ሴት ከጋብቻ ውጪ የግብረስጋ ግንኙነት ስታደርግ ቆይታ በመሃል ስትፀንስና ያስረገዘው ግለሰብ ሲክድ፤ በወንዱ ቤተሰብና በሴቷ ቤተሰብ መካከል ግጭት ይፈጠራል። "ካላ" ይህንን ግጭት ለመፍታትና ያስፀነሰውን ለመለየት በብሄረሰቡ እምነት መሰረት ላጋኬዎች የሚያዘጋጁት ስርዓት ነው።

ወላጆችና ዘመዶች ተሰባስበው ከጋብቻ ውጪ የፀነሰችውን ልጃቸው ከማን እንደፀነሰች ይጠይቋታል። ማንነቱም ትናገራለች። በተናገረችው መሰረት አጣርተው ማንነቱን ያወቁ ወላጆች በቀጥታ ወደ ላጋኬዎች በመሄድ የደረሰባቸውንና የተፈጠረውን ችግር እንዲሁም የተጠርጣሪውን ግለሰብ ማንነት ይናገራሉ። ላጋኬዎችም የተጠረጠረው ግለሰብ ቤት መልእክት በመላክ የካላ ስርዓት ላይ እንዲገኝ እንዲሁም ጥቁር ፍየል ይዞ እንዲቀርብ ትእዛዝ ያስተላልፉለታል። የተጠረጠረው ወንድ ከነ ቤተሰቦቹ የላጋኬ ትእዛዝ ፈፃሚዎች በመሆናቸው ጥቁር ፍየል ይዘው ላጋኬዎች ለዚሁ ስርዓት ማሰናጃ ባዘጋጁት በመንደሩ አከባቢ በሚገኝ የ "መቂዕ"[40] ዛፍ ስር ይቀርባሉ። በተጨማሪም የሴት ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ እንዲሁም የወንዱ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ በሙሉ በስርዓቱ ተገኝተው እንዲታዘቡ ይታደማሉ *ብርሃነ (2001) አድያቦና (2001፣ 29)* ።

ከታደሙት ዘመድ አዝማድ ውስጥ በቤተሰቡ ብሎም በአካባቢው ማሕበረሰብ ተሰሚነት ያለው አንድ ሰው ተመርጦ የመጣውን ጥቁር ፍየል እንዲያርድ ይደረጋል። ሥጋው በ "ጎላ" (በትልቅ ጎድጓዳ ድስት) እንዲበስል ይደረጋል። በስነስርዓቱ የተገኘው ሁሉም ሰው ተከፋፍሎ ይበላል። እዚህ ስርዓት ላይ ወጣወጥና ሌሎች ምግቦች እንዲቀርቡ አይፈቀድም። በስነስርዓቱ የሚቀርበውና ለምግብነት የሚውለው የበሰለ የፍየል ስጋ ብቻ ነው።

---

[39] ይህ ስርዓት በጃንሆይና ከዚያ በፊት በሌላው የሃገሪቱ ክፍል የሌባ ማወቅያ ሆኖ ሲያገለግል ከነበረው "የሌባ ሻይ ፈተና" ጋር ይዛመዳል።

[40] "መቂዕ" ብሔረሰቡ በረሃ ለበረሃ እየዞረ በኖረባቸው ዘመናት ለምግብነት ያውላቸው ከነበሩት የፍራፍሬ ዓይነቶች ዋነኛው ነው። የስርዓቱን ሂደት በዛፉ ስር እንዲሆን ያደረጉት ለረጅም ዘመናት በምግብነት እያገለገላቸው በመጣው ዛፍ ስር ሆነው ሀሰት መናገርን እንደ ሀጢአት ስለሚቆጥሩ ይመስለኛል። በስፍራው ተገኝቼ ዛፉን እንዳየሁት ለጥላነት የሚያገልግል በርከት ያለ ቅጠል የሌለው መሆኑ ግምቴን አጠናክሮታል።

ከመብሉ በኋላ ላጋኬዎች÷ በትንሽ በትንሹ ስጋ ይከትፉና በተከተፈው ስጋ ላይ ትንሽ ትንሽ ቀዳዳ በማዘጋጀት ረጅም ገመድ አምጥተው ይከቱታል። ይህ በገመድ የተከተተው ስጋ ከጋብቻ በፊት ለፀነሰችው ሴት ይሰጣታል። ከዚህ በኋላ ሰፋ ያለ ሰሃን ይዘጋጃል። ስጋ በገመድ የተቀበለችው ሴትም ከተደረደሩት የተከተፉ ስጋዎች የመጀመርያውን በመምዘዝ መጀመርያ የተገናኘሁት እና ያስፀነሰኝ ይህ ነው በማለት የወንድ ስም ትጠራለች። ከዚያም ከሷ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት የፈፀሙትን ወንዶች ስም ስጋውን በመምዘዝ አንድ በአንድ ማስቆጠር ትጀምራለች። እዚህ ቦታ ላይ ውሸት መናገር ነውር ነው ተብሎ ስለሚታመን ሁሉንም ትጠራቸዋለች። ከጠራቻቸው ወንዶች መካከል በብሔረሰቡ እምነት መሰረት ፅንሱ የመጀመርያው ተጠሪ ነው ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም የካደውን ፅንስ እንዲቀበል በላጋኬ ይወሰንበታል። ውሳኔውንም ሳያቅማማ ይቀበላል። ውሳኔ ብቻ ሳይሆን ቅጣትም ይበየንበታል። የታረደውን ፍየል ፈርስ ከሟት እስከ ፀሓይ ግባት ድረስ ከዝምብ እንዲጠብቅ ይፈረድበታል። እኔ እንደሚመስለኝ የዚህ ተምሳሌት የሰራው ስራ ርካሽ ነውና ርካሽ የሆነውን ነገር እንዲጠብቅ እና ስራውን እንዳይደግመው አመላካች ነው።

በዚህ ብሔረሰብ እምነት መሰረት በላጋኬ የተዘጋጀውን የካላ ስርዓት ሕገ ደንብ ጥሶ የተባለውን ሁሉ አለመፈፀም ጥፋት ያመጣል ተብሎ ይታሰባል። ለዚህ ነው በካላ ስርዓት የቀረበች ሴት በግብረስጋ የተገናኘቻቸው ወንዶች ሁሉ እንድትጠራ የምትገደደው። ካልጠራች የሚወለደው ልጅ ይሞታል ወይ አካለ ስንኩል ይሆናል፤ እንዲሁም ቀደም ብለው ይሁን በኋላ የሚወለዱ ልጆች የሞት እድል ወይም የተረገሙ የመሆን እድል ሊገጥማቸው ይችላል ተብሎ ስለሚታመንና እሷም ስለምታምን ነው። ስለዚህ ለልጆቿ ደህንነት ስትል አንድ በአንድ ትጠራቸዋለች *ብርሃኑ (2000)* ።

በመጨረሻ የካላ ስርዓትን የመሩ ላጋኬዎች የተረገዘው ልጅ የማን እንደሆነ ለተሰበሰበው ህዝብ ያሳውቃሉ። ህዝብም አምኖ ይቀበላል። ውሳኔው ከቀረበ በኋላ ጧት የተጀመረው የካላ ስርዓት ፀሓይ ግባት ሲሆን ያበቃል። ህዝቡም ወደየመጣበት ይመለሳል።

4.3.2.3 ላጋኬና ዕፀኞች

በኩናማ ብሔረሰብ የላጋኬዎች የማውጣጣት ስርዓት የተለያዩ ገፅታዎች አሉት። ሁለቱ ከላይ የተገለፁት ሲሆኑ ሶስተኛው ደግሞ የሚከተለው ነው። የኽውም ባህላዊ መድሓኒት (ዕፅ) ተጠቅመው ሰው ያሳምማሉ፣ ብክንክን እንዲሆን ያደርጋሉ፣ እንዲሁም ለሞት ይዳርጋሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ን ለማውጣት የሚደረግ የማውጣጣት ሂደት ነው። ይህ የማውጣጣት ሂደት ከዜሮ ተነስቶ የሚደረግ ሳይሆን የብሔረሰቡ አባላት ከሆኑት ግለሰቦች በዕፅ ምክንያት የቤተሰባችን፣ የጎሳችን አባል ታሞብናል ተገድሎብናል በማለት ለበቀል መነሳሳት ሲጀምሩና በዚህ መሃል ግጭት ሲፈጠር ነው። በዚህ ጊዜ ላጋኬዎች የአውጫጪኝ ስርዓቱን ሂደት ይጀምራሉ። ስለዚህ ጉዳይ በዓፈው ሰነድ ብርሃነ (2000) እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> ላጋኬ የተፈፀመው እኩይ ተግባር መፈፀሙንና የተፈፀመባቸው ግለሰቦችም ለበቀል መነሳሳታቸው በሰሙ ጊዜ ስርዓቱን ከማካሄዳቸው በፊት ተፈፀመ በተባለው አካባቢ በሚስጥር ጥናት ያካሂዳሉ። ከጥናቱ በኋላም የአውጫጪኝ ሂደት በቦታው እንዲፈፀም ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ ብርሃነ (2000)።

ሽማግሌዎቹ ሚስጢሩን ለማንም ሳያወጡ ከመንደሩ ራቅ ብለው ወደ በረሃ በመሄድ "ገርገጃ"[41] የተባለ ዛፍ በመቁረጥ እንደ ጊዜያዊ በረት መሳይ ይሰራሉ። ስርተው ሲጨርሱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አካባቢውን በጩኸት ብጥብጥ ያደርጉታል። ጩኸቱ ተደብቆ የነበረውን ሚስጥር ማብሰርያና የአካባቢውን ሰው ወደ ተሰራው በረት እንዲሰባሰብ የሚያገለግል ዘዴ ነው። ስለሆነም በየቤታቸውና በየስራ ቦታቸው የነበሩ ወጣቶችና አባዎራዎች ብትር፣ መጥረብያ፣ ጦር፣ ቢላ እና የመሳሰሉትን የብሔረሰቡ የጦር መሳርያዎች በመያዝ ጩኸቱ ወደ ተሰማበት አካባቢ ይተማሉ።[42] ጩኸቱ ወደ ተሰማበት አካባቢ ሲደርሱና የተሰራውን በረት መሳይ ሲመለከቱ፤ ሁሉም "የተጠረጠረ ሰው አለ ማለት ነው" ብለው ስለሚያምኑ በሽማግሌዎቹ የሚሰጣቸውን ትእዛዝ ለመፈፀም ራሳቸውን ያዘጋጃሉ።

---

[41] ይህ ዛፍ ቤት ሲሰራ ለ "ዓምድ" የሚያቆሙት የዛፍ ዓይነት ነው። ለዚህም ነው ለስርዓቱ አገልግሎት ከሌሎች ዛፎች በበለጠ የሆነው። የሁሉም ሰው የቤት ዓምድ ይህ ዛፍ ስለ ሆነ የሚሰጠው አክብሮትና እምነት ከፍተኛ ነው።

[42] እዚህ ላይ ሴቶች ወደ እንደዚህ ዓይነቱ ቦታ እንዲሄዱ የብሔረሰቡ እምነት አይፈቅድም። ምክንያቱም ሴት ሄደች አልሄደች የምትፈይደው ነገር የለም ተብሎ ይታመናል። አዋቂ ወንዶች ብቻ ናቸው የሚሄዱት።

ሽማግሌዎቹም "ሁላችሁም በረቱን እየዞራችሁ ወደ ውስጥ ግቡ" የሚል ትእዛዝ ያስተላልፋሉ። ሁሉም ትእዛዙን በማክበርና የተባለውን በመፈፀም በረቱን እየዞረ ወደ ውስጥ ይገባል። በረቱን እየዞሩ ወደ ውስጥ ሲገቡ ከሽማግሌዎቹ አንዱ ተጠርጣሪዉን ቀይ ዶሮ በመወርወር ይመታዋል። "አርደህና ጠብሰህ ትበላ ዘንድ እንደ ልማዳችን እንደ እምነታችን ልብስህን አውልቀህ ቁም" ይሉታል። የብሔረሰቡ ሕግና ደንብ ስለሆነ ከተሰበሰበው ህዝብ መሃል የተመረጠው ተጠርጣሪ የተባለውን ሁሉ ይፈፅማል፤ *ብርሃነ (2001) አድያቦና (2002)* ።

ተጠርጣሪው የተሰጠውን ዶሮ አርዶና ጠብሶ ከበላ ከተጠረጠረበት ጉዳይ ንፁህ ነው ተብሎ ይታመናል። በባህላዊ መድሃኒት (ዕፅ) ተጠቅሞ ሰው የማሳመም እንዲሁም የመግደል ልማድ ካለው ግን አይበላም። ይህን የሚያደርገው ቤተሰቡ እና በአጠቃላይ ጎሳው ይጠፋሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው። ስለሆነም ለራሱም ለቤተሰቡም ደህንነት ሲል እውነትን አያልፍም። በተጨማሪም የተጠርጣሪው ቤተሰቦች ተጠርጣሪው ወገናቸው በባህላዊ መድሃኒት ሰው የማሳመምና የመግደል ልማድ እንዳለው የሚያውቁ ወይ የሚጠራጠሩ ከሆኑና የተሰጠውን ትእዛዝ ለመፈፀም ከሞከረ ይከለክሉታል፤ ቅጣቱ እነሱንም ይጨምራልና። የማይጠረጥሩት ከሆነ ግን እንዲበላ ያደፋፍሩታል።

ተጠርጣሪው በልቶ ከጨረሰ በኋላ ሽማግሌዎቹ በራሳቸው ስሌት "አራት (4) ወይም አምስት (5) ዓመት ሰጥተነሃል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ከራስህና ከቤተሰብህ ውስጥ ማንም ካልታመመ፣ ካልሞተ ድርጊቱ ያንተ አይደለም። በነዚህ ዓመታት በቤተሰብህና በራስህ የሞት ይሁን ሌላ ክስተት ካጋጠመ በመሃላ እየገባህ ስለሆነ የድርጊቱ ፈፃሚ አንተው መሆንህ ታውቆ ለሚደርስብህ እልቂት የራስህ ችግር መሆኑን እንገልፃለን" ሲሉ የማሳረግያ ውሳኔ ይሰጣሉ።

እንደ አቶ ብርሃነ አገላለፅ፣ በተወሰኑት ዓመታት ከተጠርጣሪ ቤተሰብ በተከታታይ የሞት አደጋ ካጋጠመ እንዲሁም ከሞት ውጪ ሌሎች እንደ ተላላፊ በሽታ፣ የአካል መጉደል ያሉ ክስተቶች ከተከሰቱ ቀደም ሲል በዕፅ የታመመው ወይ የሞተው ግለሰብ የተጠርጣሪው እጅ አለበት ወይ ፈፃሚው ራሱ ነው ተብሎ ይታመናል። የታማሚ ወይ የሟች ቤተሰብም ሁሌም እየፈለጉትና እየዛቱ ይቆያሉ። ጥሩ አጋጣሚ ካገኙም ደማቸውን በደም ሊመልሱ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል። በተጨማሪም ከማሕበረሰቡ እንዲገለል ይደረጋል። በሚያዘጋጃቸው ጉዳዮች እንደ ገዝር እና ሌሎች ድግሶች ተሳታፊ ያጣል። ቤተሰቦቹና በአጠቃላይ የራሱ ጎሳ አባላት

ይጠሉታል ያገልሉታልም። ወንጀሉን ፈፅሞ እያለ ክዷል ተብሎ ስለሚታመን በአካባቢው እምነት ያጣል፤ ስለሆነም ተጠርጣሪውና አጠቃላይ ቤተሰቡ "አመለኛ! አመለኞች!" እየተባሉ ይኖራሉ *ብርሃነ (2001)* ።

4.3.2 ሳንጋኔና

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የግጭት መከሰቻ ምክንያቶች በተለያየ መልኩ አድገው እና ስር ሰደው ወደ ግድያ ደርሰው፣ ግጭቱ እየተባባሰና እየተስፋፋ የደም መመላለስ ቀጥሎ ብሔረሰቡ እንዳያልቅ፣ ሰላም የሚያወርዱበት፣ ግጭቱን የሚቀጨበት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት "ሳንጋኔና"፥ በሌላ አጠራር "የአጥንት አስታራቂ ስርዓት" የሚባል አላቸው።

በኩናማ ብሔረሰብ አራት የተለያዩ ጎሳዎች እንዳሉ በክፍል ሁለት ተጠቅሷል። ከነዚህ አራት ልዩ ልዩ ጎሳዎች ይህ ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት (ሳንጋኔና) የሚያገለግለው ከ"ካላዋ" ጎሳ ነው። ከካለዋ ጎሳ ብቻ የሚሆንበት ምክንያት የመረጃ አቀባዩ እንዳሉት "... የማስታረቅ እውቀት ከጥንቱ ተሰጥቷቸው ስለ ሆነ ይቺ የማስታረቅ ቦታ የነሱ ናት። ማንም ሌላ ሰው አይገባም።" (ገብረንጉስ፣ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 60)። በሌላ መልኩም በግጭት መፍታት ሂደት የሚታመንባቸው እነሱ ብቻ እንደሆኑ ሃይለ ወለላ "... ሳንጋኔና ማስታረቅ የራሳቸው የግላቸው ነው። ስለሆነም ፈላጭ ቆራጮቹ እነሱ ናቸው። ሁለት ሰዎች ሲገዳደሉ የመንግስት ዳኞችም ቢሆኑ ወደነሱ [ሳንጋኔና] ሂዱ። ወደኛ አትምጡ ነው የሚሉት። ከዚያ በቀጥታ ወደ ሳንጋኔና ሄደው ይታረቃሉ እንጂ ወደ መንግስት ሄደው አይክሱም ራሳቸው (ሳንጋኔና) ናቸው የሚያስታርቁት..." (ነሐሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 39) ሲሉ ነግረውኛል። በኩናማ ብሔረሰብ የሳንጋኔናነት ስልጣን የሚገኘው በምርጫ አይደለም ማለት ነው። ከዘር ወደ ዘር የሚተላለፍ ስልጣን ነው። አንድ የሳንጋኔና ስልጣን ያለው የካለዋ አባል ሲያረጅ፤ ኃላፊነቱን ወደ እህቱ ልጅ ያስተላልፋል። ያም እንደዚሁ እያለ ይቀጥላል። ህዝቡም አምኖ ይቀበላል።

ሳንጋኔና ሆኖ አገር ለማስታዳደርና የግድያ ግጭትን በባህላዊ መንገድ ለመፍታትና ዘላቂ ሰላም ለማውረድ አንዱ መስፈርት የካለዋ ጎሳ መሆን እንደሆነ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው መረዳት ይቻላል። ሆኖም ይህ ብቻ በቂ አይደለም። መሟላት ያለባቸው ሌሎች መሰረታዊ ነጥቦች አሉ ይላሉ ታዋቂ የብሔረሰቡ አባላት። ይኸውም አንድ ካለዋ የሳንጋኔና በህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ዳኛ ለመሆን የሚያስችለው አንዱ ዋና ቁምነገር የብሔረሰቡን ባህላዊ መድሓኒት ማወቅ ነው። በተጨማሪም በትዳር ህይወት የሚገኝ ወይም የኖረ፣ ቤተሰቡን በአግባቡና ያለእንከን ያስተዳደረ፣ ምራቁን ዋጥ ያደረገና በአካባቢው ማህበረሰብ ተሰሚነትን ያካበተ፣ ተናግሮ ማሳመን የሚችልና የማያዳግም ፍርድ መስጠት የሚችል መሆን አለበት ይላሉ (ብርሃነ ሃይለስላሴ ሽወለ. መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 99፣ ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 39፣ ገብረንጉስ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 60)።

የሳንጋኔና አባላት በብሔረሰቡ አባላት ዘንድ ታማኝ፣ የተናገሩት መሬት ጠብ የማይል ነው ተብለው የሚታመኑ የግድያ ግጭት አስታራቂዎች ናቸው። ከመታመናቸው በተጨማሪ ሳንጋኔናዎች የረገሙት፣ የጠሉት፣ እና በክፋ ያነሱት በሕይወት የመቆየት ዕድሉ የመነመነ ነው፤ ከብቶቹና ዘሩ ሙሉ የመበታተንና የመጥፋት እንዲሁም የሞት አደጋ ይገጥመዋል፤ የሚል የስነ ልቦና ጫና ተደምሮ በህብረተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ደረጃ ይታመናሉ። ትእዛዛቸውም ይፈፀማል።

ሁለት የተለያዩ ግለሰቦች ሲጋጩና ግጭቱ ከሮ ወደ ግድያ ሲደርስ ከሁለቱም ተጋጪዎች ገዳዩ፣ የግድያ ወንጀሉን ከፈፀመ በኋላ የሚያመራው ወደ ሳንጋኔና መኖርያ ቤት ነው። አንድ መረጃ አቀባዩ "አሁን አንድ ሰው ነፍስ ሲገድል ወደ ሌላ ቦታ አይሮጥም። ወደ በረሃ ምናምን አይታሰብም። በቀጥታ ወደ አስታራቂው ሳንጋኔና ቤት ነው የሚሮጠው።" (ሃይለ ወለላ ነሐሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 42) ሲሉ፤ ደስታ ፋካ የተባሉ መረጃ አቀበዩ ደግሞ "በኩናማ ብሔረሰብ ሁለት የተጣሉ ሰዎች ካሉ [እና] ሞት ካጋጠመ ገዳይና [የገዳይ] ቤተሰቦች ወደ አስታራቂው ቤት ሮጠው ይገባሉ።" ሲሉ አክለውበታል (መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 84)። ገዳይ ወንጀሉን ከፈፀመበት ቦታ ከደም ተበቃዮች እየተደበቀ ወደ አስታራቂው (ሳንጋኔና) ቤት ይገባል ማለት ነው። ሆኖም ሳንጋኔና ቤት ሳይደርስ በመንገድ ላይ እያለ ደም መላሾች ካገኙት ሊገድሉት ይችላሉ። ይህን ሀሳብ የበለጠ ለማጠናከር የመረጃ አቀባዩን ሀሳብ ላቅርብ።

ገዳይ ወደ ሳንጋኔና [ለመግባት] መንገድ ካጣ እና የሚከታተሉት ሰዎች ካሉ በዚያው ወደ በረኻ ይጠፋል። እንደምንም ብሎ ተሟዙሮ፣ በቤተሰብ እርዳታም ይሁን በምንም ብሎ ወደ ሳንጋኔናዎች ካልገባ እና.... የገዳይ ቤተሰቦች በትኩሱ ካገኙት ሊገድሉት ይችላሉ። እሱም ሊገድል ይችላል። ይህ የአጋጣሚ ነገር ነው ማለት ነው (ብርሃነ ሃይለስላሴ ሽወሊ መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 100-101) ።

በበረሃ ተሟዝሮም ይሁን በቤተሰብ እገዛ ሳንጋኔና መኖርያ ቤት ደጃፍ ሲደርስ ደህንነቱን ያረጋግጣል። በሚች ቤተሰብ የሚመጣ የደም መመለስ ሀሳብ ያከትማል። ስለዚህ ገዳይ አንድ መረጃ አቀባዬ "[ወደ ሳንጋኔና መኖሪያ ቤት] እየሮጠ ከገባ በኋላ የሚች ዘመዶች ቢመጡም ምንም ማድረግ አይችሉም። ተመለሱ የሚል እትዛዝ ይከተላቸዋልና ..." (አስመላሽ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 78) ሲሉ ነግረውኛል።

በሌላ መልኩም ገዳይ ወደ ሳንጋኔና ቤት መሄጃ መንገድ አጥቶ በረኻ ጠፍቶ የቀረ እንደሆነ፣ የገዳዩ ቤተሰቦች በሙሉ ተሰብስበው ወደ ሳንጋኔና ቤት ይጠጋሉ። "አንድ [ሰው] ነፍስ ሲያጠፋ ምን ይደረጋል፣ እሱ ነፍስ አጥፍቶ ቢሰወርም ቤተሰቡ ወደምንላቸው ሰዎች (ሳንጋኔና) ቤት ይጠጋሉ። ወደዛ ከቀረቡ ማንም ሰው ወደነሱ አይቀርብም። ነፍስ አጥፍተውብናል ብለው ወደነሱ አይቀርቡም" (ዑስማን ሻዲ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 73)። በተጨማሪም አቶ ገብረንጉስ "ከኛ ጉማዎች አንድን ሽዋ ወይም ካለዋ ከገደለ፣ ያ የሰባት ወር ህፃን ሳይቀር ሁላችን ተሰብስበን ወደ ሳንጋኔና ቤት እንገባለን። እነሱ (ሳንጋኔናዎቹ) ደግሞ ተቀብለው በአንድ ቦታ ያስቀምጡናል። ካስቀመጡን በኋላ ከገደልንባቸው ሰዎች መሃል ትልልቆቹን መርጠው ይዘው ወደኛ ይመጣሉ። እኛ በአንዱ ቤት አለን። እነሱ ደግሞ በአንዱ ቤት አሉ" ሲሉ ገልፀውልኛል (መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 59)።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው፣ የብሔረሰቡ አባላት በአስታራቂዎቹ ያላቸውን ከፍተኛ እምነትና ታዛዥነትን ነው። የሰውን የሚያክል ነፍስ ያጠፋ አንድ ግለሰብ በተጠቀሱት አስታራቂዎች መኖሪያ ቤት ከገባ ብሔረሰቡ ለተቋሙ ያለው እምነት ከፍተኛ ስለሆነ ፊልቶ የመጣው ደም መላሽ ይቀዘቅዛል። ተቀባብሎና ተደቅኖ የመጣው መሳሪያ ዋጋ ያጣል። ተስሎና ተዘጋጅቶ የመጣው ካራ ወደ አፎቱ ይመለሳል። ስለዚህ ገዳይ የአንድ የመረጃ አቀባዬን ሓሳብ ልጥቀስ፣ "ስትጣላ እሳቸው [ሳንጋኔና] ካሉ መጥረቢያ፣ ቢላዋ፣ ብረት አጠገብህ ካለ በፍፁም አታነሳም።

እየተጣላህ እነሱን ካየህ ዘወር ነው ማለት ያለብህ፤ አለበለዚያ ግን ጦሱ ላንተ ነው የሚሆነው" (ዑስማን ሻዲ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 74)። አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ ሸወሊ ደግሞ "ያ የሚታረቀው ሰው [ሳንጋኔ] ወደ ሚኖሩበት አካባቢ እየሮጠ ይገባል። እዛ ሰፈር ከገባ የሚገድለው ሰው የለም፣ ክልክል ነው።... የሆነ ሰው ጥፋት ፈፅሞ ወደነሱ ሲገባ፣ እነሱን ተራምዶ ማጥቃት አይቻልም፣ ክልክል ነው። በባህላችን አይገባም።" ሲሉ ነግረውኛል (መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 100)።

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሙ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ፋይዳ ከፍተኛነት ከፍ ሲል ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል። ሳንጋኔና አውቆም ይሁን ሳያውቅ ብዙጊዜ ሳያውቅ ለገደለ ሰው ጥላ፣ መጠጊያ መማጠኛ ሆና የሚያገለግል ተቋም ነው። የዚህ ተቋም ሂደት በመፅሐፍ ቅዱስ መፅሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 20 ላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ ጋር ይዛመዳል።

የኩናማ ብሔረሰብ ምንም እንኳ የክርስትና ሃይማኖት የተቀበሉት በቅርብ ጊዜ÷ በ1942 ዓ.ም÷ ቢሆንም ከፍ ሲል የተጠቀሰው ባህላዊ ተቋማቸው ግን ከአርብቶ አደርነታቸው ዘመናቸው ጀምሮ አብሯቸው እንደነበር ይታወቃል። ሆኖም የተቋሙ የመጠለያ፣ የመማጠኛ ስፍራ የመስጠት እሳቤው ከብሉዩ መፅሐፈ ኢያሱ ጋር ተመሳስሎ ታይቶኛል። የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት፤

> እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፤ "በሙሴ በኩል በነገርኋችሁ መሠረት የመማጠኛ ከተሞች እንዲሰዩ ለእስራኤላውያን ንገራቸው። ሳያስበው ድንገት ሰው የገደለ ማንኛውም ሰው ወደዚህ በመሸሽ ከደም ተበቃዩ እንዲያመልጥ ከተማዪቱ መጠለያ ትሁን (ኢያ 20፣ 227) ።

ይላል። በኩናማ ብሔረሰብ ያለውን የሳንጋኔና ቤት እንደ መጠለያነት እንደ መጠጊያነት አገልግሎት የመስጠቱ ሂደት፣ ቀደም ባሉ ዘመናት ሽንፈቱን ያመነ ማንም ግለሰብ ሮጦ ቤተክርስትያን በመግባት መጠጊያው ያደርግ እንደነበረ የታሪክ ፀሐፍት የጻፉትን ያስታውሳል። አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የሚከተለው ብለው ነበር።

> ደጃች ጓሉ ከጎጃም ደጃች ኤልያስም ከአገው ምድር ሆነው ዳሞትን ለመግዛትና ደጃች ዘውዴን ለማስገበር ከበቡ። ደጃች ዘውዴ ምንም የታወቁ ገሮግና ቢሆኑ የከበቧቸውን እነዚህን ሁለት ደጃዝማቾች ባንድ ጊዜ ተዋግተው መመለስ እንደማይሆንላቸው ስለተረዱት ጦርነቱን ትተው ደምበጫ ሚካኤል ገብተው ደወሉ። ከዚያም በሊቃውንቱና በቀሳውስቱ ምልጃ ግማሽ የጦር መሳርያቸውን አስረክበው ታርቀው ወዳገራቸው ተመለሱ[43] (1961፡308) ።

የቤተክርስትያን ደወል መደወልና ልክ በሳንጋኔና በመፅሓፈ ኢያሱ የተቀመጠውን ተዛምዶ አላቸው። በኩናማ ወንጀለኛው ጥፋቱን ቶሎ ብሎ ለሳንጋኔና ይናገራል። በመፅሓፈ ኢያሱ የተቀመጠው ደግሞ ጥፋተኛው ለመማጠኛ የተመረጡትን ከተሞች በር ጠባቂ ይናገራል። ደወሉ የቤተክርስትያኑን ሊቃውንትና ቀሳውስት መጥሪያ ሆኖ ያገለግላል። በኩናማዎች እና በእስራኤላውያን እንደሚደረገው ሁሉ ቤተክርስቲያኗም ደወል ደውሎ መጠግያ የጠየቀውን ሰው ታስታርቃለች።

ኩናማ ብሔረሰብም በራሱ እምነትና ልማድ ያቆመው መማጠኛ ስፍራው ሳንጋኔና ቤት ነው። ሰው የገደለ ሰው እንዲጠለልበት እንዲጠጋበት የመሰረተው በህላዊ ተቋሙ ነው ማለት ነው። ይህ ከኦሪት እና ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቤተክርስትያን እንደ መጠጊያነት መገልገል ጋር የሚታየው መመሳሰል ከምን የመነጨ እንደሆነ ግልፅ ባይሆንም።

የኩናማ ብሔረሰብ ጥንተ አመጣጥ ከአክሱምና አካባቢው እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቼን በመጥቀስ በክፍል ሁለት ማቅረቤ ይታወቃል። ክርስትና በፊት በአክሱምና በአካባቢው የኦሪት ስርዓት ይፈፀሙ እንደነበርም የታሪክ ድርሳናት ይጠቅሳሉ። ያም በመሆኑ የኩናማ ብሔረሰብ ይህ ከጥንት እስከ አሁን ከትውልድ ወደ ትውልድ ይዘዉት እየተሸጋገሩ ያሉት ባህላዊ የማስታረቅያና የመጠግያ ተቋም፤ በግልፅ የታወቀ ነገር ባይኖርም ከዚሁ ስርዓት የወረሱት ይሆን? የሚል አስተያየት አለኝ።

ሳንጋኔና ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው እነሱን አምኖና መጠጊያ ፈልጎ ለመጣው ገዳይ ጉዳዩ እስኪጣራ ማረፍያ ሰጥተው እና ከደም ተበቃዮቹ ከለላ ሆነው ያስቀምጡታል። ተከትሎ

[43] አጽንኦቱ የራሴ ነው።

ለመጣው ደም ተበቃይም ‹የምንም አታደርግም!› ያዘለ መልእክትም ትእዛዝም ያስተላልፉለታል።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በዚህ መልኩ ወደ ሳንጋኔና የገባው ገዳይ እና የገዳይ ቤተሰቦች እስከ ዕርቅ ስርዓቱ ድረስ ለሁሉም አንድ ክፍል ተሰጥቷቸው እንዲያርፉ ይደረጋል። ይህ በዘመናዊው መልክ ሲታይ እስርቤት እንደማለት ነው። አጠቃላይ ስርዓቱም ቢሆን ልክ እንደዘመናዊው እስርቤት ነው። ስለዚህ ጉዳይ አንድ የመረጃ አቀባዬ "አሁን እዚህ የተጋደሉም ቢሆን ወደ መንግስት የሚሄድ ማንም የለም። ቤተሰብ የተባለው ሁሉ እዛ ሳንጋኔና ቤት አንገታቸው አቀርቅረው ይቀመጣሉ። ሽንት እንኳ ቢፈለግ ሴቷን በሴት አጃቢ ወንዱ ደግሞ በወንድ አጃቢ ይወጣሉ። ልክ እንደ የፖሊስ ትእዛዝ። በቤታቸው እንደዚህ እያደረጉ ሳምንት ይቆዩና ከሳምንት ቦኋላ ያስታርቁዋቸዋል።" ሲሉ ነግረውኛል (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 47)። ከሳምንት በኋላ የእርቅ ስርዓቱን ለመጀመር የጉዳዩን መንስኤ ለማወቅ ያስችላቸው ዘንድ የማጣራት ስራ ያከናውናሉ። የማጣራት ሂደቱ የሚጀመረው ከገዳይና ቤተሰቡ ለግድያ ያዳረሳቸው ጉዳይ ምን እንደሆነ በመጠየቅ ነው። ስለዚህ ጉዳይ መረጃ አቀባዬ የሚሉት አላቸው፣ "አስታራቂው እኛ ጋር (ከገዳይ ቤተሰቦች) መጥተው አሀ ግጭቱ በምን ተነሳ? የአጋጣሚ ነው? በሴት ነው? በአሉባልታ ሀሜት ነው? ብለው እኛን ጠይቀው ነገሩን ሁሉ አይተው በቃ እነሱ ዕርቅ ሊፈፅሙ ሲቀራረቡ እነዛ ጎበዞች እኛ ደም እንመልሳለን የሚሉ ሁሉ አያቀርቧቸውም።" (ገብረንጉስ መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 59) ። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምንም ሳንጋኔናዎች ጉዳያቸው አይደለም። የግጭት መንስኤውንና ሂደቱን ለማወቅ እንጂ። ስለሆነም ሃይለ ወለላ "አሁን ራሱ ቀስ ብሎ የሚላኩ ሽማግሌዎች ይይዛል" እንዲሉት (ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 43)። ከገዳይ እና ቤተሰቡ ያጣሩት ሳንጋኔና በቀጥታ ሶስት መልዕክተኛ ሽማግሌ መምረጥ ይጀምራሉ።

በሳንጋኔና ለመልእክተኝነት የሚመረጡት ሽማግሌዎች ራሱን የቻለ መስፈርት አላቸው። የንግግር ክህሎታቸው የዳበረ፣ ሰው እንዲፋቀር እንጂ እንዲጣላ ፍላጎት የሌላቸውና ዋሽተው የማያጣሉ፣ "ዋሽተው" የሚያስታርቁ እንዲሁም የሄዱበትን ጉዳይ ሳይፈፅሙ ወደ ኋላ የማይመለሱ ሰዎች መሆን አለባቸው። ይህንን መስፈርት ራሱ ሳንጋኔናው ያውቀዋል (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 45)። ስለሆነም መስፈርታቸውን አይቶና መዝኖ ይመርጣቸዋል።

በሳንጋኔና የተላኩት ሽማግሌዎች ወደ ሚች ቤተሰብ በመሄድ እንዲታረቁ ሰላም እንዲያወርዱ በሳንጋኔና እንደተጠየቁ ይገልፁላቸዋል። ሆኖም ምንም እንኳን በአስታራቂው ያላቸው እምነት ከባድ ቢሆንም በአንድ ጊዜ አይቀበሉም፤ ያንገራግራሉ። ሽማግሌዎቹም በተደጋጋሚ በመመላለስ እሺ ለማሰኘት ይማፀኑዋቸዋል። የተመረጡትም የማስፈፀም ብቃት አላቸው ተብሎ ታምኖባቸው ነው።

የተላኩት ሽማግሌዎች የደም ተበቃዮችን እሺታ ሲያገኙ ወደ ላካቸው ሳንጋኔና ተመልሰው "እነዚህ ሰዎች ወደ ልባቸው ተመልሰዋል ሊታረቁ ፈልገዋል።" ብለው ሲነግሩት "በሉ አቅርቧቸው" የሚል መልስ ይሰጣቸዋል። እነሱም ያቀርቧቸዋል። ለገዳዮች ቤተሰብም "በሉ እናንተም ሰው ገድላችኋልና የደም ካሳችሁን ይዛችሁ ታረቁ" ሲል ሳንጋኔና ያዛል።

የዕርቅ ስርዓት ሂደቱ ከመፈፀሙ በፊት የሚች ቤተሰቦች ምን ያህል የደም ካሳ እንደሚያስፈልጋቸው በሳንጋኔና በኩል ይጠየቃሉ። ሆኖም ከሳንጋኔናው ስርዓትና ሕግ ውጪ አይጠይቁም። የተቆረጠና የተወሰነለት፣ በሳንጋኔናው የሚታዘዝ የደም ካሳ አለና ነው። "የደም ካሳውም ቢሆን ራሱ [ሳንጋኔና] በጅቶ አስቀምጦታል። እነሱ ከሕግና ስርዓቱ አልፈው ቢጠይቁ፣ "ህጋችን የሚፈቅደው ይህ ነው። ህጋችንን ትታችሁ ወዴት ወዴት በራችሁ ትሔዳላችሁ" ሲል ይገድባቸዋል (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 44)።

በሳንጋኔናው ትእዛዝ መሰረት የደም ካሳው ይወሰናል። የደም ካሳ ቁርጥ ያለ አይደለም። ሆኖም በአብዛኛው ጊዜ አንድ ህይወት የሚሰላው በከብት ነው። ይህም ለአንድ ነፍስ የሚከፈለው የደም ካሳ 16 ከብት ነው። በሌላ መልኩም አራት ፍየል እንደ አንድ ከብት እየታሰበ ተባዝቶ የሚከፈልበት አጋጣሚ ይኖራል። እንዲሁም አንድ ደርዘን አቡጀዲ እንደ አንድ ከብት ታስቦ ይሰጣል። በተጨማሪም ገዳይ የሚጠቀምባቸው የእርሻ መሳርያዎች፣ የጦር መሳርያዎችና ሌሎች ተሰብስበው እንደ አንድ ከብት ታስበው የሚከፈልበት ሁኔታ እንዳለ (ደስታ ፋካ መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 84፣ ብርሃነ ሃይለስላሴ ሽወሊ መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም÷ ስክርብ ገፅ 101) ይገልፃሉ።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሳንጋኔና በዚህ መልኩ የገዳይ ቤተሰቦች የደም ካሳውን እንዲያዘጋጁ ትእዛዝ በመስጠት ዕርቅ የሚፈፀምበትን ቀን ይቆርጣሉ። የቀኑ ጉዳይ ባመቻቸውና በተስማሙበት ቀን ሊሆን ይችላል። የቀን ገደብ የለውም።

ሳንጋኔና የዕርቅ ስርዓት የሚፈፅሙበት ቀን ሲደርስ ህዝቡ ሁሉ ሰፊ ሜዳ ላይ እንዲሰባሰብ ያደርጋሉ። ለደም ካሳ እንዲከፈሉ የተዘጋጁት ከብቶችም እሜዳው ላይ ይሆናሉ። ሳንጋኔናዎች የዕርቅ ስርዓቱን ለመመልከት በተሰበሰበው ህዝብ መሃል በመቆም፣ በብሔረሰቡ እምነት መሰረት የምርቃትን እና ዕርቁ የተሳካ እንዲሆን ፈጣሪያቸውን የሚማጸኑበትን ልመናን አስቀድመው፤ የዕርቅ ስርዓቱን መጀመር ለህዝቡ ይገልፃሉ። የተሰበሰበው ህዝብና ለመታረቅ የተዘጋጁት ጠበኞች "አሺባ" (አሜን እንደማለት ነው) እያሉ ይቀበሉዋቸዋል። ባይቀበሉዋቸው የርቃቱና የዕርቁን ስርዓት መሳካት የሚያሳይ ልመና ትርጉም አይኖረውም ተብሎ ስለሚታመን ሁሉም በአንድ ድምፅ ይቀበላቸዋል።

ዎ ...ኦዋ ...ኣዱ[44]

ዎ ... ኣምላክ [ፈጣሪ]

ድንጉል ማሽኮል[45]

ዎ... ድንግል [ፈጣሪ]

ጋላዳ ሊዳ

በተቻለህ መጠን አግዘን

ስሌካዳ ሊዳ

ጎንበስ ብለህ ተመልከተን

ላጋ ጋንጃላ ፋሉማ

በዓለም ቅናት ምድር

ማላ ሺሺማ አውኪዳ

ሰላም ዕርቅ አድርግልን

ሃበማ ኪና ኩንዳ ናምናቢናቦኮ

የታራቂዎችን ልብ አራራልን

ቶኮና ዳጋ ሙሉያ ቶኮና ማፈጌዳኮ

ከቀኝ ወደ ግራ አስኪደን

---

[44] እስከአሁን ሲቀርብ የነበረው በትግርኛ የተገኘው መረጃ ሲሆን፤ ስለ የዕርቅ ስርዓት መጀመር ማብሰርያ ምርቃት እና ዕርቁ የተሳካ እንዲሆን የሚደረገው ልመና ግን በኩናምኛ ቋንቋ የተገኘ ሆኖ አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ የተረጎሙት ነው። በተሰበሰበው ህዝብ መሐል ቆመው መመረቅ ሲጀምሩ ህዝቡም "አሺባ" "አሜን" እያለ ይከተላቸዋል።

[45] የደመቀው ኩናምኛ ቋንቋ ሆኖ በግዕዝ ፊደላት የተፃፈ ነው።

ጌጋ ዳጋ ሙሉያ ቶኮና ማፈጌዳኮ

ባለንበት ሁሉ ጠብቀን

አሜታ ሊሉማ ካሲያ ከኮባ ማፈገዳኮ

እኛን በክፋ የሚመለከት ዓይኑ ይጥፋ

ሃያ ላዋሉም ዋይያ ማማለክ

መጥፎ የሚያስብልን ዓይኑ ይደፈን

ዎ ድንጉል ማሽኮል

ዎ... [ፈጣሪ] ኩሉ ዓለም

ጋላዳ ካንቲ

ተመልከተን

አማላ ሉሉማ ካዋ

ምኞታችንን ላሳካልን

አይኳሉ

ለልጆቻችን

አጋራሲ

ለህዝባችን

ዳርካኜሲ

ለሚስቶቻችን

ዶዳኜሲ

ለልጆቻችን

ናተባኜሲ ማይዳሙ

ለሁላችን በሰላም አኑረን

አራሲ ካኪ

የጀመርነው ፍፃሜውን ወደ ብርሃን አድርሰው

አሼባ

አሜን

(ብርሃነ፡ 2001:6-7)

ሊሉ ለህዝቡ የዕርቅ ስርዓቱን መጀመር የሚያበስር ምርቃት ይሰጣሉ።

ከዚያም "ደም ሳይፈስ ስርየት የለም" እንዲል (ዕብ 9፡21) ለደም ካሳ ከተዘጋጁት አስራ ስድስት (16) ከብቶች መካከል የገዳይ አጎት[46] (የእናት ወንድም) ያመጣውን አንድ ከብት በገጀራ አንገቱን እንዲቆርጥ ይደረጋል። የተቀሩት 15 ከብቶች ለሟች ቤተሰብ እንዲሰጡ ይሆናል ብርሃነ (2001፡3)።

በሚዳው የተቀመጠው ህዝብ ክብ ክብ እየሰራ የታረደውን ስጋ እያበሰለ ይመገባል። በዚህ መሐል የተጋጩት የገዳይና የሟች ቤተሰብ እንዲቀርቡ በማድረግ ከነሱ ውስጥም ከገዳይ ቤተሰብ ገዳዩን ጨምሮ አራት፣ ከሟች ቤተሰብም አራት[47] ምራቃቸውን ዋጥ ያደረጉ ሰዎች በመምረጥ ግራና ቀኝ ያስልፏቸዋል። ቀጥለውም በተነጠፈ ሰሌን አንድ ላይ እንዲቀመጡ ይደረጋል (መድህን ከሊ. መስከረም 14፣ 2003 ዓ.ም፡ ገፅ 64) ።

በተነጠፈው ሰሌን ላይ ተቀምጠው በአንድ ሰፊ ድ የበሰለ ስጋ ይሰጣቸዋል። አንድ ላይ ይመገባሉ። መረቁንም አብረው ይጠጣሉ (ባህር ጀዕፈር መስከረም 15፣ 2003 ዓ.ም፡ 107)። በእኔ አስተያየት በአንድ ሰሌን የመቀመጣቸውና በአንድ ሰፊ ድ መመገባቸው የአብሮነት፣ ወንድምነት፣ ትስስር እንዲኖራቸው የሚያመላክት ነው። ስለሆነም ያለምንም ፊት መንሳት በሳንጋኔና ተነጥፎ በተሰጣቸው ሰሌን ተቀምጠው አድርጉ የተባሉትን ሁሉ በሕብረት ያደርጋሉ። ህዝቡም በመብላትና በመጠጣት እንዲሁም በእልልታ ያጅባቸዋል።

ከመብሉና መጠጡ በኋላ ሳንጋኔናው ተነስተው፡-

ከራማ ካራማ[48]
ካራማ ታል ፋራ
ካራማ ታል አነቢ

[46] አጎት (የእናት ወንድም) በብሔረሰቡ ከፍተኛ ቦታ አለው።

[47] አራት አራት የሚመረጥበት ምክንያት አራቱም የኩናማ ጎሳዎች እንዲወክሉ ታስቦ ነው።

[48] "ካራማ" መስዋዕት የሚለው የአማርኛ ቃል ይተከዋል። ስለሆነም አጠቃላይ ትርጉሙ የሰዋነውን መስዋዕ ተቀበለን መርቅልን እንደማለት ነው ሲሉ ዑስማን ሻዳ ነግረውኛል።

እያሉ ከፀለዩ በኋላ የመብል መጠጡን ስርዓት ዘግተው ወደ ቀጣዩ የዕርቅ ስርዓት ሂደት ያመራሉ ብርሃነ (2001) ::

ከመብል መጠጡ ስርዓት ማሳረግያ ምርቃት በኋላ፣ አስታራቂው ሽማግሌ (ሳንጋኔና) የሚች ቤተሰቦችንና የገዳይ ቤተሰቦችን የማስታረቅ ሂደት የመጨረሻ ክፍል፤ ተጋጪዎች ከታረደው ከብት አንድ ቅልጥም እንዲፍቁና በደንብ እንዲጠርጉት በማዘዝ ይጀምራሉ። እነርሱም የተሰጣቸውን ቅልጥም ጥርግ አድርገው ፍቀው ከስጋ ነፃ የሆነ አጥንት ያደርጉታል። ከስጋ ነፃ የሆነው አጥንት ለሁለቱ ቤተሰቦች እንደ ማስታረቂያም እንደ ቃለመሀላም ሆኖ የሚያገለግል ነው። ስለዚህ ጉዳይ መረጃ አቀባዮቼ የሚሉትን ላቅርብ።

> ... የቅልጥሙን ስጋ በደንብ አድርገው አጥርተው ይበሉታል። ከዚህ በኋላ ሳንጋኔናው፥ ህዝብ ተሰብስቦ በተቀመጠበት ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ...ትንሽ ጉድጓድ ቆፈር ቆፈር አድርገው ቅልጥሙን ያጋድሙታል። ከዚያ ትንሽ ጠጠር በማንሳት *(አስታራቂው ራሱ ለራሱ የሚፀልየው ፀሎት ፀልዮ፤ ጠጠሩን የሚቀባበት ባህላዊ መድሓኒት ቀብቶ)* የያዛት ጠጠር ቀስ አድርጎ ወርወር ያደርጋታል። አጥንቷም ስብር ትላለች።[49] ቀጥሎም "በሉ እዚህ መጥታችሁ ማሉ ከናንተ መካከል ወንድሜን ወገኔን ገደልክብኝ ብሎ ሰው ለመግደል ያሰበ እንደዚህ አጥንት ይሰበር ይላል"። እነሱም ይደግማሉ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ስክርብ ገፅ 44)።

የአጥንቱ መሰረታዊ ትርጉም፣ በተጋጪዎች ሁለተኛ ግጭት እንዳይከሰት ከተከሰተም የግጭቱ ጀማሪ ግለሰብ እንደ አጥንቱ እንደሚሰበር ቃለመሃላ፣ እንዲሁም ማስፈራርያም ማስታረቂያም ሆኖ የሚያገለግል ነው። በሌላ መልኩም ከአንድ አጥንት ስጋ መብላታቸው ወንድማማችነታቸውና ወዳጅነታቸው እንዲዳብር የሚያመለክት ሲሆን፣ ከበሉት በኋላ እንዲሰበር መደረጉ ደግሞ በክፋ ብትተሳሰቡ፣ ደም እመልሳለሁ የሚል ሃሳብ በውስጣችሁ

---

[49] ለአጥንት መስበርያ አገልግሎት የሚውለውን ባህላዊ መድሓኒት [ሳንጋኔናዎች] ብቻ ናቸው የሚያውቁት። እርስ በራሳቸው ይቀባበሉታል እንጂ ማንም አያውቀውም (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ገፅ 46)። ለዚህም ነው ሳንጋኔና ለመሆን ባህላዊ መድሓኒት ማወቅ እንደ አንድ መስፈርት የተወሰደው። የሽማግሩ ሂደትም፤ ሳንጋኔና ሲያረጁ ስልጣናቸውን እና የሌሎቹ ባህላዊ መድሓኒት እውቀታቸው የሚያስተላልፉት ለእህታቸው ልጅ ነው። ከልጃቸው እንኳን አትሆንም። በብሄረሰቡ የእህት ልጅና የእናት ወንድም ጥብቅ የሆነ ትስስር አላቸው። ይህ ትስስር ሊመነጭ የቻለው ኩናማ በጥንት ጊዜ አንድ ልጅ በእናቱ ነበር የሚጠራው፤ ከየትኛው አባወራ እንደተወለደ አይታወቅምና *(ስለዚህ ሀሳብ በብሔረሰቡ የግጭት መከሰቻ ምክንያቶች በሚለው ንኡስ ርእስ ተገልጧል።)* ነው። ስለሆነም ከየትም ይወለድ ከየት ም የእህት ልጅ ተብሎ ስለሚጠራ የበለጠ ትስስር የፈጠረላቸው ይመስለኛል።

ብታሳድሩ አጥንታችሁ ይሰበራል፤ የሚል መልእክት ያቀፈ እንደሆነ የብሔረሰቡ አባላት ይናገራሉ።

በዚህ መልኩ የተሰበረው አጥንት የበለጠ ወንድማማችነታቸውንና ወዳጅነታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ሲባል፣ በአጥንቱ ውስጥ ያለው መቅን ከሚችና ከገዳይ ቤተሰብ የተመረጡት ሰዎች ደረታቸውን እንዲቀቡ ይደረጋል። አንድ መረጃ አቀባዬ እንደነገሩኝ፦

> ...አሁን ሳንጋኔና ቅልጥሚን ስብር አድርገው በውስጡ የሚገኘው መቅን ሳብ አድርገው አውጥቶትንሽ እዚህ ጋር (ደረታቸው ሰፍተው እያሳዩኝ) ደረቱ ጋር ይቀባዋል። ሁለቱንም ታራቂዎች ማለት ነው። ከዚያ ሁለት ሁለት እየሆኑ ደረት ለደረት ይነካካሉ። በመቀጠል "ወንድሜ ነህ ወንድሜ ነህ ምንም አልልህም ምንም አትለኝም ሁለታችን ወንድማማቾች ነን። ቂም በቀል የሚባል ነገር [ይብቃ።] በአንድ መአድ በልተናል፣ ለወደፊቱም እንበላለን። እንዲሁም በረሃ ይሁን በመንደር አንድ ላይ ነን። ሰውነቴን ትጠብቅልኛለህ ሰውነትህን እጠብቅልሃለው" ተባብለው በቃ አለቀ በዚህ ይጨርሳሉ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም፥ ገፅ 45) ።

ከአጥንቱ መሰበር እና ከመቅን መቀባት በኋላ በብሔረሰቡ ባህላዊ ሕግና ስርዓት መሰረት ለቂም በቀል መነሳት፣ በክፋ መተሳሰብና ደም ለመመለስ መሞከር ውጉዝ ነው። ከመወገዙም አልፎ በዕርቁ ስነ ስርዓት ላይ የተነገረው "ትሰበራለህ" የሚል መሸምገያም ማሰፈራርያም ትልቅ ቦታ እና እምነት ስላለው በፍፁም አይሞክርም። እንደ ወንድም እንደ ወዳጅ ተያይተው አብረው ውሃ ይቀዳሉ፤ አብረው እንጨት ይለቅማሉ። ከዕርቅ ስርዓት በኋላ ያለው ሰላምና መግባባት ምን እንደሚመስል በከፊል የሚያመለክት ቀደም ብሎ የተፈፀመን የዕርቅ ስርዓት አጭር ታሪክ አንድ የመረጃ አቀባዬ ነግረውኝ ነበር።

> አሁን... ሀበሻ ሆነን ክርስትያን ከሆንን በኋላ ሁለት ሰዎች በሴት ተገዳደሉ። እና ያ የገደለው ሰው አስረው ወደ ሽሬ ወሰዱት። ከዚያ ግን እነዛ እቤት የቀሩት የገዳይ ቤተሰቦች የሰባት ወር ህፃን ሳይቀር በሙሉ ተሰባስበው ከዚህ (ከሽራሮ) ወደ ኤርትራ ሄዱ። ያ የባህላዊ እርቅ ስርዓት የሚፈፅመው ሳንጋኔና ኩናማችን የሚያስታርቅልን ሊያስታርቅ ወደ ኤርትራ ሄዶ ስለነበር ከዚህ ሁሉም ተሰባስበው ወደ ኤርትራ ወረዱ።

እዛው ታርቀው የደም ካሳቸውም ከፍለው ተመለሱ። የታሰረውም መጥቶ አሁንም ቢሆን አሉ አብረው እየኖሩ ነው። የሚኝ ቤተሰብና የገዳይ ቤተሰብ አሁንም አሉ አንድ ላይ ተቀምጠው ይበላሉ ይጠጣሉ (ሃይለ ወለላ ነሓሴ 20፣ 2002 ዓ.ም÷ ገፅ 41)። [50]

ሲሉ ገልፀውልኛል።

በአጠቃላይ፥ በኩናማ ብሔረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች የተከሰቱትን ግጭቶች፤ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓት አማካኝነት እንዴት እንደሚያስወግዱ በተገኘው መረጃ መሠረት ቀርቧል።

[50] ይህን ቃለ መጠይቅ ያደረኩት የብሔረሰቡ አጠቃላይ ስብሰባ በነበረበት ወቅት ነበር። ስለሆነም ታረቁ የተባሉት ቤተሰቦች (የልጅ ልጅ ልጅ) አቦይ ሃይለ አሳይተውኛል። ሆኖም ስለዚህ ጉዳይ መጠየቅም ሆነ ማንሳት እንዳማይቻል መረጃ አቀባዬ አስቀድመው አስጠንቅውኝ ስለ ነበር አልጠየኳቸውም።

5. ማጠቃለያ

ኩናማ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች (ethnic groups) አንዱ ነው። የብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ ከአክሱምና አካባቢው ሆኖ፥ አባላቱ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ እና በኤርትራ ይገኛሉ።

ብሔረሰቡ ስያሜውን ያገኘው አንድም ከንግስታቸው ከንጉስ ባዜን ባለቤት ስም "ኩናሜ" ከሚለው ሲሆን፤ አንድም ደግሞ በወቅቱ ሲደርስ ከነበረው ተደጋጋሚ ጦርነት "ዘወር ምበልኩ ምሐሸ" (ዞር ብል ይሻለኝ ነበር) ከማለት የመጣ እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል።

ኩናማ የበርካታ መንፈሳዊና ቁሳዊ እምነቶችና ልማዶች ባለቤት ነው። እነዚህን እምነቶችና ልማዶች በአካባቢው በሚኖሩ ሌሎች ብሄረሰቦች ሳይበገር የቻለውን ያህል ከትውልድ ትውልድ ሊያስተላልፋቸው ቆይቷል። በአሁኑ ጊዜ ግን በአካባቢው ህዝብ ተዕእኖም ይሁን ከስልጣኔ ጋር በመቀራረቡ አንዳንድ ጠቃሚ ስርዓቶቹንና ልማዶቹን በመተው ላይ እንደሚገኝም ከጥናቱ ለመረዳት ይቻላል። ለምሳሌ ያህል የ "ላጋኬ" ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ተጠቃሽ ነው። እስከ አሁን ድረስ ከሚገለገልባቸው በርካታ ስርዓቶቹ ደግሞ "ባህላዊ የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት" ዋነኛው እንደሆነ የጥናቱ ግኝት ነው።

ይህ ጥናት በኩናማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም የኩናማ ብሔረሰብ የግጭት ብያኔ፣ ዋና ዋና የግጭት መነሻ ምክንያቶች ክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊትና በኋላ ያላቸው ልዩነት፤ እንዲሁም ባህላዊ የዕርቅ ስርዓታቸው ምን እንደሚመስል በዚህ ጥናት ለማሳየት ተሞክሯል።

ስለ ግጭት ብያኔ፣ ስለ ዋና ዋና የግጭት መነሻ ምክንያቶች ክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊትና በኋላ፤ እንዲሁም ስለ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓታቸው አጠቃላይ ሁኔታ፤ በባህልና ታሪክ ዕውቀታቸው እንዲሁም በአስታራቂነታቸው በአካባቢው የተመሰከረላቸው የሀገር ሽማግሌዎች፣ ገበሬዎች፣ "የቤት እመቤቶች"፣ ከወረዳው የመንግስት ሀላፊዎች ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት በማካሄድ እንዲሁም ክልዩ ልዩ ሰነዶች እና መፅሔቶች መረጃዎች ተሰብስቧል።

የኩናማ ብሔረሰብን ወደ ግጭት ከሚያስገቧቸውና ለግድያ ግጭት ከሚያደርሷቸው ምክንያቶች÷ ክርስትናን ከመቀበላቸው በፊት÷ ከኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ከእለት ተእለት ኑሮ ጋር የተሳሰሩ ሲሆኑ፤ ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ ደግሞ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው "በትዳር ላይ መወሰለት" ዋነኛው የብሄረሰቡ መገዳደያ እንደሆነ ከጥናቱ ለመረዳት ተችሏል። የተከሰቱት ግጭቶች ስር ሰደውና ተስፋፍተው የከፋ አደጋ እንዳያደርሱ የሚከላከሉበት ብሎም ዘላቂ ሰላም የሚያሰፍኑበት ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት እንዳላቸውም በጥናቱ ለማሳየት ተሞክሯል።

ቀላል የሚባሉ ግጭቶችን የሚፈቱ "ላጋኬ" ወይ መንደር ቆርቋሪዎች የሚባሉ የሀገር ሽማግሌዎች ሲሆኑ፤ "ሳንጋኔና" ወይ የአጥንት አስታራቂዎች ተብለው የሚታወቁት የሀገር ሽማግሌዎች ደግሞ የግድያ ግጭትን የሚፈቱ ናቸው። ላጋኬ ቀላል ለሚባሉ ግጭቶች ዘላቂና ፍትሃዊ የሆነ ብይን እንደሚሰጡ በብሔረሰቡ የታመኑ መሆናቸውንና ከፍርዳቸውም ንቅንቅ የሚል እንደሌለ፤ የግድያ ግጭትን በተመለከተ ደግሞ÷ ከገዳይ ቤተሰብ እና ከሟች ቤተሰብ አራት አራት በመምረጥ ዳግመኛ ወደ ግጭት እንዳይመለሱ በመለመን (በማስፈራራት)፤ ስርዓታቸው የሚያዘውን የዕርቅ ስርዓት በመፈፀምና መሃላ በማስፈፀም፤ እንዲሁም ለሟች ቤተሰብ ከገዳይ ቤተሰብ የደም ካሳ በአግባቡ በማስከፈል ረገድ ሳንጋኔና ያላቸው ሚና በጥናቱ ተመልክቷል።

የብሔረሰቡ አባላት በባህላቸውና በእምነታቸው መሰረት ከትውልድ ትውልድ ሲረካከቡት የመጡትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ከዘመናዊ ፍርድ ቤት በበለጠ እንደሚያምኑና እንደሚመርጡ ጥናቱ አሳይቷል።

ኩናማ ብሔረሰብ ለሳንጋኔና፤ ለላጋኬ አስተራቂዎች እንዲሁም በሳንጋኔና ባህላዊ መድሐኒት ተቀብቶ ለመሃላ ለሚሰበረው አጥንት እና ከአጥንቱ ለሚወጣው መቅን ከፍተኛ እምነት እንዲሁም ፍራቻ ስላላቸው ሁለት የታረቁ የብሄረሰቡ አባላት ዳግመኛ ወደ በቀል የሚያመሩበት ሁኔታ አይፈጠርም። ይልቁንስ ተሳስበውና ተከባብረው እንዲኖሩ እንደሚያስገድዳቸው በጥናቱ ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

6. ይሁንታዎች

ይህ ጥናት "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው። ስለሆነም፣ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት ከታዩ ሁኔታዎች በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል።

- ኩናማ ብሔረሰብ በአከባቢው ካለው ማሕበረሰብ አንፃር አነስተኛ ቁጥር ያለው ብሔር በመሆኑ በሌላው ብሔር እየተዋጠ ያለ ህዝብ ነው። ስለሆነም ቀደም ሲል ሲገለገልባቸው የነበሩትን በርካታ እምነቶችና ልማዶች እንዲሁም ቋንቋው እየተዋጡና እየጠፉ ይገኛሉ። የብሔረሰቡ ህፃናት የሚማሩት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሳይሆን በትግርኛ፣ የመንግስትና ሌሎች ስብሰባዎች የሚከናወኑት በትግርኛ፣ ገበያ ሲገበያዩ የሚጠቀሙበት ቋንቋ ትግርኛ፣ እምነትና ልማዶቻቸው እንደ አሳፋሪና አስነዋሪ ስራ እየታዩ የሌላውን ብሔር አሰር በመከተል ላይ ናቸው። ስለዚህ የዚህ ብሔረሰብ እምነትና ልማድ እንዲሁም አጠቃላይ ባህሉና ቋንቋው ከትውልድ ትውልድ እንዲሸጋገር የሚመለከተው አካል በተለየ መንገድ ሊታደገው እና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

- የኩናማ ብሔረሰብ አባላት ተከባብረው የሚኖሩት ባህላዊ ህጋቸውን በማክበር (በመፍራት) ነው። ከመንግስት ዘመናዊ የፍትሕ አካላት አሰራር በበለጠ ባህላዊ ደንባቸውን ይመርጣሉ። ይተዳደሩበታልም። ስለሆነም የአከባቢው ዘመናዊ የፍትህ አካላት ለባህላዊው የግጭት መፍቻ ተቋም እና አባላቱ እውቅና በመስጠት ራሱ የቻለ በጀት እንዲኖራቸው ቢያደርጉ፣ እንዲሁም በየጊዜው የሚፈቱዋቸውን ግጭቶች ሪፖርት እንዲያደርጉ ግንዛቤ ቢሰጡዋቸው፣ ለባህላዊው የግጭት መፍቻ ተቋም ዕድገትና ዘላቂነት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል።

- ብሔረሰቡ በባህላዊ መድሐኒት የታወቀ እንደሆነ ተገልጧል። ሆኖም ለነዚህ ብሔረሰቦች በአካባቢው የሚገኙ ትግርኛ ተናጋሪ ህዝቦች ጥሩ ስም አይሰጧቸውም። "ቅጠል በጣሽ"፣ "ስር ማሽ" የሚሉ ስያሜዎች ይሰጧቸዋል።

በዚህ ምክንያትም ለባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓታቸው ማስረገጫ ሆኖ የሚያገለግለውና ለዘመናዊው የመድሐኒት ቅመማ መሰረት የሆነውን ባህላዊ መድሐኒት (Folk Medicine) እንዲተዉት ብሎም እንዲረሱት፤ እንዲሁም ለዕርቅ ስርዓቱ መዳከም ምክንያቶች ናቸውና የአካባቢው ህብረተሰብ በመልካም ጎኑ ቢመለከተው ለባህላዊ መድሐኒቱ ዕድገት እንዲሁም ለባህላዊው የዕርቅ ስርዓት ቀጣይነት ወሳኝነት አለው።

- የብሔረሰቡ ሴቶች በብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ከቁጥር የማይገቡ ሰዎች ተደርገው ይወሰዳሉ። ለምሳሌ፦ በባህላዊ የዕርቅ ስርዓቱ ምንም እጅ የላቸውም። ስለሆነም የኩናማ ብሔረሰብ አባላት ይህንን አስተሳሰብ አስወግደው የሴቶችን መብት የጠበቀና ተሳትፏቸውን ያካተተ ስራ መስራት እንዳለባቸው የግንዛቤ ሀሳብ ቢሰጣቸው መልካም ይሆናል።

- ይህ ብሔረሰብ የበርካታ ባህላዊ ስርዓቶች ባለቤት መሆኑ ተጠቅሷል። ሆኖም እነዚህ ልዩ ልዩ ስርዓቶች የዚህ ጥናት ትኩረት ባለመሆናቸው እዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም። ስለዚህ ሌሎች በዚህ አካባቢ መስራት የሚፈልጉ አጥኚዎች ይህን "ተቀድቶ የማይነጥፈውን ባህል" ቢያጠኑና ወደ አካዳሚያ ቢያመጡት ብሔረሰቡን በማስተዋወቅና ባህሉን አቅቦ እንዲይዝ በማበረታታት ጉልህ ድርሻ ይኖራቸዋል። ይህ ሀሳብ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ በልዩ ልዩ መጻህፍትና መጣጥፎች ሲጽፉት የነበረ ነው። ለዚህ ብሔረሰብ ጠቃሚ ይሁንታ ሆኖ ስላገኘሁት በራሴ አገላለጽ በመጭመቅ ተገልግዬበታለሁ።

ዋቢ መፃህፍት (References)

Aleme Eshet. "**Whose History Is Ethiopian History**?". Addis Ababa University, International Symposium on History and Ethnography in Ethiopian Studies. (Organized In Collaboration With the Italian Cultural Inst.), Nov. 18-25: 1982.

Natty, Alexander **"The Impact of Euro- Christian mission of Kunama Traditional Culture**." M.A Thesis, Addis Ababa University. 1982.

_____, **Elders And Juniors In The Kunama Society**. Addis Ababa University, International Symposium on History and Ethnography in Ethiopian Studies. (Organized In Collaboration With The Italian Cultural Inst.), Nov. 18-25: 1982.

Aster Zewdie. "**The Ethio-Nilo Saharans**". M.A Thesis, Addis Ababa University, 1981.

AllWood, J. Hultebg (Ed.). "**Types of Conflict and Conflict Handling: An Academic Seminar**." New Genres in Science Studies, Dep. Of The Theory of Science, University of Gutenberg, 1993.

Bender M.L and Et Al (Eds.) **Language In Ethiopia**. London: Oxford University Press, 1976.

Bohannan, Paul. (Ed.) Introduction **Law and Warfare: Studies in the Anthropology of Conflict**. Austin: University Of Texas Press, 1967.

Cittadini, M. "**The Kunama and Marriage Ceremonies: A Kunama Marda Marriage**" A Paper Prepared In Advance for the Interdisciplinary Seminar of the Faculties of Arts and Education, In Journal of Ethiopian Studies. Addis Ababa University, 1967.

Coser, Lewis. "**Conflict, Social Aspects.**" International Encyclopedia of Social since Vol. 3. P. 232-236. The Macmillan Company and Free Press, 1968.

David, N. Fransworth "**International Relations an Introduction**". Illinois: Nelson Hall, Inc. 2004.

Fekade Azeze (Comp.). **Some Studies on Traditional and Related Methods of Conflict Resolution**. Selected And Compiled, Addis Ababa: 2004

Fisher, J. Ronald. **Social Psychology: An Applied Approach**, New York: St Martin's Press, 1982.

Fisher, D and Ibrahim Et Al. **Working With Conflict: Skills and Strategies for Action.** Bath. UK; Zed Books, 2000.

Goldstein, Kenneth. **A Guide For Field Works In Folklore**. The American Folklore Society: Folklore Association; Inc, 1964.

Gulliver, P.H. **Disputes and Negotiations: A Cross Cultural Perspective**. London: Academic Press, Inc, 1979.

Heinz J. "**Conflict- A Literary Review**". University Of Duisburg-Essen, 2006.

Kriesberg, Louis. **Constructive Conflict: From Escalation to Resolution**. Usa: Rowman and Littlefield Publishers, Inc. 1998.

Loomis, Charles P. and Zona K. Loomis. **Modern Social Theories**. Princeton D. Vans No Stand Company, Inc. 1965.

Murdock, George Peter. **African Its Peoples and Their Culture History**. New York: McGraw-Hill, 1959.

Nikodimos Idries. "**The Kunama and Their Languages**". M.A Thesis, Addis Ababa University, 1987.

Schellenberg, James A. **Conflict Resolution. Theory, Research and Practice**. Albany: State University of New York Press, 1996.

Sifting, E. Friedrich **Dynamic and Procession Nature of Conflicts**. 2006.

Tsegaye Regasa. **Learning to Live with Conflicts: federalism as a tool of Conflicts Management in Ethiopia**. (Draft Prepared For Presentation In A Training Organized By The Council Of Nationalities of The SNNPRS). Hawasa, July 2009.

Trevaskis, G.K.N. Eritrea: A Colony in Transition 1941-52. Green Wood Publishers Westport Connecticut, 1977.

Toure, T Amadou Adebayo A. (Ed.) **Comprehending Africa Conflicts: Comprehending Africa Conflicts. The Search for Sustainable peace and good governance**, London, Z Ed. Cooks, 1999.

መስፍን ዘረኣብሩክ መንገሻ፣ **ካብ ኤርትራ ክሳብ ኢትዮጵያ ዛንታን ወሎዶን**፣ አዲስ አበባ፣ ሰማያታ ማተሚያ ቤት፣1990።

ሰለሞን ተሸመ፣ "**የግድያ ግጭት ባህላዊ አፈታት በስሪ ኦሮሞዎችና አማራዎች-ንፅፅራዊ ጥናት**"፣ የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ሰለሺ አባተ፣ "**የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት**"፣ የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ቆርነሊዎስ ዐስማን፣ "**አጭር የኩናማ ብሔረሰብ ማወቅያ**"፣ አዲስ አበባ፣ 1980። (ያልታተመ)

ተክለ ጻድቅ መኩርያ፣ **የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ** ፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተምያ ቤት፣ 1961።

ታየ ገብረማርያም (አለቃ)፣ **የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ**፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1955።

ኒቆዲሞስ ኢድሪስ፣ "**የአባያዊ ቋንቋዎች ዘርፍ ክፍል አንድ-አንድ የኩናማ ቋንቋ አፋዊ ኪነተ-ቃላት ስብስቦች መዘርዝር**" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1973። (በስቴንስል ተመቶ የተባዛ ያልታተመ 50 ገፅ ያለው።)

አብርሃም ታደሰ፣ "**ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሔረሰብ**" የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1999።

አየለ ፍቅሬ፣ "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባሕር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ጎብረተሰብ"፣ የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1998።

አበበ ሃይሉ፣ "ሀገረሰባዊ የአስተዳደር ስርዓትና የግጭት አፈታት ዘዴዎች በአኝዋ ብሔረሰብ"፣ የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1999።

እምሩ ኃይለ ሥላሴ፣ <u>ካየሁት ከማስታውሰው</u>፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2001።

ዓለመ. ካሣዬ፣ "ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ሥርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ"፣ የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 1999።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ <u>የመጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት</u>፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

የወረዳ ታሕታይ አድያቦ ማስታወቂያ መምርያ፣ <u>አድያቦና መጽሔት</u>፣ መቐለ፣ ቤት ማሕተም ፕላኖግራፊ፣ 1ይ ሕታም፣ ቁፅሪ 2፣ 2000።

_____፣ <u>አድያቦና መፅሔት</u>፣ መቐለ፣ቤት ማሕተም ፕላኖግራፊ፣ 1ይ ሕታም፣ ቁፅሪ 3፣ 2001።

ዮናስ ተሸመ፣ "በአሚባራ ወረዳ የአፋር ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ"፣ የኤም. ኤ. ዲግሪ መሚያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2002።

ገ/ኪዳን ወልደሃወርያት፣ “ናይ ኩናማ ባህሊ ፅንዓት፤ አብ ብሔረሰብ ኩናማ ቅድሚ መርዓ ወሲብ ግድን እዩ”፣ እንዳስላሴ፣ መምርሒ ባህሊ ትግራይ፣ 1988። (ያልታተመ)

ፅገ ሃይለማርያም፣ ሕልመይ፣ ቤት ሕትመት ደስታ መቐለ፣ መቐለ፣ 2000።

ፈቃደ አዘዘ፣ የስነቃል መምርያ፣ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፣ 1991።

አባሪ አንድ

አውራ የመረጃ አቀባዮች አጭር መግለጫ

1. የአቀባይ ስም፡- አቶ ሃይለ ወለላ ያዲ

አቶ ሃይለ ወለላ ተወልደው ያደጉት በታሕታይ አድያቦ ወረዳ ጣብያ ለምለም ልዩ ስሙ "ገዛ መቐር" ተብሎ በሚታወቅ ቦታ ሆኖ አሁንም እዚህ ቀበሌ ኗሪ ናቸው። ሃይለ ወለላ እድሚያቸው 77 ሲሆን ከአራቱም የኩናማ ጎሳዎች ለአስታራቂነት ከሚመረጡት ካለዋ ጎሳ ተወላጅ ናቸው። የመተዳደርያ ስራቸው በእርሻ እና በብዛት ከብት በማርባት ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥም የቤተክርስትያን ሰበካ ጉባኤ አስተባበሪ እንዲሁም የአገር ሽማግሌ በመሆን የሚያገለግሉ ግለሰብ በመሆናቸው በማህበረሰቡ ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው ናቸው። እንዲሁም ተባባሪ ምልሻ በመሆን አገር ድንበራቸው የሚያስከብሩ ታጣቂ ናቸው። ይሄውም ሻብያ ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ግንባር ቀደም በመሆን አኩሪ ስራ እንደሰሩ የአካባቢው ተወላጆች ይመሰክሩላቸዋል። እኚህ በአካባቢው ማሕበረሰብ ከፍ ያለ ቦታና ክብር ያላቸው የዕድሜ ባለፀጋ አጠቃላይ የብሄረሰቡ አመጣጥ እንዲሁም የጥናቱ ትኩረት ስለሆነው የብሄረሰቡ የዕርቅ ስነ ስርዓት ሰፊ መረጃ ሰጥተውኛል።

2. የአቀባይ ስም፡- ብርሃነ ሃይለስላሴ ሸወሊ ጋሉ[51]

አቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ ዕድሜያቸው 52 ሲሆን በወረዳ ታሕታይ አድያቦ በሚገኘው የኩናማ ብሄረሰብ መገኛ ቦታ ጣብያ ለምለም "ሽምብሊና" ተብሎ በሚታወቅ የገጠር ከተማ ተወልደው ያደጉ ሲሆኑ ከአራቱ የብሄረሰቡ ጎሳዎች የ"ጉማ" ጎሳ ተወላጅ ናቸው። ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋ ዲፕሎማ አግኝተዋል። በተጨማሪም ከቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በርቀት ትምህርት ክፍል በስራ አስተዳደር ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። የአቶ ብርሃነ ሃይለስላሴ መተዳደርያ የመንግስት ስራ ነው። የታሕታይ አድያቦ ወረዳ የመንግስትና ህዝብ ግንኙነት

---

[51] በኩናማ በህዝረሰብ ላይ የሚደረግ ማንኛውም መንግስታዊም ይሁን ያልሆነ ጉዳይ እኚህ ግለሰብ ካልፈቀዱና ብሄረሰቡን ካላሳመኑ ማንም ምንም ማድረግ አይችልም። ስለሆነም ወደ አካባቢው የሚጓዝ ማንኛውም ሰው ግለሰቡን ማግኘትና ማሳመን የግድ ይለዋል። ለአብነት ያህል አንድ ነገር ላንሳ። ብሄረሰቡ ከሚገኝበት አንዱ "መዳበ" የሚባል ቦታ ለመድረስ በመጓዝ ላይ እያለን ገበያ ለመሄድ ጓዝ የተሸከሙ የብሄረሰቡ አባላት አጋጠሙን። አሸክሟቸው አስገርሞኝ ካሜራየን አቀናሁ። ፍፁም ነብር ሆነው እምቢተኝነታቸው በማላውቀው ቋንቋ ገለፁልኝ። ከመቅፅበት አሁንም በማላውቀው ቋንቋ አብረውኝ ያሉት አቶ ብርሃነ በግምት አንድ ሁለት ቃል ብቻ ተናገሩ። ወድያው የከሰመው ፊታቸው ብርሃን ተላብሶ ለፎቶግራፉ ፍቃደኛ ሆነውልኛል። ሌሎች አጋጣሚዎችም እንደዚሁ በኚህ ግለሰብ አጋዥነትና ብርታት መረጃዎቼን በአግባቡ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ቢሮ ሃላፊ በመሆን ያገለግላሉ። እንዲሁም ብሄረሰቡን በመወከል በክልልና በፌደሬሽን ምክርቤት አባል ናቸው።

አቶ ብርሃነ ብሄረሰቡ በቋንቋው የሚማርበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ላይ ታች ከሚሉ የብሄረሰቡ አባላት ውስጥ በግንባር ቀደም የሚጠቀሱ ግለሰብ ናቸው። ስለሆነም የብሄረሰቡ ተወላጆች በቋንቋቸው የሚማሩበትን መንገድ በማመቻቸት እና ትምህርቱ እንዲጀመር ባደረጉት ጥረት መስከረም 16፣ 2003 ዓ.ም በይፋ አስመርቀዋል።

አቶ ብርሃነ የብሄረሰቡን ባህል፣ እምነትና ልማድ በፅሁፍ ሰንደው ለማስቀመጥ ላይ ታች እያሉ የነበሩ አሁንም ቢሆን እያሉ ያሉ ውጤታማ ግለሰብ ናቸው። ይህውም በትግራይ ክልል በወረዳ ታሕታይ አድያቦ ቅርንጫፍ የሚገኘው የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ በነበሩበት ጊዜ "አገር በቀል እውቀት" የሚል ፕሮግራም በማዘጋጀት የብሄረሰቡ አጠቃላይ ባህልና ልማድ እንዲሁም የብሄረሰቡን ጠቃሚና ጎጂ ልማዶች በመለየት ከ 15 የሚበልጡ በእጅ የተፃፉ መጣጥፎች በደብዳቤ መልክ በቀጥታ ለክልሉ እየላኩ ብሄረሰቡን በማስተዋወቅ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል[52]። በተጨማሪም፥ በቅርቡ ወደ ህትመት የሚበቃው "የኩናማ ቋንቋና ባህል" የሚል የብሄረሰቡን ታሪክ፣ አጠቃላይ ባህሉንና ልማዱን የሚያሳይ መፅሃፍ አሰናድተው አስቀምጠዋል።

አቶ ብርሃነ በማህበራዊ ህይወታቸውም ቢሆን ተግባቢና ሰው አክባሪ ናቸው። እንዲሁም ብሄረሰባቸው ወዳድ እና ካለበት የአስተሳሰብ ይሁን የኑሮ ችግር ተላቆ ማየት የሚናፍቁ ግለሰብ ናቸው። ስለሆነም፥ እኚህ ግለሰብ አገሩን ከማስተዋወቅና ደህንነቱን ከመጠበቅ እንዲሁም መረጃ ሰጪዎች ከመምረጥና በየስብሰባ ቦታው አብሪያቸው እንድሄድ በማድረግ ሰዎችን ከማስተዋወቅና በአካባቢው የተለመደው መጓጓዣ ብስክሌታቸውን በማዋስና በየገጠሩ አብረውኝ በመንከራተት አስፈላጊውን መረጃ እንዳገኝ ረድተውኛል። በተጨማሪም በቅርቡ መፅሃፉ ለማሳተም ዝግጅት ላይ ስለሆኑ ብሄረሰቡን የሚመለከት ሁሉ ሰፊ እውቀት ያለቸው በመሆናቸው ስለብሄረሰቡ አመጣጥ፣ ባህል፣ የጎሳ ልዩነት እንዲሁም የጥናቱ ዋና ትኩረት ስለሆነው ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት "አንዱ የምንኮራበት ባህላችን ነው" እያሉ አስፈላጊውን መረጃ ሰጥተውኛል።

---

[52] የእነዚህ መጣጥፎች ቅጂዎች በአጥኚው እጅ ይገኛሉ።

3. የአቀባይ ስም፡- ደስታ ፉካ ሓዳስ

አቦይ ደስታ ፉካ ሓዳስ የ 80 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ሆነው፥ በታሕታይ አድያቦ ወረዳ ልዩ ስሙ "ገዛ አዱራ" ኗሪ ናቸው። አቶ ደስታ ክካለዋ ጎሳ ተወላጅ በመሆናቸው ብሔረሰቡን ለረጅም ጊዜ በሽምግልና ሲያስተዳድሩት የቆዩ ግለሰብ ናቸው። እንዲሁም የብሔረሰቡን ታሪክ በማወቅ አንቱ የተባሉ ናቸው። ስለሆነም የብሔረሰቡን ዋና ዋና የግጭት መከሰቻ ምክንያቶችና ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ሂደት ላይ በወቅቱ የነበራቸው የግል ህመም ሳይበግራቸው ያላለፉትን የዕርቅ ሂደት እያስታወሱ እና ምሳሌዎችን እየጠቀሱ በርካታ መረጃ በመስጠት ተባብረውኛል።

4. የአቀባይ ስም፡- ገብረ ንጉስ

አቶ ገብረ ንጉስ በ ታሕታይ አድያቦ ወረዳ ጣብያ ለምለም ልዩ ስሙ "መዳበ" ተብሎ በሚታወቅ ጎጥ ኗሪ ሆነው፥ የ69 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ናቸው። አቶ ገብረ ንጉስ በዋናነት በግብርና የሚተዳደሩ ሆነው በተወሰነ መልኩ ከብት በማርባት እንዲሁም አንዳንድ እደጥበቦች በመስራት ይተዳደራሉ።

ገብረ ንጉስ ከአራቱ የኩናማ ብሔረሰብ ጎሳዎች የጉማ ተወላጅ ሆነው በባለቤታቸው አማካኝነት ከአስታራቂው ጎሳ (ካለዋ) ጋር ቁርኝት ያላቸው ግለሰብ ናቸው። ስለሆነም በአካባቢው ለሚፈጠሩ ጥቃቅን ግጭቶችን በመፍታት ታወቁ ናቸው። እንዲሁም የተናገሩትን ሁሉ በአካባቢው ህዝብ ተሰሚነት ያላቸው ናቸው። በተጨማሪም ስለ ብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ እና ታሪክ ስለ ባህላዊው የግጭት አፈታት ስርዓት ያላቸው እውቀት ከፍተኛ እንደሆነ በብሔረሰቡ አባለት ይነገራል። ስለሆነም ስለ አጠቃላይ የብሔረሰቡ የግጭት መነሻ ምክንያቶችና የግጭት አፈታት ስርዓት መረጃ በመስጠት አግዘውኛል።

5. የአቀባይ ስም፡- መድህን ክሊ

ወ/ሮ መድህን ክሊ የ60 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ናቸው። ከአራቱ የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ጎሳዎች የ"ሸዋ" ጎሳ አባል ሆነው በጣብያ ለምለም ልዩ ስሙ "መዳበ" በተባለ አካባቢ ኗሪ ናቸው።

በብሔረሰቡ ሴቶች እንደ አዋቂ፣ እንደ ታላቅ ሰው ታይተው ለመረጃ ሰጪነት የሚመረጡ ባይሆኑም÷ በአቶ አብርሃ ሃይለስላሴ ጠቋሚነት ያገኘሁዋቸው እኚህ ወይዘሮ ስለ የኩናማ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ሰፊ ማብራርያ ከመስጠታቸው በተጨማሪ ድሮ ያለፉትን የዕርቅ ስርዓቶች እያስታወሱ መረጃ በመስጠት ተባብረውኛል።

6. የአቀባይ ስም፡- ዑስማን ሻዳ

አቶ ዑስማን ሻዳ በ ጣብያ ለምለም መዳበ የተባለ አካባቢ ኗሪ ሆነው የ66 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋ ናቸው። ዑስማን ሻዳ በብሔረሰቡ ለአስታራቂነት ከሚመረጠው ከ "ካለዋ" ጎሳ ተወላጅ ሆነው አጠቃላይ የብሔረሰቡን ታሪክ እውቀታቸውና በአካባቢው ያላቸው ተሰሚነት አንቱ የተባሉ ናቸው። ስለሆነም ስለብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ እንዲሁም ስለብሔረሰቡ ዋና ዋና የግጭት መከሰቻ ምክንያቶችና የአፈታት ስርዓት መረጃ በመስጠት እገዛ አድርገውልኛል።

7. የአቀባይ ስም፡- አስመላሽ በኪ

አቶ አስመላሽ በኪ 44 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ግለሰብ ሆነው÷ በጣብያ ለምለም "መዳበ" ተብሎ በሚታወቅ አካባቢ ኗሪ ናቸው። አስመላሽ መተዳደርያቸው ግብርና ነው። ከአራቱ የኩናማ ብሔረሰብ ጎሳዎች የ "ካለዋ" ጎሳ አባል ናቸው። በሚኖሩበት አካባቢ በንግግር አሳማሪነታቸውና በብሔረሰቡ ታሪክ አዋቂነታቸው የታወቁ ናቸው። ስለሆነም ስለብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥ፣ ስለ አጠቃላይ የግጭት መንስኤ ምክንያቶችና የአፈታት ሒደት መረጃ በመስጠት ለዚህ ጥናት መሳካት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

8. አቶ ባህር ጃዕፈር

አቶ ባህር ጃዕፈር በላይ 33 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ጎልማሳ ሆነው÷ በታሕታይ በአድያቦ ወረዳ "ሽራሮ" ከተማ ኗሪ ናቸው። ከአራቱ ብሔረሰቡ ጎሳዎች የ "ጉማ" ጎሳ አባል ናቸው። አቶ ባህር በታሕታይ አድያቦ ወረዳ የጣብያ ለምለም አስተዳዳሪ ናቸው። ስለሆነም በየጎጡ አብረውኝ በመጓዝ ከህዝብ ጋር በማስተዋወቅና ደህንነቴን በመጠበቅ እንዲሁም የሚያውቁትን መረጃ በመስጠት እገዛ አድርገውልኛል።

አባሪ ሁለት

የአጋዥ መረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

ተ.ቁ	ሙሉ ስም	ፆታ	ዕድሜ	ጎሳ	የመኖርያ አድራሻ	መግለጫ
1.	ካሽኪ ዑመር	ወ	91	ካለዋ	መዳበ	የኩናማ ብሔረሰብ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት መሪ (ሳንጋኔና)
2.	ተስፋይ ኮም	ወ	39	ካለዋ	ገዛ መቐር	ገበሬ
3.	ንጉስ ገ/እግዚአብሔር	ወ	40	ካለዋ	ገዛ መቐር	ገበሬ
4.	ዋሕድ ገ/መስቀል	ወ	33	ሴማ	መዳበ	ሚሊሻ
5.	ባህር ጃዕፈር	ወ	33	ጉማ	ሽራሮ	በወረዳ ታሕታይ አድያቦ የኩናማ ብሔረሰብ ዋና አስተዳዳሪ
6.	ለተብርሃን ሊጋ	ሴ	44	ሴማ	መዳበ	የቤት እመቤት
7.	ጋያ ጃምቦ	ወ	36	ሸዋ	ዕርዲ ወያነ	ፖሊስ
9.	አዳዲ ካላላ መንዲ	ወ	48	ሴማ	ገዛ መቐር	ገበሬ
10.	ጃምቦ ረዳ ካሳ	ወ	55	ሸዋ	ገዛ አዱራ	ገበሬ
11.	ቻካ በኪ	ወ	37	ጉማ	መዳበ	ሚሊሻ

አባሪ ሦስት

ፎቶ ግራፎች

ሀ. የኩናማ ብሔረሰብ የጎሳ መለያ የቤት ምልክት





ኩናማ ብሔረሰብ ለረጅም ዘመናት ሲመገባቸው ከነበሩ ፍራፍሬዎች ውስጥ አንዱ የሆነው "መቂዕ"


የጉማ


የሴማ

ለ. የዋና መረጃ ምንጮች ፎቶግራፎች



የኩናማ ብሔረሰብ ባህላዊ የዕርቅ ስርዓት ዋና መሪ (ሳንጋኔና) የሆኑት
አቶ ካሽኪ ዑመር፣ መዳበ

በስተቀኝ ያሉት ደግሞ አቶ ዑስማን ሻዳ፣ መዳበ



አቶ ሃይለ ወለላ ፣ ገዛ መቐር



በኩናማ ብሔረሰብ አከባቢ ብቻ የሚበቅልና ለምግብነት የሚጠቀሙበት "ቡልቱግ"

ማረጋገጫ

ስሜ እና ፊርማዬ ከዚህ በታች ያስቀመጥኩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ የትምሕርት ክፍል የድሕረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ወጥ ስራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎችና ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ሃፍታይ ገ/እግዚአብሔር አለማዮህ

ፊርማ፡-_____

የማስረከቢያ ጊዜ፡- ጥር 2003 ዓ.ም